# እፍታ አዲስ ዘመን

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 187 መጋቢት 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ኢትዮጵያ እና አሜሪካ

## ግንኙነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ተስማሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ መስማማታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንትና የዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንን ተቀብለው አነጋግረዋል።

ለረጅም ዓመታት የቆየውን የኢትዮጵያ እና የዩናይትድ ስቴትስን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር ስምምነት ላይ መድረሳቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል።

ውይይታቸውም በተለያዩ የሀገር ውስጥ፣ ቀጣናዊ እና የሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ እና በዩናይትድ ስቴትስ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ መስማማታቸውን ጽህፈት ቤቱ ገልጿል። በተጨማሪም በሀገራቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ በጥልቀት መምከራቸው ታውቋል።

በውይይቱ ወቅት ኢትዮጵያ በሰላም ስምምነቱ ላይ እያስመዘገበች ያለችው ስኬት ተቀባይነት ማግኘቱ ተመላክቷል። በኢኮኖሚው፣ በልማት ጥረቶች፣ በተለይም በግብርና እና በቀጣናዊ መረጋጋት ላይ ያሉ ጉዳዮችም ትኩረት እንደተሰጠባቸው የጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት መረጃ ያመለክታል።

ኢትዮጵያና አሜሪካ በተለያዩ የትብብር መስኮች ላይ የተመሰረተውን የረዥም ዓመታት አጋርነት ለማጠናከር የሚሰሩ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

በተያያዘ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን የአሜሪካ የውጭ

ኢትዮጵያና አሜሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

# “የተደረሰው የሰላም ስምምነት በፍጥነት ተግባራዊ መደረጉ ትልቅ ስኬት ነው”

- አንቶኒ ብሊንከን

**ግርማቸው ጋሻው እና ቢሳል ደርሶ**

አዲስ አበባ ፡- በሕወሓትና በመንግሥት በኩል በፕሪቶሪያ እና በኬንያ የተደረገውን ስምምነት ተከትሎ የስምምነት መርሆዎች በፍጥነት መተግበራቸው ኢትዮጵያ ለሰላም ያላትን ቁርጠኝነት ያሳየ ነው ሲሉ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ገለጹ፡፡

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘመን ተሻጋሪ ግንኙነት እንደምታጠናክር ገልጸው፤ በኢትዮጵያ ያደረጉትን ይፋዊ የስራ ጉብኝት አስመልክቶ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል።

በሰላም ስምምነቱ የተቀመጡ ተግባራት በፍጥነት መተግበራቸውን በተመለከተ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጋር ባደረኩት ውይይት ተረድቻለሁ ያሉት ብሊንከን በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ወደ ሰላማዊ ሕይወት እንዲመለሱ መደረጉ የሚበረታታ ነው ብለዋል፡፡

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የመሰረተ ልማቶችና የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መልሶ ግንባታ

“የተደረሰው የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ፡- ሀዲስ አብርሃ

## አፍሪካ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት የአየር ንብረት ለውጥን መቆጣጠር ይኖርባታል

ገጽ 4


















የተከበሩ ወይዘሮ ሙሉ ደርጋ



የተከበሩ አቶ አበባው ደሳለው



የተከበሩ ወይዘሮ አስቴር ከፍተው



የተከበሩ አቶ ኢተፋ ኦብሳ



የተከበሩ ወይዘሮ አዲሷ አሰፋ

# የምክር ቤት አባላት የሕዝብ ቅሬታዎችን ለመፍታት በትኩረት እንደሚሠሩ አስታወቁ

**ታደሠ ብናልፈውና አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ባደረጉት ውይይት በመነሳት የተነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት በትኩረት እንደሚሠሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አስታወቁ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በተመረጡበት አካባቢ ለአንድ ወር በመዘዋወር ሲያካሂዱት የነበረውን የሕዝብ ውይይት አጠናቀው ወደ ምክር ቤቱ ተመልሰዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የአዲስ አበባ ተመራጭ የተከበሩ ወይዘሮ ሙሉ ይርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኅብረተሰቡ የ60 ና የ90 ቀናት ፕሮጀክቶች መጀመራቸው እንዲሁም የተለያዩ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች መኖራቸውን አንስቶ፤ በኑሮ ውድነት፣ በመሰረተ ልማት መጓተት፤ የትምህርት ጥራትና የቁሳቁስ ተደራሽነት እጥረት፤ ተጨማሪ ሥራ እንደሚጠበቅ ሕዝቡ አንስቷል።

በሌላ በኩል በውይይቱ ወቅት በብልሹ አሠራር፣ በተቋማት ግንባታ መዘግየት፣ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ፣ በሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች ላይ የሚታዩ ችግሮች መፈታት እንዳለባቸው ሕዝቡ ጠይቆናል ያሉት የተከበሩ ወይዘሮ ሙሉ፤ የሕዝቡ ጥያቄ መፍትሄ እንዲያገኝ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትኩረት እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የምዕራብ ጎጃም ዞን ጅጋ ወረዳ ተመራጭ የተከበሩ አቶ አበባው ደሳለው በበኩላቸው፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦት እጥረት፣ የኑሮ ውድነት ማሻቀብ፣ የተቋማትና መሰረተ ልማት ግንባታ መጓተት፣ የመንገድ ግንባታ ዝቅተኛ አፈጻጸም፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ደካማ መሆን በቅሬታነት ከሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች ናቸው ብለዋል፡፡ በተጨማሪ በጸጥታ ምክንያት የመንገድ መዘጋት፣ በሀገሪቷ ያለው የሰላምና የፀጥታ ጉዳይና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዞኑ በርካታ ተፈናቃይ መኖሩ ከሕዝብ ጋር ባደረጉት ወይይት መነሳቱን ገልጸው፤ ከሕዝብ የተነሱ ጥያቄዎች ተገቢው መልስ እንዲያገኙ የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን ነው ያሉት።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ተመራጭ የተከበሩ ወይዘሮ አስቴር ከፍተው ደግሞ፤ የንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ የስራ እድል ፈጠራ፣ የትምህርት ጥራት፣ የኑሮ ውድነት፣ የመሰረት ልማት ግንባታና የመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ በትኩረት መስራት እንደሚገባ ኅብረተሰቡ ማንሳቱን ገልጸዋል።

የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካል የሆነው የሀላላ ኬላ በጥሩ ደረጃ ላይ መድረሱን ኅብረተሰቡ ማድነቁን የገለጹት ወይዘሮ አስቴር፤ በአንጻሩ ወረዳዎች ላይ ያለው ጥራቱን ያልጠበቀ የመሰረተ ልማት ስራ ሊስተካከል እንደሚገባ ኅብረተሰቡ መጠየቁን ተናግረዋል። ከሕዝብ የተነሱ ቅሬታዎች በየደረጃቸው እንዲፈቱ ከክልልና ከፌዴራል መንግሥት ጋር በቅንጅት እንሰራለን ብለዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የኢሉባቦር አካባቢ ተመራጭ የተከበሩ አቶ ኢተፋ ኢብሳ በበኩላቸው፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ኅብረተሰቡ ጥያቄ ማንሳቱን ጠቁመው፤ ችግሮቹ በዘላቂነት እንዲፈቱ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል ብለዋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የኦሮሚያ ክልል ወልመራ ጣቢያ ተመራጭ የተከበሩ ወይዘሮ አዲሷ አሰፋ በበኩላቸው፤ በሆስፒታሎች የመድኃኒት እጥረት መኖር፣ የፕሮጀክቶች መጓተት፣ አግባብ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪና የኑሮ ውድነት ሊስተካከል እንደሚገባው ከሕዝብ ጋር ባደረጉት ውይይት መነሳቱን ተናግረዋል።

በአንጻሩ የክልሉ መንግሥት ሽምቅ ውግያ እያካሄዱ ላሉ ቡድኖች የሰላም ጥሪ ማቅረቡን ህብረተሰቡ እንደሚደግፍ በውይይቱ መገለጹን ጠቁመው፤ በችግር የተነሱ ቅሬታዎች ላይ ትኩረት አድርጎ ለመስራትና መፍትሄው እንዲገኝ በጋራ መስራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሥነ-ምግባር ደንብ መሰረት ተመራጮች በዓመት ሁለት ጊዜ ወደየተመረጡበት አካባቢ ሄደው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ከሕዝብ ጋር ውይይት ያካሂዳሉ።

# ዝርያ በማሻሻል የእንስሳት ተዋፅኦ ምርታማነትን ማሳደግ ተችሏል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡-የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል የእንስሳት ተዋፅዖ ምርታማነትን ማሳደግ እንደተቻለ የአማራ ክልል እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ::

በክልሉ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዳዊት ገዳሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል፣ የመኖ ልማት እንዲሁም የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ስትራቴጂን በመከተሉ በእንስሳትና ዓሳ ልማት ዘርፍ ላይ አበረታች ውጤት ተገኝቷል::

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፣ በበጀት ዓመቱ 22 ሺ 376 ቶን የማር ምርት ለማምረት ታቅዶ ባለፉት ሰባት ወራት ብቻ 20 ሺ አምስት ቶን ተመርቶ የእቅዱን 89 በመቶ ማሳካት ተችሏል፤ ወተት 1 ሚሊዮን 515 ሺ 388 ሊትር በዓመት ለማምረት ታቅዶ በሰባት ወሩ 1 ሚሊዮን 62 ሺ 231 ሊትር ወተት ተመርቶ የእቅዱም 70 በመቶ ተከናውኗል:: እንቁላል 523 ሚሊዮን በዓመት ለማምረት ታቅዶ በሰባት ወሩ 400 ሚሊዮን የተመረተ ሲሆን ይህም የእቅዱ 76 በመቶ ነው::

የሀገር በቀል እንስሳትን ምርታማነት ከውጭ ደም ካላቸው ጋር ሲነጻጸር አናሳ መሆኑን የተናገሩት አቶ ዳዊት፤ ለአብነት እንቁላልን ብንመለከት ከሀገር በቀል ዶሮዎች በዓመት ከ50-60 እንቁላል የሚገኝ ሲሆን የተሻሻለው ዝርያ ካላቸው ግን በአማካይ 140 እና ከዚያ በላይ እንቁላል የሚገኝ በመሆኑ የዝርያ ማሻሻል ስራ አስፈላጊ ነው ብለዋል::

የስጋ፣ ወተት እንዲሁም የእንቁላል ምርቶችን ለማሳደግ የተሻሻለ መኖ ማልማት እና የፋብሪካ ምጥን መኖዎችን ማግኘት አስፈላጊ በመሆኑ በየደረጃው



አቶ ዳዊት ገዳሙ

በሚገኙ ባለሙያዎች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ በሰፊው ተከናውኗል::

አቶ ዳዊት አክለውም፤ ወቅቶችን መሰረት አድርገው የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎች በእንስሳቱ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ክትባት በመስጠት በሽታው ከመከሰቱ በፊት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል:: ከዚህ በዘለለ በሽታው ሲከሰት ለእንስሳት ህክምና መስጠት አስፈላጊ ስለሆነ በክልሉ ያሉ ከ90 በመቶ በላይ በሚሆኑ ቀበሌዎች የእንስሳት ክሊኒክ ተገንብቷል::

በዘርፉ የታየው አበረታች ውጤት በክልሉ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ባለፉት ሰባት ወራት ለ29 ሺ 789 ሰዎች በቋሚነትና ለ16 ሺ 48 ሰዎች በጊዜያዊነት የስራ ዕድል መፈጠሩን አቶ ዳዊት አስረድተዋል::

ከንብ ማነብ ጋር በተያያዘ ህገወጥ የኬሚካል ርጭት እንዲሁም ዘመናዊ የማነቢያ ቁሳቁሶች የዋጋ ንረት ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ እንደቀጠለ ያነሱት አቶ ዳዊት፤ አርሶ አደሩ ኬሚካል ከመርጨት ይልቅ ማረም ቢችልና ኬሚካል መርጨት አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ንቦች ወደ ማደሪያቸው ሲገቡ ኬሚካሉን መጠቀም ቢቻል እንዲሁም የሚጠቀሙት ኬሚካል በመንግሥት የተፈቀደ ቢሆን ጉዳቱን መቀነስ ይቻላል ያሉት ኃላፊው አርሶአደሮች ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል::

# በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ስኬታማ የሌማት ትሩፋት ሥራ እየተከናወነ ነው ተባለ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የሌማት ትሩፋት ተግባራዊ በመደረጉ የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ከማስጠበቅና ለዜጎች የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ ተጨባጭ ለውጦች እየታዩ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበክር ኸሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የሌማት ትሩፋት መርሃ-ግብር በተለይ የወተት፣ የእንቁላል፣ የማርና የዓሳ ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው።

በክልሉ በሚገኙ ወረዳዎች 48 ወተት የሚመረትባቸው፣ 480 የዶሮ ማርቢያ እንዲሁም 54 የንብ ማነቢያ መንደሮች ተለይተው ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ ሲሉ አስረድተዋል።

በክልሉ የሚገኘውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የቀንድ ከብት ሀብት፣ የንብ እና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘመናዊ ዘዴ በማሻሻል ለቀጣዮቹ አራት ዓመታት በሚቆየው የሌማት ትሩፋት መርሃ ግብር ምርታማነትን ለማሳደግ ይሰራል ብለዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ 7 ሺህ ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት በዶሮ ርባታ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል። ዘመናዊ የንብ ቀፎዎችን በማቅረብ ወጣቶች የአንድ ዓመት ምርታቸውን ለክልሉ እንዲያቀርቡ የሚረዳ አሰራርም ተዘርግቷል። ቀደም ሲል በዓመት ይመረት የነበረውን 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኪሎ ግራም የማር ምርት ወደ 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኪሎ ግራም ከፍ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በተጨማሪ በክልሉ በዓመት የሚገኘው የወተት ምርት ከ30 ሚሊዮን ሊትር ወደ 72 ሚሊዮን ሊትር ከፍ ለማድረግ እና የእንቁላል ምርታማነትን ደግሞ ከ22 ሚሊዮን ወደ 111 ሚሊዮን ለማድረስ ግብ ተቀምጧል ሲሉ ኃላፊው አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ባበክር ገለጻ፤ የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን ለማሳደግ የቀንድ ከብትና የዶሮ ዝርያዎችን የማሻሻልና ጤናቸውን የመበቅ እንዲሁም በቂ የመኖ ዝግጅት የማቅረብ ስራዎች እየተከናወኑ ነው።

በሌማት ትሩፋት ስራው በቀን እያንዳንዳቸው አንድ ነጥብ አራት ሊትር ወተት የሚሰጡ 1 ሺህ 100 የወተት ላሞች በክልሉ ይገኛሉ።

በሌማት ትሩፋት ስራዎች በጅምሩ ውጤቶች እየታዩ ቢሆንም በተፈለገው ልክ ዕድገት እንዳይመጣ ምክንያት የሆኑ ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመዋል። በተለይ የዶሮ ጫጩት ማስፈልፈያ ማሽኖች እጥረት ለከብቶች የሚሰጥ የተቀነባበረ የመኖ እጥረት እንዳለ ገልጸዋል።

ችግሩን ለመቅረፍ የዶሮ ጫጩት ማስፈልፈያ የተለያዩ ግንባታዎች ተጀምረዋል። በተጨማሪ በመኖ ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በመጋበዝ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አቶ ባባከር ጠቁመዋል፡፡

ባለሀብቶች ከዚህ ቀደም ትኩረት ባልተሰጣቸው ዘርፎች ላይ ገብተው እንዲሰሩ የሚረዳ ውይይት ከክልሉ መንግሥት ጋር እያካሄዱ መሆኑን ገልፀው፤ ባለሀብቶቹ በመረጡት ከተማ ለአምስት ዓመታት የሚቆይ ቦታ ተሰጥቷቸው በሌማት ትሩፋት ሥራዎች እንዲሳተፉ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

በክልሉ በሚከናወኑ የሌማት ትሩፋት ስራዎች የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚረዱ የማር፣ የዶሮ፣ የወተት እንዲሁም ሌሎች ምርቶች በስፋት በገበያ ላይ እንዲቀርቡ ይደረጋል ሲሉም ኃላፊው አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም የሌማት ትሩፋት መረሃ-ግብርን በሀገር አቀፍ ደረጃ በአርባ ምንጭ ከተማ በይፋ ማስጀመራቸው የሚታወስ ነው።

# በኦሮሚያ ክልል ለተከሰተው ድርቅ እስካሁን ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተሰብስቧል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ለተከሰተው ድርቅ ድጋፍ የሚሆን ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ:: በኦሮሚያ ክልል የተከሰተውን ድርቅ ተከትሎ ያጋጠመውን ችግር በጋራ ለመፍታት የሰብዓዊ እርዳታ ላደረጉ አካላት የሁለተኛ ዙር የእውቅና መርሃ ግብር በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል::

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ በመድረኩ ላይ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ መንግሥት በድርቅ ምክንያት የተጎዱ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየሰራ ይገኛል:: በድጋፍም እስካሁንም አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል::

በመርሃ ግብሩ ላይ ተገኝተው ድጋፍ ያደረጉትን አካላት ያመሰገኑት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በድርቅ ምክንያት እስካሁን ምንም አይነት የሰው ሕይወት እንዳላለፈ ገልጸዋል::



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አሁን ድርቅ ባለባቸው አካባቢዎች ዝናብ መዝነብ በመጀመሩ ችግሩን ያቀለዋል ያሉት አቶ አወሉ፤ አሁንም ርዳታ የሚያደርጉ አካላት ድጋፋቸውን አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል::

የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ሲሳይ በበኩላቸው፤ እውቅና የተሰጠው በገንዘብ ድጋፍ ላደረጉ 83 አካላት እንዲሁም በዓይነት ድጋፍ ላደረጉ 36 አካላት መሆኑን ተናግረዋል:: የቡሳ ጎኖፋ አባል በመሆን በሰውሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ የሚከሰቱ አደጋዎችን በጋራ መከላከል እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል::

ድጋፍ አድርገው እውቅና ከተሰጣቸው አካላት መካከል አንዱ የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር ሲሆን ተቋሙ በኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ አካላት የ100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አድርጓል::

መከላከያ ሚኒስቴርን ወክለው ንግግር ያደረጉት ብርጋዴል ጀኔራል ይልማ መኳንንቴ፤ በሀገሪቱ የተከሰተውን የድርቅ አደጋ ተከትሎ መከላከያ ሚኒስቴር ድርቁን ለመከላከል አፋጣኝ መልስ እንዲሰጥ ከአመራሩና ከሠራዊት አባላት ጋር በመወያየት ድርቅ በተከሰተባቸው ሁሉም አካባቢዎች ድጋፍ ለማድረግ ወስኗል ነው ያሉት::

በዚህም መሰረት ሠራዊቱ በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ የግዳጅ ቀጠና ውስጥ ሆኖ ከደመወዙ ላይ ይህን ድጋፍ በኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች በማድረጉ ደስተኛ ነው ብለዋል::


አቶ ሽታዬ ዩሙራ


አቶ በረከት አሰፋ

# በሲዳማ ክልል በመጪው ክረምት ከ320 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት ተደርጓል

**አብርሃም ሳሙኤል**

ሐዋሳ፡- በሲዳማ ክልል በመጪው የክረምት ወቅት ከ320 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዝግጅት መጠናቀቁን የሲዳማ ክልል ግብርና ቢሮ እና የክልሉ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን አስታወቁ::

ተቋማቱ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በመጪው ክረምት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን እውን ለማድረግ በቅንጅት ሰፊ ዝግጅት ማድረጋቸውንና ወደ ሥራ መግባታቸውን አስረድተዋል:: ችግኞችን ለመትከል ጉድጓዶች የተቆፈሩ ሲሆን፣ 32 ሺህ ሄክታር መሬትም ለችግኝ ተከላ ስራው ዝግጁ መሆኑንም አስረድተዋል::

የሲዳማ ክልል የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን ኃላፊ አቶ ሽታዬ ዩሙራ እንደገለጹት፤ በዘንድሮው ዓመት ክልሉ ከአምናው በበለጠ ሰፊ ዝግጅት በማድረግ በርካታ ስራዎችን ማከናወኑን ገልጸው፣ ለደን አገልግሎት ብቻ የሚውሉ 165 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል መዘጋጀታቸውን አመልክተዋል::

እንደ አቶ ሽታዬ ገለጻ፤ የሚተከሉ ችግኞች ለደን አገልግሎት የሚውሉ ናቸው:: እነዚህም ለማገዶ፣ ለቤት ግንባታ፣ ለጣውላና ለኢንዱስትሪ እንዲሁም ለውሃና አፈር ጥበቃ አገልግሎት የሚውሉ ተብለው የተለዩ ናቸው::

ለተከላ የተዘጋጁት ችግኞች 70 በመቶ ሀገር በቀል እና 30 በመቶ ደግሞ ከባህር ማዶ የተገኙ ዝርያዎች መሆናቸውን አቶ ሽታዬ ገልጸው፣ ለደጋማና ለቆላማ አካባቢዎች ተስማሚ የሚሆኑ እንደ ቀርከሃ፣ ዋንዛ፤ ግራቪሊያና ሌሎችም መካተታቸውን ተናግረዋል:: በቀጣይ ሚያዝያ ወር 65 ሚሊዮን ችግኞች ለተከላ ዝግጁ ናቸው ብለዋል::

በክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ የተፈጥሮ ሀብትና አነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክተር አቶ በረከት አሰፋ በበኩላቸው፤ በዘንድሮው ዓመት በቢሮው በኩል ብቻ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን 39621 ኪ.ግ የችግኝ ዘር ለማዘጋጀት ዕቅድ ተይዞ፣ 38912 ኪ.ግ ዘር በማዘጋጀት ለወረዳ ችግኝ ጣቢያዎች መሰራጨቱን ገልጸው፣ በዚህ ዓመት ለምግብነትና ለሌሎች አገልግሎት የሚውሉ በአጠቃላይ 155 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ዘር መዘጋጀቱን ገልጸዋል::

የችግኝ ዓይነቶችም የፍራፍሬ፣ የቀርከሃ፣ የመኖ፣ የቡናና፣ ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው የችግኝ ዘሮች ስለሆኑ፣ በሚያዝያ ወር በቂ ዝናብ ከዘነበ ለምግብነት አገልግሎት የሚውሉትን እስከ 30 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ሙሉ ዝግጅት መደረጉን አቶ በረከት ተናግረዋል::

ባለፈው ዓመት ከተተከሉት ውስጥ 82 በመቶ መጽደቁን ያስታወቁት አቶ በረከት፣ ኅብረተሰቡም የተተከሉትንና ገና የሚተከሉ ችግኞችን እንደራስ አድርጎ በመንከባከብና በመጠበቅ ክልሉን ወደ አረንጓዴ በመቀየር የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል::

# ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ለመቀነስ በጋራ መስራት እንዳለባቸው ተገለጸ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ሀገራት በተቀናጀ መንገድ በጋራ መስራት አለባቸው ሲሉ የውሃና ኢነርጂ ሚንስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ተናገሩ፡፡

ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ እንደገለጹት፤ አፍሪካ የበርካታ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ብትሆንም በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ በድርቅና በተለያዩ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ይከሰታሉ። በመሆኑ ተጽዕኖውን ለመቀነስ አገራት በቅንጅት በመስራት ችግሩን መቋቋም አለባቸው።


ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ

አፍሪካ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት እና ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነውን የሰው ኃይል በጋራ ለመጠቀም ስምምነት ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሀገራት መካከል ያለውን የርስ በርስ ግንኙነት በማጠናከር ከጊዜ ወደ ጊዜ የዓለም ስጋትነቱ እየጨመረ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቀነስ ጥረት ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ኢንጂነር ሀብታሙ እንደገለጹት፤ አፍሪካ ለአየር ንብረት ለውጥ መባባስ ያላት አስተዋጽኦ አነስተኛ ነው። ይሁንና በችግሩ ተጎጂነቷ ግን ከፍተኛ ሆኗል። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ድርቅ፣ የደን ቃጠሎ፣ የአፈር መሸርሸር እንዲሁም ሌሎች ችግሮች ይከሰታሉ።

በደቡብ ኢትዮጵያና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት የተከሰተው ድርቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ችግር ላይ ጥሏል። ችግሩ በሌሎች የአህጉሪቷ ቦታዎች የተለመደና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ አካል በመሆኑ ፕሮጀክት ተነድፎ በጋራ በመስራት ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የጀመረችው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ስኬታማ እና ለጎረቤት ሀገራትም ተሞክሮ የሚሆን ነው፡፡ ይህ ተግባር ሊበረታታና ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡ ኢትዮጵያ የ10 ዓመት የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እቅድ በመንደፍ የአካባቢው ሥነ-ምህዳር ለመጠበቅ የጀመረችውን ጥረት አጠናክራ እንደምትቀጥል ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ተናግረዋል፡፡

የአየር ንብረቱንም ለማስተካከል የሃይድሮ-ሜትሮሎጂካል ሥራዎችና የተለያዩ ተጓዳኝ የመሰረተ-ልማት ክንውኖችን ማከናወን ይገባል። በተጨማሪ በሀገራት መካከል የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚረዳ ጥብቅ ግንኙነት መመስረት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡


አቶ ፈጠነ ተሾመ

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ በበኩላቸው፤ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች በሀገራት መካከል በትብብር ሊሰራበት ይገባል ነው ያሉት።

በተለይም የአፍሪካ ኢኮኖሚ ከተፈጥሮ ሀብት ጥገኝነት ሙሉ በሙሉ ያልተላቀቀ በመሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳቱ የከፋ ነው፡፡ ችግሩን ለመቀነስ በተለይ የአፍሪካ ቀንድና ከሰሐራ በታች በሚገኙ አገራት የአረንጓዴ ልማት ስራዎችን በቅንጅት መስራት አለባቸው ብለዋል።

የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ለአፍሪካ ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ አሰራር ሥርዓት መተግበሪያና የአየር ንብረት ለውጡ ጉዳቶች ማገገሚያነት የሚያግዝ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር አጽድቋል።

# የአዲስ አበባ ምክር ቤት የተለያዩ ሹመቶችንና ረቂቅ አዋጆችን አጸደቀ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ምክር ቤት 2ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ ጉባኤ የተለያዩ አስፈፃሚ አካላት ልዩ ልዩ ሹመቶችንና ረቂቅ አዋጆችን አጸደቀ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባዔ በሁለተኛ ቀን ውሎው የተለያዩ ውሳኔዎች በመወሰን ትናንት ተጠናቋል።

ምክር ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የቀረበለትን የተለያዩ አስፈፃሚ አካላትና ልዩ ልዩ ሹመቶችን አፀድቋል፡፡ በዚህም መሰረት ዶክተር ጀማሉ ጀንበር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ የአረንጓዴ ልማትና የከተማ ውበት ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ ቢኒያም ምክሩ ንግድ ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ አብርሃም ታደሰ የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ አደም ኑሪ የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ በላይ ደጀን የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ፣ ወይዘሮ ሃቢባ ሲራጅ ቴክኒክና ትምህርት ሥልጠና ቢሮ ሃላፊ፣ አቶ ካሳሁን ጎንፋ የአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ አያሌው መላኩ የአዲስ አበባ አቤቱታ ሰሚ ጉባኤ ሰብሳቢ ሆነው ተሹመዋል፡፡ ተሿሚዎቹም በምክር ቤቱ አባላት ፊት ቀርበው ቃለመሃላ ፈጽመዋል፡፡ ምክር ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ ቴክኒክና ሙያ፣ ሥልጠና እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በአዲስ መልክ እንዲደራጅም ወስኗል፡፡

የከተማው ምክር ቤቱ ከተመለከታቸው ጉዳዮች መካከል የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ይገኝበታል፡፡ ምክር ቤቱ ለመረጠው ሕዝብ ድምጽ መሆን እንዲችል የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ጠንካራ አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል ተብሎ በመታመኑ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላምና ፍትህ አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ ከዚህ በፊት የነበረው አዋጅ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት እንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የምክር ቤቱ የጽህፈት ቤት አዋጅ መሻሻል ምክር ቤቱ የበለጠ አቅም እንዲኖረውና ከሕዝብ የተሰጠውን አደራ በተግባር ለመወጣት ፋይዳው የጎላ መሆኑንም አቶ ሙሉነህ አብራርተዋል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ላይ የምክር ቤት አባላት ከተወያዩ በኋላም ጸድቋል፡፡

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማና የወረዳ ምክር ቤት የሚመረጡ አባላትን ቁጥር ለመወሰን በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከምክር ቤቱ አባላት በተነሱ ጥያቄዎች ላይ ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁን በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ለከተማው ዕድገትና ልማት ሲባል የተመደበውን በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግና ደንብ ጠብቆ፣ ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው ሁኔታ ለታለመለት ዓላማ ብቻ ውሎ የተፈለገውን ውጤት ማስገኘቱን በማረጋገጥ የተገኙ ክፍተቶች ማሻሻል እንደሚገባ ምክር ቤቱ በውይይቱ አመልክቷል፡፡

የመንግሥት ተቋማት ውስጥ እየተንሰራፋ የመጣውን የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በየተቋማት የተቋቋሙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራር፣ አደረጃጀት ማጠናከር እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

ምክር ቤቱ በሁለት ቀናት የጉባዔ ቆይታው የከተማ አስተዳደሩን የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ጨምሮ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ሹመቶችን በማጽደቅ በትናንትናው ዕለት ጉባኤውን አጠናቋል።

# የሥራ ክህሎትን የሚያጎለብት ሥልጠና ለተመራጮች እየተሰጠ ነው

**አማን ረሺድ**


ፎቶ ፡- ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሚሰጠው ሥልጠና የአባላቶችን የስራ ክህሎት የሚያጎለብትና ለተሻለ ስራ መነሳሳትን የሚፈጥር መሆኑን ተገለጸ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን አቅም ለማጎልበት ያለመ የሁለት ቀናት ሥልጠና ትናንትና በምክር ቤቱ አዳራሽ መሰጠት ጀምሯል። የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ በሥልጠናው መክፈቻ እንደገለጹት፤ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የአቅም ግንባታ ሥልጠና መሰጠቱ አባላት ከሕዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የሚረዳ ነው፡፡

የሥልጠናው ዓላማ አባላትን በተለያየ መንገድ አቅማቸውን ለመገንባት ያለመ ነው ያሉት አፈ ጉባዔው፤

በመሆኑም አባላቱ ሥልጠናው ውጤት እንዲያመጣ በአግባቡ መጠቀም ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጽህፈት ቤት ኃላፊ ምስራቅ መኮንን (ዶክተር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የምክር ቤት አባላት በሀገሪቷ የመጨረሻው የሥልጣን ባለቤት ስለሆኑ በየጊዜው አቅማቸው እየተገነባ መሄድ ይኖርበታል።

በአሁኑ ወቅት እየተሰጠ ያለው ሥልጠና የምክር ቤት አባላት ነገሮችን እንዴት በጥልቀት ማየትና መመርመር እንዳለባቸው የሚያሳይ እና የአባላትን የአመራርነት ክህሎት ለማሳደግ የሚረዳ ነው ሲሉ ዶክተር ምስራቅ አስረድተዋል፡፡

የምክር ቤት አባላት የተሰጣቸውን መደበኛ ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስፈልጓቸው ክህሎቶችና አጠቃላይ አቅጣጫዎች ላይ ሥልጠናው እየተሰጠ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ለአባላት እየተሰጠ ያለው ሥልጠና ጊዜውን የጠበቀና ተገቢ ነው፡፡ የምክር ቤት አባላት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ከተወያዩ በኋላ እንዴት ቢሰሩ ሕዝቡን መጥቀም ይችላሉ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሚሰጠው ሥልጠና ዛሬ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ከሥልጠናው በመቀጠል የኢትዮጵያ አየር መንገድ አሁን ላይ ያለበት አጠቃላይ ሁኔታ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን አዲስ የገነባውን ዘመናዊ ህንፃ ምልከታ እንደሚካሄድ ተገልጿል።

# አፍሪካ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት የአየር ንብረት ለውጥን መቆጣጠር ይኖርባታል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ የዘላቂ ልማት ጎሎችን ለማሳካት የሚስተዋለውን የአየር ንብረት ለውጥ መቆጣጠር እንደሚገባት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ:: 55ኛው የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጉባዔ ከትናንት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ነው::

በጉባዔው ንግግር ያደረጉት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ነመራ ገበየሁ፤ በ2023 አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በአፍሪካ የሚስተዋሉ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ ሥራ ይጠበቃል:: አፍሪካ በዕድገት ጎዳና ውስጥ ለመግባት ጠንካራ ሥራ መስራት አለባት::

ያለፈው የፈረንጆች ዓመት ለአፍሪካ ከባድ ጊዜ እንደነበር በመጠቆም በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ምክንያቶች የኢኮኖሚ ችግሮች በስፋት የተስተዋለበት ዓመት መሆኑን አንስተዋል::

የአየር ንብረት ለውጥ በአፍሪካ የምግብ ዋስትናን ለማረጋጋጥ ችግር ሆኗል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የአየር ንብረት ለውጥን መቆጣጠር ለዘላቂ ዕድገትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋጋጥ ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብለዋል:: ለአየር ንብረት ለውጥ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ተናግረው፤ ይሁንና የአየር ንብረት ለውጥ መቆጣጠር ሥራ ያለ በቂ የገንዘብ እገዛ ትርጉም የለውም ሲሉ ገልጸዋል::

የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ጥበቃ በማድረግ በአፍሪካ የሚስተዋለውን ድህነትና ልዩነቶችን መቅረፍ ካልተቻለ አፍሪካ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅባት ጠቁመዋል::

እንደ ዶክተር ነመራ ገለጻ፤ የኑሮ ውድነት፣ የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም፣ ድህነት፣ የምግብ ዋስትና አለመኖር፣ የኢነርጂ ዋስትና እጥረትና ማኅበራዊ አለመረጋጋት መኖር የአፍሪካ የወቅቱ ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን አንስተዋል::

የድህነት መስፋፋትና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አለመኖር ለአፍሪካ አህጉር ትልቅ ፈተና ነው ያሉት ዶክተር ነመራ፤ በ2022 አፍሪካ ካሏት ዜጎች መካከል ግማሽ ያህሉ በድህነት ውስጥ ይገኛል:: ይህም ካለፉት ዓመታት እጅግ እየጨመረ የመጣ ችግር በመሆኑ በጋራ መስራት አማራጭ የሌለው ተግባር ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል::

ባለፉት ዓመታት በዓለም ደረጃ በሚስተዋሉ በሰው ሰራሽና በተፈጥሯዊ ችግሮች የተነሳ ከ150 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ወደ ድህነት አረንቋ ለመግባት አፋፍ ላይ እንደሚገኝ ተናግረው፤ በተለይ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለድህነት መባባሱ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ገልጸዋል::

አፍሪካ ካሉባት ችግሮች ለመውጣት የዓለምን ኢኮኖሚ ሂደት በትክክል መረዳትና ለዚያ የሚሆን ዕቅዶችን ለመስራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል:: የውስጥና የውጭ ሀብቶችን በማስተባበር የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ማካሄድ፣ ኢንቨስትመንትን መሳብና የማህበራዊ ጥበቃ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል::

የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ፔድሮ በበኩላቸው፤ አፍሪካ በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች ብትሆንም ባላት አቅም ልክ ባለመሰራቱ በርካታ ዜጎቿ በድህነት ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል:: የሚስተዋለውን የስራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣትና የዘላቂ ልማት እቅዶችን ቀርጾ መስራት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል::

እንደ ጸሐፊው ማብራሪያ፤ አፍሪካ እንደ አህጉር የሚስተዋለውን የአየር ንብረት ለውጥ ችግር በመቆጣጠር የስራ ዕድልን በስፋት መፍጠር፣ የምግብ ደህንነትና ማረጋገጥ አለባት:: እንዲሁም ነጻ የንግድ ቀጠናን በማጠናከር በጋራ መስራትና ድህነትን ለመቀነስ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም ይገባል::

# “የተደረሰው የሰላም ስምምነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉ አሜሪካ በእጅጉ ታደንቃለች፤ አሜሪካ ለሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ለኢትዮጵያ ከ331 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሰብአዊ ድጋፍ መደረጉን ይፋ አድርገዋል። አንቶኒ ብሊንከን እንዳስታወቁት ድጋፉ በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እና በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት አማካኝነት የሚሸፈን ነው፡፡ ድጋፉም በተለያዩ ምክንያቶች በችግር ለተጋለጡ ወገኖች ለምግብ፣ ለመድሃኒት፣ ለንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚውል መሆኑን ገልፀዋል።

በተለይ በግጭት ለተጎዱ፣ ለተፈናቀሉ፣ በድርቅ ለተጠቁ እና ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ዜጎች ሕይወት አድን ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስችል ተናግረዋል።

በፕሪቶሪያ እና በናይሮቢ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ትልቅ ስኬት ነው፡፡ ተፈጻሚነት ላይ በሁለቱም ወገኖች የተጠናከረ ስራ ሊሰራ እንደሚገባ አንስተዋል። ዘላቂ ሰላም ለማምጣትም የሽግግር ፍትህን አጠናክሮ መተግበር እና ሀገራዊ ምክክር ማከናወን ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በሌላ በኩል የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የአሜሪካ ቆንፅላ ጽህፈት ቤትን (የመን ኮሚዩኒቲ ትምህርት ቤትን) ጎብኝተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ እና ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከንን በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ማነጋገራቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

አቶ ደመቀ ከአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና ከልዑካን ቡድናቸው ጋር በሁለትዮሽ እና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገልጿል። በፕሪቶሪያ እና በናይሮቢ ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በኋላ ያሉ የአፈጻጸም ሂደቶች፣ በልማት እና የዴሞክራሲ ግንባታ በሚሰሯቸው ስራዎች እና መሰል ጉዳዮች ላይ ሁለቱ ሀገራት መምከራቸውም ተጠቁሟል።

ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ሂደት መንግሥት በቁርጠኝነት በመሥራት ላይ እንደሚገኝ አቶ ደመቀ ገልጸዋል። የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን ለማሳለጥ መንግሥት እያደረገ ያለውን ጥረት የአሜሪካ መንግሥት ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል መጠየቃቸውን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በጋራ ተጠቃሚነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተው የኢትዮ-አሜሪካ ግንኙነት ላቅ ወዳለ ደረጃ ሊሸጋገር ይገባዋል!

የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነት ዘመናትን የተሻገረ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩትም አሜሪካ በዓለም ላይ ካሏት ጠንካራ አጋሮች መካከል ኢትዮጵያ በሦስተኛ ደረጃ ተቀምጣ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በተለይም በንጉሡ ዘመን ኢትዮጵያ እንደ ዋነኛ የአሜሪካ አጋር የምትወሰድና በዚሁ ምክንያትም በተለይ በሚሊቴሪው ዘርፍ አሜሪካ ጠንካራ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች። ቀጥሎ የመጣው የደርግ መንግሥት ይከተለው በነበረው ርዕዮተ ዓለም የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም የኢሕአዴግ መንግሥት ስልጣን ከያዘ በኋላ ግንኙነቱ እንደገና ታድሶ የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ከለውጡ በኋላ ትግራይ ውስጥ ለሁለት ዓመታት የተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ እና የአሜሪካ መንግሥታት ግንኙነት ዳግም መሻከር የታየበትና የአፍሪካ ሀገራት ከቀረጥ ነጻ በሆነ መልኩ ሸቀጦቻቸውን እንዲያስገቡ ከፈቀደችው የንግድ ዕድል ኢትዮጵያ እንድትሰረዝ እስከማድረግ ደርሶ ነበር።

ሆኖም ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷ በተከበረበት ሁኔታ በሃገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለ መግባትና ለዓለም አቀፋዊ ሰላምና ደኅንነት በጋራ የመቆም የጥንት የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ በመመሥረትም በጦርነቱ ወቅት ጭምር ከአሜሪካ ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ እንዳይበላሽ በብዙ ስትጥር ቆይታለች።

ይህም ጥረቷ ፍሬ አፍርቶ ጥቅምት 23 ቀን 2015 በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶርያ የሰላም ስምምነት ከተደረሰ በኋላ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት መጠነኛ ለውጥ አሳይቷል። በሂደትም የኢትዮጵያ መንግሥት የሰላም ስምምነቱን ለመተግበርና የሰብዓዊ ድጋፍ አገልግሎቱ በአግባቡ እንዲዳረስ እያደረገው ያለው ድጋፍ በአሜሪካ ዘንድ በጎ ምላሽ አስገኝቷል። ይህ ደግሞ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ሰሞኑን አዲስ አበባ እንዲገኙ አድርጓቸዋል። የብሊንከን ጉብኝት ከጦርነቱ መቆም በኋላ በከፍተኛ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን የተደረገ ጉብኝት ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሰሜኑ ጦርነት እንዲቋጭና ይህንኑ ተከትሎም የሰብዓዊ ዕርዳታ በአግባቡ እንዲዳረስ፤ የተቋረጡ መሠረተ ልማቶች መልሰው አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ረገድ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አከናውኗል። በሌላም በኩል የሰላም ሂደትን የሚያጠናክረውን የሽግግር ፍትሕ ለመተግበር በሂደት ላይ ነው። ይህ ደግሞ በአጠቃላይ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት የሚያመላክት በመሆኑ በጦርነቱ ምክንያት ተበላሽቶ የነበረው የአሜሪካ እና የኢትዮጵያ መንግሥታት ግንኙነት ወደ ቀድሞው ቦታው እንዲመለስ ያስቻለ ነው።

ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የአሜሪካ ዋና አጋር ሆና ዘመናትን ዘልቃለች። በዚህም ሁለቱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነትንና መከባበርን ባማከለ መልኩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ሲመሩ ቆይተዋል። በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ዋነኛ ስጋት የሆነውን ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ሁለቱ ሀገራት ለዓመታት ያህል ተጨባጭና ውጤታማ ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ያላት አቀማመጥ፤ የሕዝብ ብዛት፤ እያደገ ያለ ኢኮኖሚ ባለቤት መሆኗና በቀጣናው ያላት ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ተደማጭነት በዓለም አቀፍ ፀጥታና ደኅንነት ጂኦ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ያላት ሃገር ያደርጋታል።

ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትስስሮችን የሚያጠናክሩ ታላላቅ ተቋማትን በመመሥረት ጭምር በዓለም ዲፕሎማሲ መድረክ ጉልህ ሚና ስትጫወት የቆየች አገር ናት። ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እስከ አፍሪካ ኅብረትና ኢጋድ ድረስ የዲፕሎማሲ አሻራዋን ያሳረፈችባቸው ተቋማት በርካታ ናቸው። ለዓለምና ቀጣናዊ ሰላም መስፈን ጦር ማሰማራትን ከማንም ቀድማ የጀመረችው ኢትዮጵያ፣ እንደ ጎረቤት ሶማሊያ ያሉ አገሮች ሰላማቸው ጸንቶ እንዲቆሙ ለማስቻል ብዙ መስዋዕትነትም የከፈለች ሀገር ናት።

ስለሆነም እንደአሜሪካ በመሳሰሉ ሀገራት የኢትዮጵያ ሚና በአግባቡ የሚታወቅና ግንኙነቱም በጋራ ተጠቃሚነት መርሕ ላይ የተመሠረተ ነው። ምስራቅ አፍሪካ የሽብርተኞች መናኻሪያ እንዳይሆን ኢትዮጵያ እየተጫወተችው ያለው ሚና አካባቢውን በትኩረት ለምትከታተለው አሜሪካ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። በሌላም በኩል ኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ ሀገራት ሰላም አስከባሪ ሠራዊቷን በመላክ በአፍሪካ ብሎም በዓለም ሰላም እንዲሰፍን የበኩሏን ሚና የምትጫወት ሀገር ነች። ሆኖም ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ መልኩ ያላትን ሚና በአግባቡ እንድትወጣ ደግሞ የተረጋጋ ሰላምና የተጠናከረ ኢኮኖሚ ያስፈልጋታል።

ስለሆነም ከአሜሪካ እና ከፍተኛ ተደማጭነት ካላት ዓለም አቀፍ ተቋማት ብድር፣ ያለባትን የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማሸጋሸግ፣ በጦርነቱ መዘዝ የተነፈገቻቸውን እርዳታዎች እና የበጀት ድጎማዎችን እንዲሁም ወደ አጎዋ የቀረጥ እና ታሪፍ ነጻ ንግድ መመለስ ከአሜሪካ የሚጠበቁ የቤት ሥራዎች መሆን ይገባቸዋል። ከዚህ አንጻር የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን የኢትዮጵያ ቆይታ ረጅም ዘመናት የቆውየን የኢትዮ አሜሪካ ግንኙነት ላቅ ወዳለ ደረጃ የሚያሸጋግር እንደሚሆን ይታመናል!


# አዲስ ዘመን

እፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የአንድነትን ዋጋ ከዓድዋ ተምረን ፅንፈኞችን እንታገል

**ሙሉቀን ታደገ**

የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን አንድነት የተንጸባረቀበት ከመሆኑም ባሻገር የአንድ አገር ሕዝብ ያለምንም ልዩነት በአንድነት መቆም ከቻለ ማንኛውንም ዓይነት የችግር ዳገት በቀላሉ መውጣት እንደሚችል ለዓለም ሕዝብ ማሳየት የተቻለበት ነው።

ዛሬ ላይ የአንድነትን እና የመተባበርን ጥቅም ከዓድዋ ድል የተማሩ እና የተገነዘቡ በርካታ አገራት አገራቸውን ከቅኝ ግዛት ከማላቀቅም ባለፈ ተባብረው በመሥራት ኢኮኖሚያቸውን ከፍታ ማማ ላይ ማስቀመጥ ችለዋል።

ስለ ዓድዋ ድል ሲነሳ ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ ድል ማድረግ እንዲችሉ የረዳቸውን አብይ ምክንያት ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። ኢትዮጵያውያን የዓድዋ ጦርነት ድል እንዲያደርጉ ያስቻሉ በርካታ አስቻይ ምክንያቶች ቢኖሩም አንዱና ዋነኛው ምክንያት ግን የአባቶቻችን የአመራር ጥበብ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።

ምን ዓይነት ጥበብ? ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ ይኸው ነው... ከጦርነቱ በፊት ጣሊያን የኢትዮጵያውያንን አንድነት ለመሸርሸር በማሰብ የተለያዩ የአውራጃ ገዥዎችን በጥቅም እና በስልጣን በመደለል የውስጥ አንድነትን ለማዳከም ከፍተኛ ሥራ ሠርታለች። አልተሳካም የንጉሡ የቀኝ እጅ የሆኑትን ራስ መኮንን ሳይቀር በስልጣን እና በጥቅም እስከማባበል የደረሰ ሙከራ አድርጋ ነበር።

ከተለያዩ የታሪክ ድርሳናት የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከጦርነቱ በፊት የጣሊያን ሰላዮች በንግድ እና በፖለቲካ ወኪልነት፣ በሐኪምነት እና በመሐንዲስነት በየአውራጃዎች በመሰማራት እና ለመሳፍንቱ የቅርብ ሰው በመሆን በወቅቱ በኢትዮጵያውያን መሳፍንቶች እንደ ብርቅ የሚቆጠሩትን ጠመንጃ፣ ሽጉጥ ፣ ስጋጃ፣ ጨርቃ ጨርቅ እና ሽቶ መሰል የመደለያ ዕቃዎችን ከጣሊያን እና ከአውሮፓ በማምጣት በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ የሆነ የስለላ እና የመከፋፈል ሥራ ይሠሩ ነበር።

ይህንን ተከትሎ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል መሳፍንቶች እና መኳንንቶች ለጣሊያን አድረው ነበር። የአፄ ምኒልክ የአመራር ጥበብ የተፈተነውም በዚህ ነበር። አፄ ምኒልክ እና በዙሪያቸው የነበሩ ከፍተኛ አመራሮች በአንድ በኩል በወቅቱ የአገራቸውን ጥቅም በስልጣን እና በነዋይ አሳልፈው የሰጡ የስልጣን እና የነዋይ ሴሰኛ መሳፍንቶችን እና ሹመኞችን ጥበብ በተሞላበት አኳኋን ከአገሪቱ የፖለቲካ ድግስ እንዳይሳተፉ በማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ አገራቸውን በነዋይ ያልቀየሩ አገር ወዳድ መሳፍንቶች እና መኳንንቶችን ደግሞ በፖለቲካው ድግስ ከመታደም አልፈው በአገሪቱ የፖለቲካ ድግስ ላይ ዋና አጋፋሪ መሆን እንዲችሉ አድርገዋል።

በዙሪያቸው የነበሩ ከፍተኛ አመራሮች ከነዋይ ይልቅ አገራቸውን ያስቀደሙ፤ በጥበብ የታሹ መሪዎችን በፖለቲካው ድግስ ዋና አድራጊ ፈጣሪ ማድረጋቸው እና በነዋይ ተገዝተው እኩይ ተግባር ያረገዙ ባንዳዎችን ደግሞ በጥበብ ከአገሪቱ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ ገሸሽ ማድረግ መቻላቸው የዓለምን ሕዝብ በአድናቆት «አጃይብ» አስብሎ እጅን በጉንጭ ላይ የሚያስጭን ድልን እንዲያስመዘግቡ ረድቷቸዋል። የዓድዋ ድል!

የአሁን መሪዎችም ይህንን የአባቶቻችንን ጥበብ እንደ ትምህርት ወስደው በወቅታዊ የአገራችን ፖለቲካ ሜዳ ላይ የሚታዩ ደንቃራ የሆኑ የጽንፈኛነት አስተሳሰቦችን በጥበብ ከፖለቲካው ሜዳ ማስወጣት ይገባቸዋል ባይነኝ።

«የእሳት ልጅ አመድ» እንዲሉ አሁን ላይ የዓድዋን ድል ተባብረው ያስመዘገቡ አባቶች የሆንን ልጆች የተሳፈርንበት ባቡር እና እየሄድንበት ያለው የባቡር ሃዲድ ኢትዮጵያውያን መድረስ ከሚፈልጉት የእድገት ማማ ላይ እንዲያደርስ እንቅፋቶቹ ሊወገዱለት ይገባል። የአገራችንን ሁለተናዊ እንቅስቃሴ የሚመለከት ማንም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ እውነት እኛ የዓድዋን ድል ያስመዘገቡ ልጆች ነን ? ብሎ ራሱን መጠየቁ ግድ ነው።

በተለይም በአገራችን ፖለቲከኞች መካከል የሚታየው ጤነኛ ያልሆነ እኔ ልቅደም እኔ ልቅደም በሚል የሚደረግ ሩጫ እና የእርስ በርስ መጠላለፍ ስንመለከት ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን እና አባት አርበኞች የሚያደርጉት ጦርነት እንጂ ምናችንም የዓድዋን ድል ያስመዘገቡ አባቶች ልጆች አንመስልም የሚለውን ለመጠየቅ መገደዳችን የማይቀር ነው።

አሁን ላይ ለራሳቸው የፖለቲከኛ ካባ ያለበሱ አንዳንድ ፅንፈኛ (የሃይማኖትን እና የብሔር) ፖለቲከኞች ግለሰቦች እና ቡድኖች የተለያዩ ተልካሻ ምክንያቶችን እየወለዱ እና እያዋለዱ ኢትዮጵያውያንን ወደ አንድነት ከመውሰድ ይልቅ መለያየትን መርጠው በሰፈር እና በሃይማኖት አቧድነው ወደ ከፋ ችግር ሊወስዱን እየሞከሩ ነው።

እነኝህ በጥፋት እና በጅብደኝነት የተካኑ አፅንፈኞች ይህንን እኩይ ተግባራቸውን እንደ ፖለቲካ እውቀት በመቁጠር ራሳቸውን ከስህተት ከመመልስ ይልቅ በጥፋቱ ባቡር ተሳፍረው እና ተከታዮቻቸውንም አሳፍረው በጥፋቱ ጎዳና መሽምጠጡን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል። የሚገርመው ደግሞ የአገሪቱን ችግር ማወሳሰብን እንደ ትልቅ የፖለቲካ እውቀት መቁጠራቸው ነው።

እነኝህ አካላት የፖለቲካ አዋቂ በመምሰል በየአደባባዩ ይደስኩሩ እንጂ አገራችን ችግር ገጥሟት ፖለቲካዊ የአመራር ጥበብ በፈለገችባቸው ወቅቶች አንድም ጊዜ የመፍትሔ ሃሳብ ሲያዋጡ አላየናቸውም። ሕዝብ በረሃብ እና በጦርነት አይሆኑ ሆኖ ሲፈተን እና ሲጎሳቆል እንኳን የነዋይ ሴሰኝነታቸውን ጥም ከማርካት እና የራሳቸውን ጥቅም ለማግበስበስ ከመራኮት ውጪ ለሕዝቡ ምንም ሲያደርጉ አልተስተዋሉም።

ፈላስፎች «ነፍስ ስጋን ካሸነፈቻት ስጋ የነፍስ መቃብር ትሆናለች » ያሉት እንደእነዚህ ዓይነት ፖለቲከኞችን ለማመላከት አስበው ይመስለኛል። የሚገርመው እነኝህ ፖለቲከኛ ነን ባይ ግለሰቦች ለሕዝባቸው አብዝተው እንደሚጨነቁ እና እንደሚያስቡ በየአደባባዩ ለመደስኮር የሚቀድማቸው ኃይል አለመኖሩ ነው። ለዲስኩር ሲሽቀዳደሙ ከብርሃን ፍጥነት በላይ ናቸው። እጅጉንም አታላይ እና አስመሳዮች ናቸው።

ከማስመሰል እና ከማታለል ጋር ተያይዞ አሁን ላይ በአገራችን ያሉ ፖለቲከኞችን ስመለከት የውጫሌን ውል ያጭበረበረውን አንቶኖሊን ያስታውሰኛል። ብዙዎቹ እንደ አንቶኖሊ አስመሳይ እና አታላይ ናቸው የሚሉት ሌላ የሚያደርጉት ሌላ። እንደእነዚህ ዓይነት አስመሳይ እና የአንድነትን ምስጢር መረዳት የተሳናቸውን ጽንፈኛ ፖለቲከኞችን መታገል የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው።

የውጫሌን ውል መጭበርበር እንዳጋለጠው እንደ ቀኛአዝማች ዮሴፍ ዓይነት በአመራርነት ደረጃ የሚገኙ ከመንግሥት አካላት ብዙ እንጠብቃለን። እደግመዋለሁ ! እነኝህን የፖለቲካ ካባ በለበሱ ፅንፈኞች አገራችን እንዳይሆኑ ሆና ሳያበላሿት ሁሉም ኢትዮጵያዊ አምርሮ ሊታገላቸው ይገባል።

ይህ መሆን ያለበት ዛሬውኑ ሳይረፍድ ነው። ነገር ግን ከረፈደ በኋላ በአስመሳዮች የሚፈጠርን ችግር መመለስ ዳሽን ተራራን የመውጣት ያህል እንዳያስቸግረን ያሰጋኛል። መራር ዋጋ እንዳያንከፍለንም ያስፈራኛል። ሰላም!

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የክፍለ ዘመናችን ታላቅ ግኝት

**(የመጀመሪያ ክፍል)**

አሁን አሁን በፖለቲካው ተወስደን/obsessed/ ሆነን ፤ ሁላችንም ፖለቲከኛና ተንታኝ ሆነን አረፍነው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ኪነ ጥበባዊ ጉዳዩን እርግፍ አድርገን ትተነዋል። አየሩንና መልካውን የሴራ ትንተናና የደባ ስለቃ ተቆጣጥሮታል። ለዛሬ ለለውጥ ያህል ሳይንስ ላይ ጫጭሬያለሁ። ወደፊትም ከአገራዊ ጉዳዮች መሳ ለመሳ ወቅታዊ ዓለምአቀፍ ጉዳዮች ላይ አተኩራለሁ። አበው እመው ሰማይን ያለ ባላ፣ ምድርን ያለ ካስማ ያቆምህ የሚል ይትበህል አላቸው። የፈጣሪን ጥበብና ሁሉን ቻይነት ሲገልጹ።

በአጽናፍ ዓለም /ዩኒቨርስ/ከ200 እስከ 300 ቢሊዮን የሚደርሱ ከዋክብት፤ 2 ትሪሊየን ጋላክሲዎች የሚኖሩ ሲሆን፤ ህላዌአቸው ለምድራችንና ለፍጥረት እንዲመቹ ተደርገው ነው የተፈጠሩት። በፔሬዲክ ቴብል የሚገኙ 118 ንጥረ ነገሮች መጠን እንኳ በተፈጥሮ የተመጠነ ነው ይላሉ በዝግመተ ለውጥ ሳይሆን በፈጣሪ ህላዌ የሚያምኑ የስነ ፈለግ ወይም የስነ ጠፈር ተመራማሪዎች። የ21ኛው መክዘ ክስተት የሆነው የ«ጄምስ ዌብ ቴሌስኮፕ» /አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር/ይሄን ተአምር ነው ገላልጦ ያሳየን ይላሉ ተመራማሪዎች።

የጀምስ ዌብ ቴሌስኮፕ በሰው ልጆች ታሪክ የአጽናፈ ዓለምን/universe/ወይም የህዋን/space/ ጓዳ ጎድጓዳ ፤ በርብሮና አብጠርጥሮ ጥርት አድርጎ ለዚያውም 13.8 ቢሊዮን አመት ወደኋላ ተመልሶ ያስመለከተ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ የ21ኛው መክዘ ክስተት ነው። ለግንባታው 10 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የወጣበት ሲሆን፤ ለማጠናቀቅ ደግሞ 30 ዓመታትን ወስዷል።

ከቴሌስኮፑ ግንባታ ጀርባ ያሉ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የአሜሪካ የጠፈር ምርምር (ናሳ) ፣ የአውሮፓና የካናዳ የጠፈር ሊቃውንት ተሳትፈዋል። ሊቃውንቱ ይሄን በዓይነቱ ልዩ ፣ ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ቴሌስኮፕ ሠርተው ለማጠናቀቅ አምላካቸው፤ ትዕግስቱን ፣ ጊዜውን እና ዳጎስ ያለ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ሲለማመኑ ነበር ይለናል TIME መጽሔት በስላቅ። ይኸው ልመናቸው ተሰምቶ በትዕግስት በጽናት ሦስት አስርት አመታትን ወስዶና ቢሊዮን ዶላሮቹን ፈጅቶ ለስኬት በቅቷል።

ነገሩ ወዲህ ነው በ1996 ዓ.ም የናሳ የስነ ፈለክ/astronomers/ሊቃውንት ኮሚቴ የመጪውን ትውልድ ግዙፍ የህዋ ቴሌስኮፕ ለመገንባት ወሰነ። 13.8 ቢሊዮን አመታትን ወደ ኋላ ተጉዞ ጠፈርን የሚመለከት ቴሌስኮፕ በስምንት አመት ማለትም እስከ 2007 ዓ.ም ለማጠናቀቅ አቅዶ ፣ ሆኖም ከእቅዱ በ22 አመታት ዘግይቶ፤ ከተያዘለት የ500 ሚሊዮን ዶላር በጀት 20 እጥፍ 10 ቢሊዮን ዶላር ጨርሶ በወርሀ ታኅሣሥ 2021 ዓ.ም ተጠናቀቀ። የጄምስ ዌብ ቴሌስኮፕ የጊዜንና የህዋን ርቀት አጥፍቶ ነው ህዋን የሰው ልጆች ዓይን ስር አቅርቦ እያሳየ ዓለምን ዳር እስከዳር ጉድ እያሰኘ ያለው።

ሊቃውንት አጽናፈ ዓለም ከ13.8 ቢሊዮን አመታት በፊት በተከሰተ ትልቅ ፍንዳታ/Big Bang/ ነው የተፈጠረው ብለው ያምናሉ። በአግራሞትና በአድናቆት እጅን በአፍ እያስጫነ ያለው ይህ ቴሌስኮፕ ከዛ ሩቅ ዘመን አንስቶ ነው እንግዲህ፤ በሙቀት ብርሃን ጨረር ታግዞ የሰው ልጅ እስከዛሬ ተመልክቷቸው የማያውቁ አስደናቂ የህዋን ገጽታዎች እያስመለከተ ያለው። ባለፈው ሐምሌ ሜሪላንድ በሚገኘው የናሳ ማዕከል ፤ በጀምስ ዌብ ቴሌስኮፕ የተነሱ አራት ምስሎች ለመጀመሪያ ጊዜ ፤ ለብዙኃን መገናኛዎች ይፋ ሲሆኑ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ መነጋገሪያ ሆነው ነበር ሲል የTIME መጽሔት ያወሳል ።

የሚያንጸባርቅ በሕብረ ቀለም የተንቆጠቆጠ የአቧራ መሰል ወይም የጭስ ዳመና /nebulae/ ፤ ከዚህ በፊት ታይቶ የማያውቅ ልብን በሀሴት የሚሞሉ የከዋክብት ክምችት/galactic clusters/፤ በአጽናፈ ዓለም ከዚህ ቀደም ተደርሶባቸው የማያውቁ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የከዋክብት ክምችትን/SMACS 0723/ የሚያሳዩ ምስሎች ፤ በናሳ አስተዳዳሪ ቢል ኔልሰን አማካኝነት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደንና ምክትላቸው ካማላ ሀሪስ በተገኙበት በኋይትሀውስ ይፋ ሆነዋል።

ከሥነ ሥርዓቱ በኋላ ፕሬዚዳንት ባይደን ባደረጉት ንግግር፣«እነዚህ አስገራሚ ምስሎች አሜሪካ ዛሬም ፋና ወጊና ትላልቅ ፈጠራዎችን ማከናወን እንደምትችል ለዓለም ያረጋገጡ ናቸው ።» ብለዋል፤ በማስከተለም፣ «ይህ እኛ አሜሪካውያን ማሳካት የማንችለው ምንም ራእይ እንደሌለ ያሳያል። የዌብ ቴሌስኮፕ ደግሞ ፤ የአሜሪካውያንን የማያቋርጥ አስተዋይነት የተሞላበትን የፈጠራ ችሎታ ያረጋግጣል።» በማለት አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

የዌብ ቴሌስኮፕ እስካሁን እያነሳ የላካቸው የህዋ ምስሎች በራሳቸው ስኬት ከመሆናቸው ባሻገር፤ ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለ ቴሌስኮፕ ተገንብቶ እንደማያውቅም አረጋግጧል። በ1990 ዓ.ም ወደ ህዋ ከመጠቀው ሀበል ቴሌስኮፕ እጅግ የረቀቀ ነው። የዌብ ቴሌስኮፕ ከመሬት 1.6 ሚሊዮን ኪሎ ሜትር ርቆ ህዋ ላይ የተቀመጠ ስለሆነ፤ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ይሠራል። ምህንድስናውና በህዋ ላይ የተቀመጠበት ስፍራ ከሀበል የተለየ ያደርገዋል።

የሀበል ቴሌስኮፕ ከምድራችን 547 ኪሎ ሜትሮችን ርቆ በሚገኝ ምህዋር ላይ ተቀምጦ መሬት በመዞር ህዋን ያስመለክታል። ሀብል በብረት በቱቦ ቅርጽ የተሰራ/ሲሊንደር/ ሲሆን ውስጡ ደግሞ ከአንድ አቅጣጫ የሚገባ ብርሃንን የሚቀበል ኦፕቲክስ አለው። ሀብል ምስሎችን የሚያነሳው በተለመደው አግባብ ማለትም በዓይን የሚታይ ሕብረ ቀለምን/spectrum/ በመጠቀም ነው።

ይህ ማለት መስታወቶች ከፀሐይ፣ ከመሬትና ከሌሎች አካላት ከሚመነጭ አዋኪ ብርሃን መከለል አለባቸው። የሀብል ቴሌስኮፕ የምናየውን ብርሃን ጨረር ሲጠቀም የጄምስ ዌብ ቴሌስኮፕ ደግሞ በሙቀት ጨረር የሚመነጨውን ብርሃን /infrared spectrum/፤ በመጠቀም እስከ ዛሬ ተደርሶባቸው የማያውቁ አጽናፍ ዓለማትን ማለትም፤ 13.8 ቢሊዮን አመታትን ወደ ኋላ ተመልሶ ያሳያል። ሀብል ቴሌስኮፕ ግን የምናየውን ብርሃን ስለሚጠቀም የምናየው ብርሃን ደግሞ በህዋ ውስጥ ባለ አቧራና ጭስ መሰል አየር ስለሚጋረድ የዌብን ያህል የማሳየት አቅም የለውም።

የጄምስ ዌብ የህዋ ቴሌስኮፕ 6000 ኪሎ ግራም ሲመዝን፤ ዋናው መስታወቱ ደግሞ 6.5 ሜትር ይረዝማል። ባለ ሰባት ጎን ማዕዘን 18 ክፍሎች ያሉት ቴሌስኮፕ ስለሆነ የጸጉርን አንድ ስልሳ ሺህኛ ወይም የሜትርን አንድ ቢሊየነኛ አቅርቦ የማሳየት አቅም አለው ይላል TIME መጽሔት። የሀብል የህዋ ቴሌስኮፕ ህዋን የሚዞር ፤ የመስታወቱ መጠንም 2.5 ሜትር ስለሆነ የሚያነሳው ምስል ጥራት ከዌብ በ100 እጅ ያንሳል። የዌብን የህዋ ቴሌስኮፕ ከፀሐይ ፣ ከመሬትና ከጨረቃ

**የዌብ ቴሌስኮፕ እስካሁን እያነሳ የላካቸው የህዋ ምስሎች በራሳቸው ስኬት ከመሆናቸው ባሻገር፤ ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለ ቴሌስኮፕ ተገንብቶ እንደማያውቅም አረጋግጧል።**

ሙቀት ለመከላከል የመስታወቱ ማህደር የፀሐይ መከላከያ መሣሪያ ተገጥሞለታል።

የካይት ዓይነት ቅርጽ ያለው ይህ የፀሐይ መከላከያ አምስት ንብርብር ያለው እጅግ ስስ ማለትም ከጸጉር አምስት እጥፍ ብቻ የሚበልጥ መሆኑን መጽሔቱ ያብራራል። ውጫዊ የፀሐይ መከላከያው እስከ 230 ዲግሪ ፋራናይት ወይም 110 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት መከላከል በመቻሉ፤ የቴሌስኮፑን ውስጣዊ ክፍል ከዜሮ በታች በ394 ዲግሪ ፋራናይት ወይም 237 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ቀዝቃዛ አድርጎታል። ይህ እጅግ ቀዝቃዛ የሆነው የቴሌስኮፑ ውስጣዊ ክፍል በጠፈር ውስጥ ያለውን ዝቅተኛ የሙቀት ጨረር ተጠቅሞ ፤ እስከ የህዋ ውስጠኛ አካል በመዝለቅ በቴሌስኮፑ መስታወት በመመዝገብ ወደ ሚታይ ምስል ይቀይረዋል።

የዌብ ቴሌስኮፕ ጠረፍን አቅርቦ ማሳያ ብቻ ሳይሆን ሩቅ የሆነ ጊዜንም ወደ ኋላ ተመልሶ የሚያስመለክት የጊዜ ማሽን ነው ይለዋል የTIME መጽሔት። ዛሬ በቴሌስኮፑ የምናየው የ13.8 ቢሊዮን አመት የከዋክብት ክምችት የዛሬውን ሳይሆን በሚያስገርም ሁኔታ ከ13.8 ቢሊዮን አመት በፊት የነበረውን ነው። በመላው ዓለም የሚገኙ የስነ ፈለክ ተመራማሪዎች ሳይቀር በቴሌስኮፑ በመገረምና በመደነቅ ላይ ናቸው። ዌብን ተጠቅመው ምርምር ለማድረግ ካላቸው ጉጉት የተነሳ መነሻ ሀሳባቸውን በማቅረብ ወረፋ እየያዙ ነው። የጠፈሩ ዓለም ለዘመናት ከእይታችን ሸሽጎ ያኖረውን አስገራሚና አስደናቂ ምስጢርና ውበት የዌብ የህዋ ቴሌስኮፕ እያስመለከተ ነው።

በነገራችን ላይ የዌብ የመጀመሪያው መስታወት በስሱ በወርቅ የተለበጠ መሆኑ ብርሃንን በቀላሉ እንዲያንጸባርቅ አስችሎታል። የዌብ ቴሌስኮፕ ዛሬ የሚገኝበት የጠፈር አካል ላይ ለመድረስ ከመሬት ከመጠቀ በኋላ አንድ ወር ወስዶበታል። በዓለማችን እጅግ ውድ ፣ ዘመናዊና የመጀመሪያ የሆነውን የዌብ ቴሌስኮፕ ለመገንባት ለአመታት ሌት ተቀን ሲታትሩ የኖሩ ፤ 20ሺህ ሊቃውንት የድካማቸው ፍሬ የሆነውን የዌብ ቴሌስኮፕ ሲመጥቅ ለማየት በጉጉት እየተጠባበቁ ነው፤ ትለናለች ታሪካዊ ቀኑን የእናት ምድርና የአጽናፈ ዓለም የልብ ወዳጅ የሆነው "NATIONAL GEOGRAPHIC" መጽሔት ጸሐፊ ናዲያ ድራኬ።

30 አመታትን ከፈጀ እልህ አስጨራሽ ፤ ዕቅድ፣ ንድፍ ፣ ግንባታ ፣ ጥበቃና ከተደጋጋሚ ሙከራ በኋላ ውስብስብ የሆነው የዌብ ቴሌስኮ ለመምጠቅ ተዘጋጅቷል። የማምጠቁ ሒደት በስኬት ይጠናቀቅ ወይስ አንዳች ያልተጠበቀ እክል ገጥሞት ይስተጓጎል የሚለው ጥያቄ በሁሉም አእምሮ ውስጥ እየተመላለሰ ነበር በማለት ታስታውሰናለች። የሚንቀለቀለው ሮኬት ውስብስቡን የዌብን ቴሌስኮፕ ያለ እንከን ከታቀደለት በማድረስ ለአጽናፈ ዓለም አዲስ ብስራት ይዞ ይመጣ ፤ ወይስ እንደ ቻሌንጀር ፈንድቶ ያን ሁሉ ድካም ጊዜና ገንዘብ ከንቱ አድርጎ ለናሳም ለአሜሪካም ሌላ የሀፍረት ከል ያከናንብ ስትል ጸሐፊዋ በወቅቱ ስጋቷን ገልጻ ነበር።

በመጨረሻም በግንባታው የተሳተፉ ሳይንቲስቶች ፣ ሒደቱን በቅርብ የሚከታተለው ኋይት ሀውስ ፤ ለአመታት እንደ ነፍስ ጡር ቀን ሲቆጥሩለት የኖሩት የሳተላይቱ ማምጠቂያ ቀን ታኅሣሥ 25 2021 ዓ.ም ሆኖ ተቆረጠ። ቀኑ ደረሰና ቴሌስኮፑ በደቡብ አሜሪካ ሰሜናዊ ምሥራቅ የባህር ዳርቻ ላይ በምትገኘው የፍሬንች ጉያና የጠፈር ወደብ ወደ ህዋ መጠቀ። በዕለቱም በተሳካ ሁኔታ በመምጠቅ ለ30 ቀናት የሚያካሂደውን የ1.6 ሚሊዮን ኪሎ ሜትር የህዋ ጉዞ ጀመረ። በወሩ ቀድሞ በታቀደለት የጠፈር አካል መድረሱ ተረጋገጠ። ቀጣዩ ሥራ ቴሌስኮፑ በተገጠመለት ፕሮግራም መሠረት፤ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውስብስብ የሆነ ሒደት አልፎ ለምልከታ ዝግጁ የመሆኑን ነገር ማረጋገጥ ለሳይንቲስቶች ሌላ ጭንቅ ጥብ ነበር ስትል ታስታውሰናለች።

አንዷት ሒደት ከተዛነፈች አጠቃላይ የጀምስ ዌብ ቴሌስኮፕ ተልዕኮ ይጨናገፋል ትለናለች ናዲያ። ቴሌስኮፑ ከሰው ልጅ ንክኪ ርቆ ራሱን በራሱ ለተልዕኮው ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ለዚህ ነው የናሳው ምክትል አስተዳዳሪ ፓሜላ ሜልሮይ ተልዕኮውን፤ «ለአደጋ የተጋለጠ፣ ከተሳካ ደግሞ የህዋን ምርምር ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚያሸጋግር ፤» ስትል የገለጸችው። ሆኖም ትላለች የ"NATIONAL GEOGRAPHIC" መጽሔት ጸሐፊ ናዲያ ድራኬ፤ በዘርፉ ከሚፈጥረው ተአምር አንጻር፤ የተሆነለት ነገር ሁሉ ይገባዋል። የሰው ልጅ ለዚህ መርሀ ግብር የቱንም ያህል ዋጋ ቢከፍል ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም ትለናለች።

የጄምስ ዌብ የህዋ ቴሌስኮፕ ወርቃማውንና 6.4 ሜትር የሚሰፋውን ዓይኑን ከፍቶ እያሳየን ያለው ትዕይንተ ዓለም/cosmos/፤ አይደለም ለተራው ሕዝብ ለስነ ፈለክ ሊቃውንትም በአግራሞትና በአድናቆት እጅን በአፍ የሚያስጭንና የማወቅ ጉጉትን የሚጨምር ነው። የጄምስ ዌብ ቴሌስኮፕ ህዋን ብቻ ሳይሆን ጊዜንም አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር ነው ይላሉ የአውሮፓ የስፔስ ማዕከል ከፍተኛ አማካሪ ማርክ ማክካውግሬን፤ ቴሌስኮፑ አጽናፈ ዓለም ተፈጥሮበታል ተብሎ በሳይንቲስቶች ከሚታመንበት 13.8 ቢሊዮን አመት ወደ ኋላ ተመልሶ የሚያስመለክት ነው ይሉናል አማካሪው። ቀጣዩንና የመጨረሻ ክፍል በነገው ዕትም ይጌ እመለሳለሁ።

ሻሎም !

አሜን።

# ወቅታዊ

# ‹‹ምርትን በመያዝ ሌላ ፖለቲካዊ ቀውስ ለመፍጠር የሚደረጉ ሙከራዎች አሉ ››

- አቶ ጃንጥራር አባይ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ

**ሙሉቀን ታደገ**

**በሀገራችን በተለይም ደግሞ በመዲናችን አዲስ አበባ የኑሮ ውድነቱ ከፍ ብሎ መታየቱ ከማንም የተሰወረ አይደለም::በተለይ ደግሞ ከሰሞኑን የጤፍ ዋጋ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አሻቅቧል::የመዲናዋ ነዋሪዎችም በኑሮ ውድነቱ ክፉኛ እየተፈተኑ ነው::ከዚህ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተያይዞ መንስኤው ምንድን ነው? ችግሩን ለመቅረፍስ ምን እየተሠራ ነው? ስንል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ ከሆኑት አቶ ጃንጥራር አባይ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል። መልካም ንባብ ::**


ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

**አዲስ ዘመን፡- በአዲስ አበባ ከተማ ኅብረተሰቡን እያሰቃየ ያለውን የኑሮ ውድነት የከተማ አስተዳደሩ ያውቀዋል? ካወቀው በየቀኑ በፍጥነት ለሚጨምረው የኑሮ ውድነት ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** ችግሩን የከተማ አስተዳደሩ ያውቀዋል። ያለው ኑሮ ውድነት በጣም አስከፊ መሆኑን እንረዳለን:: ከኑሮ ውድነት አኳያ በየጓዳው ገብተን የምናያቸው ችግሮች እጅግ በጣም አሳሳቢ ናቸው:: የኑሮ ውድነትን ለመፍታት ለአለፉት ሁለት ዓመታት የማኅበራትን አቅም ተጠቅመን ምርት ወደ መጋዘን እያስገባን በማኅበራት በኩል ተዘዋዋሪ ፈንድ መድበን ግዥ እንዲፈጽም በማድረግ አንጻራዊ ምርት ለነዋሪው እንዲቀርብ ተደርጓል::

ሲቀርቡ የነበሩ ምርቶቹም በጣም የድሎት ሳይሆን ኅብረተሰቡ የሚፈልገው እና በአቅሙ ልክ ሊገዛው የሚችለው አይነት ምርቶችን ነው:: ከዚህ አንጻር ስንዴ፣ ቀይ እና ሰርገኛ ጤፍ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ለኅብረተሰቡ እንዲቀርቡ ተደርጓል::

ለዳቦ ፋብሪካዎችም በቂ ጥሬ እቃ በማቅረብ ዳቦ በተመጣጠነ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እንዲቀርብ ሲሠራ ቆይቷል:: ይህንንም ለማሳለጥ ከተማ አስተዳደሩ እየደጎመ በተለይም ደግሞ እንደ አዲስ አበባ የሸገር ዳቦ ኩባንያም ድጋፍ በማድረግ እና በመቀናጀት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል::

ከላይ ከተጠቀሱት ባሻገር ለበዓላት ወቅት እንኳን ሆነ ተብሎ ምርት ሊያዝ ይችላል ብለን ስለምናስብ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር ግብይቱ እንዲሳለጥ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን እየሠራን ነው የመጣነው:: ለገናም፣ለዘመን መለወጫ ፣ ለመስቀል ፣ ለእሬቻም ለሁሉም በዓላት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር የሚያስችል አደረጃጀት እንዲሁም ግብረ ኃይል በማደራጀት እየሠራን በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚነሱ ቅሬታዎችን አንጻራዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል::

አሁን ላይ ችግሩን ያለማወቅ ወይም ችግሩን ችላ የማለት ጉዳይ አይደለም:: እንደ ከተማ አስተዳደራችን ያለው እና በቅርብ ጊዜ የገጠመን ችግር ግን ከዚህ ቀደም ከነበረው ለየት ያለ ነው:: በቅርቡም ይህ ችግር ያጋጥመናል ብለን በመስጋት ምርት በስፋት መግዛት አለብን ብለን ዩንየኖች ገዝተው እንዲያከማቹ ለማድረግ ሙከራዎች አድርገናል::

እንዳጋጣሚ ባለፉት ሁለት ወራት ምርት ወደከተማው በስፋት ያለመግባት ሁኔታዎች አስተውለናል:: ይህም ሲሆን ከተማ አስተዳደሩ ቀድሞ ለነዋሪው ገዝቶ መጋዘን ላይ የተቀመጠ ምርት ስለነበር ያንን ሙሉ በሙሉ ወደ ግብይት አስገብተነዋል:: የሚሸጥበት ዋጋም አንጻራዊ የሆነ ቅናሽ ያለው ነው ::

ነገር ግን ከኅብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ ይህ በቂ አይደለም:: በቂ ባለመሆኑ ምክንያት አሁን ላይ ዋጋው በከፍተኛ ደረጃ ንሯል:: በተለይ ጤፍ ፣ስንዴ ፣ ዱቄት እና የጥራጥሬ ሰብሎች ላይ እየተስተዋለው ያለው የዋጋ ንረት ከፍተኛ ነው::

አሁን ላይ ለተከሰተው የዋጋ ንረት በርካታ ምክንያቶች አሉ:: አንዱ ምክንያት ምርት ወደ ከተማው እንዳይገባ በማሰብ በአንዳንድ አካባቢዎች ምርት እንዳይወጣ የመከልከል ሁኔታዎች መፈጠሩ ነው:: በሌላ መንገድ ደግሞ ንግድ ላይ ያሉ፣ ድለላ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት ምርት በመጋዘን የማጠራቀም እና ወደ ግብይት እንዳይገባ የማድረግ ሁኔታዎች አጋጥመዋል:: በወፍጮ ቤቶችም ብዙ ምርቶችን በመያዝ ወደ ግብይት የሚገባውንም ምርት በትንሹ ቀናንሰው ብቻ በማቅረብ ዋጋ ሲወደድ ለመሸጥ የሚታዩ ፍላጎቶች እና ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች አሉ:: ሌላው ለዋጋ ንረቱ ዋነኛ ምክንያት በተለያዩ አካባቢዎች ኬላዎችን በመዘርጋት ምርት በነጻነት እንዳይንቀሳቀስ እና ግብይቱ እንዳይሳለጥ መደረጉ ነው:: አሁን ላይ ለተከሰተው የዋጋ ንረት ምርት እንዳይገባ የሚያደርግ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች የወለዱት ችግር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ::

ከክልሎች ጋር ባለን ግንኙነት ወይም መስተጋብር ያረጋገጥነው በዚህ ዓመት ያለው የምርት መጠን እና የተመረተው ምርት ለፍጆታ በቂ ምርት መኖሩን ነው::

ከዚህ ባሻገር የከተማ አስተዳደሩ ምርት እንዳይደርሰው ለማድረግ በሕገ ወጥ መንገድ በኮንትሮባንድ ምርቱ እንዲወጣ የማድረግ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን መረጃዎች ያሳያሉ:: በእርግጥ ይህንን እንደ ከተማ አስተዳደር የምንከታተልበትም እና የምንሠራበት ሁኔታ የለም። እኛ አዲስ አበባ ላይ ኬላ የለንም:: ምርት በነጻነት እንዲገባልን ነው የምንፈልገው:: ነገር ግን ይህ እንዳይሆን የሚያደርጉ አካላት አሉ:: እነኝህ አካላት በግለሰብ እና በቡድን ደረጃም ሕገወጥ ተግባር እየፈጸሙ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ::

አንዳንድ አካባቢ ደግሞ በአንድ ወረዳም ጭምር የመታጠር ሁኔታዎች አሉ:: ምርት ከአንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ እንኳን እንዳይንቀሳቀስ የሚደረግበት ምልክቶች ታይተዋል:: እነኝህ በጣም ትክክል አይደሉም:: በዚህም የክልል ዩንየኖች እንደፈለጉ ተንቀሳቅሰው በቂ የሆነ ምርት እንኳን ማከማቸት አልቻሉም ::

ዩንየኖች በበቂ ሁኔታ መግዛት ባለመቻላቸው አዲስ አበባ ያሉት ዩንየኖች ክልል ላይ ከሚገኙ ዩንየኖች ምርት ገዝተው ማምጣት አልቻሉም:: በሕጉ መሠረት የአዲስ አበባ ዩንየን ምርት ከአርሶ አደሮች አይገዛም:: የሚገዛው ከዩንየኖች ነው :: ይሁን እንጂ ከተማ አስተዳደሩ አለፍ ብሎ ወስኖ ከመሠረታዊ ማኅበራትም ጭምር ምርት ተገዝቶ እንዲመጣ አድርጓል:: ከማኅበራቱ ግን መግዛት አይቻልም :: ይህን ያደረግነው ኑሮ ውድነቱን ለማስታገስ በማሰብ ሕግ ጥሰን ነው ::

ሌላው የዋጋ ንረቱን ካባባሱ ምክንያቶች አንዱ ወደ አዲስ አበባ የመጣውን ምርት ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ መጋዘኖችም፣ አዲስ አበባም በማይታዩ አካባቢዎች በመከዘን እና ለወፍጮ ቤት ትንሽ ምርት በማቅረብ ወደፊትም ይጨምራል የሚል የተዛባ አመለካከትን በኅብረተሰቡ ውስጥ የመፍጠር እንቅስቃሴዎች አሉ:: ይህም የዋጋ ንረቱን ከወለዱ ምክንያቶች አንዱ ነው ::

ከዚህ አኳያ በከተማ አስተዳደሩ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት እናውቀዋለን:: የመፍትሔ አቅጣጫዎችም አስቀምጠናል:: ነገር ግን ከጥር ወር አጋማሽ በኋላ ያለው ሁኔታ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ካለው ፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር በሕገ ወጥ መንገድ ዋጋ በማናር ሕዝብን ለማነሳሳት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም ::

ምክንያቱም ምርት አለ፤ ምርት ካለ ደግሞ ወደ ግብይት መግባት አለበት:: አዲስ አበባ ግን ኬላ ዘርግታ የምትከለክልበት ሁኔታ የለም:: የምንፈልገው ምርቱ እንዲገባ ነው:: ነገር ግን እጥረት እንዲፈጠር እና ብጥብጥ እንዲነሳ የሚፈልጉ ኃይሎች መኖራቸውን ምልክቶች አሉ:: በሌላ መንገድ ደግሞ ከገባ በኋላ ትንሽ ትንሽ ብቻ ምርት በማውጣት እና በመሸጥ አብዛኛውን ምርት ደግሞ የመደበቅ ሁኔታዎች ይታያሉ:: እነኝህን እየፈተሽን ማስተካከያ እያደረግን ነው:: ነገር ግን በትልቁ ችግሩን የፈጠረው ወደ አዲስ አበባ የሚመጣው አቅርቦት አለመኖሩ ነው ::

**አዲስ ዘመን ፡- ለዋጋ መናሩ በየቦታው ሕገ ወጥ ኬላዎች መኖራቸው አንዱ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል:: ኬላዎቹ የት እና በማን የተዘጉ ናቸው ?**

**አቶ ጃንጥራር ፡-** ኬላዎቹ ያሉት የት ነው የሚለውን ነገር ልዩ ቦታው ይህ ነው ብሎ መናገር አይቻልም :: ይሁንና ኬላዎቹ እንዲነሱ ተደርጓል:: ትክክል አለመሆኑንም ከፌደራል መንግሥቱ ጭምር አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ነው:: ይህ ችግር በሁሉም አካባቢዎች የተከሰተበት ሁኔታ አለ:: ይሄ ለምን ይፈጠራል? ለሚለው እንደ አዲስ አበባም ንግድ ቢሮ ከንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ውይይት ተደርጎበታል:: ችግሩ አሳሳቢ ነው:: በተለይ ከክልሎች የሚመጣውን ምርት ወደ አዲስ አበባ እንዲገባ ነጻ መሆን አለበት የሚለውን አቅጣጫ ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

**አዲስ ዘመን ፡- በዘይት እና መሰል ሸቀጦች ላይ የዋጋ መሻሻል አይታይም:: ከቀን ወደ ቀን ዋጋቸው የመጨመር ነገር ይስተዋላል:: እዚህ ላይ የእርስዎ ምልከታ ምንድን ነው?**

**አቶ ጃንጥራር ፡-** አንዴ ዋጋቸው ከተሰቀለ በኋላ ዋጋቸው ያልቀነሱ ዘይትን የመሰሉ ምርቶች አሉ:: በነገራችን ላይ የገበያ ንረቱ ዓለማቀፋዊ ገጽታም አለው:: ሀገራዊ ብቻ አይደለም:: ከተማ አቀፍ ገጽታ ብቻ አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ የሚካሄዱ ጦርነቶች የምርት ዋጋ ላይ ንረት እንዲኖር አድርጓል:: ይሄ የሚካድ አይደለም:: ዘይት እና ስንዴ ከየት እንደምናመጣ ይታወቃል:: በመሆኑም አሁን ላይ በፊት እንደነበረው ስንዴ እና ዘይት በምቹ ሁኔታ የምናመጣበት ሁኔታ የለም ::

ይህንን ችግር መንግሥት ተረድቶ ገበያውን ለማረጋጋት ምርቶች ከመንግሥት በጀት ድጎማ እየተደረገ እየቀረቡ እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ነገር ግን የዋጋ ንረቱ ከመንግሥት ድጎማም በላይ ነው::

ነጋዴዎች ዘይትን የሚያስገቡበት ዋጋ እየታወቀ ከዚህ በላይ ዋጋ መሸጥ አትችልም ቢባል ምርቱን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ ነጋዴዎች ምርት ማስገባቱን ያቆማሉ:: ስለዚህ የመጀመሪያ አማራጫችን ነጋዴዎች ምርቱን እንዲያስገቡ ማድረግ ነው:: አቅርቦቱን ማስፋት ነው:: አቅርቦቱ በሰፋ ቁጥር የዋጋ መቀነስ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ:: ስለዚህ የመንግሥት ሚና የሚሆነው አቅርቦት እንዲኖር መሥራት ነው::

የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ መንግሥት ሁሉን አቀፍ ሙከራ እያደረገ ነው:: ለምሳሌ ምርቶችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት እና የመሳሰሉት እርምጃዎችን እየወሰደ ነው:: ይሁንና የምርቶች ዋጋ መናር ዓለማቀፋዊ አንድምታ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



ስላላቸው ችግሩ ከፍተኛ ነው። የእኛ ለየት የሚያደርገው ሸማቹ ከሚያገኘው ገቢ አንጻር ምርቶቹ የሚገዙበት ዋጋ ተመጣጣኝ አለመሆኑ ነው። ማኅበረሰቡንም ችግር ላይ የጣለው ይኸው ነው። የመንግሥት ሠራተኛው ለቤት ኪራይ የሚያወጣው ዋጋ ከፍተኛ ነው። የቤት ኪራይን እኛም ለመቆጣጠር ሕግ አውጥተናል፤ ደንብ አጽድቀናል። በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ጭማሪ እንዳይደረግ እና ከተከራዩት ዋጋ በላይ እንዳይጨምሩ እየተሠራ ነው። ምክንያቱም የዋጋ ንረት የምንለው የግድ የሰብል ምርቱን ብቻ ስላልሆነ ነው።

አንድ ደመወዝተኛ የሚያገኛትን ገቢ ለቤት ኪራይ ካዋለ ሌሎቹን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት በምን ገዝቶ ይጠቀማል? ከኑሮ ውድነቱ በተጨማሪ ሕዝባችንን እየፈተነ ያለው የሚያገኛው የገቢ አቅም ጭምር ነው። ከሚያገኛት የገቢ አቅም ለትራንስፖርት፣ለቤት ኪራይ አውጥቶ፣ለመብራት ለውሃ ከፍሎ ከዚያ የምትቀረዋን ደግሞ ጤፍ ለመግዛት የማያስችል ሁኔታ እንዳለ በብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ብሎም በብዙዎቹ የከተማ አስተዳደሩ ነዋሪዎቻችን ምሬት አለ። ይህን በደንብ በዝርዝር እናውቀዋለን። ምን ያህል ከፍተኛ ችግር እንዳለም ይታወቃል።

ይህንን ችግር ለማቃለል ቢያንስ ቢያንስ ትምህርት ቤት የሚውሉ ሕጻናትን በቀን ሁለት ጊዜ እንዲመገቡ እያደረግን ነው። የሴፍትኔት ተጠቃሚዎችንም በስፋት አገልግሎቱን እያገኙ ነው። ይሁን እንጂ ይህም ቢሆን አዲስ አበባ ላይ ካለው ችግር አኳያ በቂ አይደለም።

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ላይ ሳይወለድ የመጣ የሕዝብ ቁጥር እድገት አለ። በአዲስ አበባ ከፍተኛ የውልደት መጠን ስላለ አይደለም። ሰፊ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍል ወደ አዲስ አበባ ስለሚገባ እንጂ።

በዚህ ምክንያት የቤት ዋጋም ይንራል ፤ የሥራ ዕድል ፈጠራውንም መሻማት ይኖራል ፤ የምታመርተውን ምርት መቀራመት ይኖራል። ሁሉም ገዥ ይሆናል። የምርት ዋጋው ይጨምራል። ይህም ሌላ ምክንያት ነው። እነኝህ ሁሉ ችግሮች ባሉበት ኅብረተሰቡ በጣም የሚታገስ እና የሚተሳሰብ ሕዝብ በመሆኑ ብዙዎቹን ችግሮች ከመንግሥት ብቻ ሳይጠብቅ በራሱ ይፈታል።

በንግዱ ማኅበረሰብም በቀናነት ሕዝብን አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች መኖራቸው፤ ምርትንም በማቅረብ የሸያጭን ዋጋ ባለማናር፤ ብዙዎቹ በተለይም ኢንዱስትሪው ላይ የተሰማሩ ወገኖች እየከሰሩም ፤ ሠራተኛን በሥራቸው ላይ የሥራ አጡን ችግር ይቀንሳሉ። የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንኳን ቢያጋጥማቸው ሠራተኛ አንበትንም ብለው ዋጋ እየከፈሉ የሚያኖሩ እና ጥሩ ሥራ የሚሠሩ ኩባንያዎች አሉ። የዚህ ሁሉ ድምር ግን ኑሮ ውድነቱን ከመቀነስ አኳያ አሁንም ቢሆን መሠረታዊ ለውጥ ያልመጣበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን ።

የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የከተማ ግብርና ብለን ጀመርን፤ በዚህም ጥሩ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ብንችልም አሁንም ቢሆን ዳር እስከዳር ሁሉም ሰው የማይተገብረው በመሆኑ በቂ አቅም እና በቂ ገቢ ያለው ማኅበረሰብ ተፈጥሯል ማለት አይቻልም ።

ለተፈጠረው ችግር ዘላቂ መፍትሔ የሚሆነው ግን ገቢን ማሳደግ እና ምርትን መጨመር ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም። እኛ የምንኖርበት ከተማ ስለሆነ የግብርና ምርት ማምረት ባይቻል እንኳን ቢያንስ ከኢንዱስትሪዎች እና ከአገልግሎት የሚገኘውን ምርት ማሳደግ ያስፈልጋል።

ሁለተኛ በገጠሩ እና በክልሎች የሚደረገውን የምርት እድገት ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚያው ልክ አቅርቦቱ ከፍ ስለሚል ገቢውም እንዲሁ እየሆነ ዋጋውም እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ዓለማቀፋዊ ተግዳሮቶች ተጽዕኖ የሚያሳድሩበትን ጉዳይ ምርት እና ምርታማነት በማሳደግ ችግሩን መፍታት ካልተቻለ ችግሩ ፈታኝ ነው። ይህ ምንም የሚያሻማ አይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ትልቅ የግብርና አቅም ባለው ሀገር ብዙ ምርት አምርቶ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለውን መሸፈን የሚያስችል እድል እያለ ይህን አለመጠቀማችን በራሱ በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ምሬት እየፈጠረ ነው ።

ይህንን ከማድረግ አንጻር አሁን የተጀመሩ የምርታማነት ስትራቴጂዎች አሉ። እነኝህ የበጋ ስንዴ ምርት ፣ የመስኖ ምርት ፣ የከተማ ግብርና ሥራዎች በአጠቃላይ እንደ ሀገር የልማት ትሩፋት ተብሎ ታውጆ እየተተገበሩ ያሉ ሥራዎች ናቸው። ሁሉንም ተግባራዊ ካደረግናቸው ምርት በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። ያኔ የምርቶቹን ዋጋ ማረጋጋት ይቻላል።

በዘላቂነት የዋጋ ንረቱን ለመቀነስ ግን መፍትሔው በሁሉም መስክ ምርታማነትን መጨመር ነው። ይህ ሲባል ምርታማነት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው፣በሆቴል እና ቱሪዝም እንዲሁም በግብርና እና በመሳሰሉት ያለውን ያካትታል።

እንደ አዲስ አበባ ግን ሰፊ የጤፍ ፍጆታ ኅብረተሰቡ ይፈልጋል። ይህንን ለመፍታት አሁንም ማኅበራቱን በተጠናከረ መንገድ ምርት ወደ ከተማ እንዲያስገቡ ለማድረግ የሚያስችል ትስስር ፈጥረናል። ይህ አሁን ያለውን ችግር ለመፍታት ያስችላል ብለን እናስባለን ፤ ግብረኃይልም ተደራጅቷል፤ እየሠራ ነው ።

ግብረኃይሉ ያሉት ሥራዎች ሁለት ናቸው። አንደኛው አገልግሎቱን ማሳለጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሕገወጥነትን መቆጣጠር ነው። ከዚህ አኳያ ዋና ተቀዳሚው አጀንዳችን ምርት ወደ ገበያ እንዲወጣ ማድረግ ነው ። ዋጋ ይጨምራል በሚል ምርትን ለመያዝ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተገቢነት የላቸውም። ሁሉም ሰው በሀገሪቱ በንግድ ሕግ መሠረት መንቀሳቀስ አለበት።

ወደፊት ዋጋ ይጨምራል በማለት ትክክል ባልሆነ አስተሳሰብ ምርትን በመያዝ ሌላ ፖለቲካዊ ቀውስ ለመፍጠር የሚደረጉ ሙከራዎች አሉ። ይህ ትክክል አይደለም። ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግሥት ቁጥጥሩን አጠናክሮ ይቀጥላል። ከምንም በላይ ግን ቀዳሚ የሚሆነው አቅርቦትን ማስፋት ነው።

በዚህ አጋጣሚ ለመላ ሕዝብም ሆነ ለንግዱ ማኅበረሰብም ማሳሰብ የምንፈልገው የሕዝብን እሮሮ ለመጨመር፣ የሕዝብን ብሶት ለማባባስ በሕገወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ አካላት ከድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው የሚለውን ነው። ይህ ድርጊታቸው ተገቢ ነው ብለን አናስብም። በመንግሥት የቁጥጥር እርምጃ መውሰድ ይቻላል። ነገር ግን ከዚያ በፊት ሰዎች መተሳሰብ አለባቸው። ያላቸውን ምርት ወደ ግብይት ማውጣት አለባቸው። መጠነኛ የሆነ ትርፍ እስካለ ድረስ ዘላቂ የሆነውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ማሰብ ያስፈልጋል።

በሰዎች ጉዳት የሚገኝ ሀብት፤ በግጭት የሚያተርፍ ሰው የለም። ለግጭት የሚዳርጉ አካሄዶች እና የሰዎችን እሮሮ መሣሪያ እናደርጋቸዋለን ብለው የሚያስቡ ሰዎች ካሉ ይህ ጠቀሜታ ያለው አይመስለኝም። በእንደዚህ አይነት ድርጊት የሚሳተፉ ኃይሎች ካሉ ይህንን ‹‹ተው›› የሚል ማኅበረሰብ ያስፈልጋል። ማኅበረሰቡ ችግሩን ተገንዘዝቦ ራሱን ከማይጠቅሙ እንቅስቃሴዎች መውጣት ያስፈልጋል። ይህን በሚያደርጉ አካላት ላይ ቁጥጥሩ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

አሁን ኬላዎችም ክፍት ናቸው፤ ምርትም ክልሎች ላይ አለ። ምርት የሚገባበትን ሁኔታ እየፈጠርን ነው። ችግሩን ለመፍታት መንግሥት አልተኛም ፤እየሠራ ነው። ችግሩም በዝርዝር ይታወቃል።

**አዲስ ዘመን፡- የጤፍ ዋጋስ ከውጭ እንደሚገባው ዘይት ተሰቅሎ ይቀራል ወይስ ወደነበረበት ይወርዳል? አሁን የናረውን የምርት ዋጋ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ያስተካክለዋል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** አሁን ለምሳሌ ማኅበራት ቀደም ብለው ገዝተው የነበሩትን ምርት የሚሸጡበት ዋጋ እንደገባበት ጊዜ ይወሰናል። ከ4 ሺ 800 እስከ 6 ሺ 500 ድረስም ሲሸጡ ቆይተዋል። አሁን ያለን ስምምነት የጤፍ ዋጋ በተለይ ከማኅበራት ጋር መጠባበቂያ በመውሰድ የእኛ ማኅበራት ለክልል ማኅበራት ገንዘብ በመስጠት ከየአካባቢው ገዝተው እንዲያመጡ ስምምነት ላይ ደርሰናል። ስምምነታችን ዋጋውን በሚቀንስበት መንገድ ላይ ያተኩራል። የትራንስፖርት ዋጋና መሰል ሁኔታዎችን ጨምሮ አዲስ አበባ ላይ የሚገባበትን ዋጋ ገና እያየነው ነው። ነገር ግን አሁን የሚወራውን አይነት ከፍተኛ የዋጋ መጠን በአንጻራዊነት ይቀንሳል ብለን አቅደን እየሠራን ነው። ይህም ተከታታይ የሆነውን የምርት ክምችት መፍጠር ከቻልን ቢያንስ ቢያንስ ዝም ብሎ የተሰቀለውን ዋጋ አንጻራዊ የሆነ ቅናሽ እንዲያመጣ ለማድረግ እየተሠራ ነው። ይህ ማለት ግን ችግር አይኖርም ማለት ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ መዛባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ባለፈው ዓመት 6 ሺ 500 ይሸጥ የነበረው ጤፍ አሁን ከ6 ሺ 500 በታች እናወርደዋለን ማለት አይደለም። ይህ ሊሆን አይችልም። ቢያንስ ቢያንስ እንኳን ገበያው የሰቀለውን፤ ድንገት የወጣውን ፤በሕገወጥ መንገድ ከፍ ያለውን ዋጋ በሚፈታ መልኩ እንዲወርድ የሚያስችል እንቅስቃሴ ይደረጋል። በምን ያህል መሸጥ አለበት የሚለውን መወሰን የሚቻለው ምርቱ በስፋት ቀርቦ ዋጋውን ስናየው ነው ።

አሁን ባለን ግምገማ አዋጭ ነው ብለን የገባንበት ሁኔታ አለ። ገበያ ላይ ያለው ማለትም እዚህም እዚያም በሚደረገው አሉባልታ ያለው የገበያ ዋጋና እኛ የምንገዛበት ዋጋ በፍጹም ልዩነት አለው። እርሱን ዝቅ አድርገን የምናቀርብበት ሁኔታ ይፈጠራል። በልበ ሙሉነት በዚህ ዋጋ የማንልበት ምክንያት ግዢው ላይ የሚሳተፈው ማኅበር ገና ወደ ክልሎች ሄዷል። ከክልሎች ሰብስቦ ይዞ የሚመጣውን ዋጋ በሚቀጥለው ሳምንት አካባቢ የሚያቀርብ ይሆናል። እኛም ስለሁኔታው የምንገልጽበት ሁኔታ ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ኑሮውን ለማረጋጋት በሚል የሰንበት ገበያ ተቋቁሞ ነበር። በተጨማሪ ማኅበራት ለዳቦ አምራቾች ግብዓት እንዲያቀርቡ ሲደረግ ነበር። ይህና መሰል ተግባራት የኑሮ ውድነቱን አቅልሎታል ተብሎ ይታሰባል? ካሉ ተጨባጭ መሳያዎችን ቢጠቅሱልን?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** እውነት ለመናገር የሰንበት ገበያ በየአካባቢው በመፈጠሩ ምክንያት ዋጋን ከማረጋጋት አኳያ ብዙ አዎንታዊ ሚናዎችን ተጫውቷል። በአዲስ አበባ መጀመሪያ ላይ 119 የሰንበት ገበያዎች ነበሩ። በኋላም 126 የሆኑ አካባቢያዊ ገበያዎች ተፈጥረዋል። በዚህም አንጻራዊ የዋጋ ቅናሽ ባለው ሁኔታ ምርት የሚገዛበትን ሁኔታ አመቻችቷል።

አንዳንድ ጊዜ ምርቱን ከተፈለገበት ለማድረስ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በአዲስ አበባ ውስጥ ምርት ጭኖ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ደግሞ የምታወጣው ወጪ በጣም ከባድ ነው። የታክሲ ዋጋ፤ እኔ እጭናለሁ በሚል የሚደረግ ፍትጊያና የጫኝ አውራጅ ክፍያ ብዙ ነው። እነኝህን ሁሉ ችግሮች ተቋቁሞ የሰንበት ገበያዎች የሕዝቡን ችግር በሚፈታ መንገድ አካባቢያዊ ግብይት መፈጠር ችለዋል።

ሁለተኛ ገበያው የተፈጠረላቸው አካላት ቀጥታ አምራቾች በመሆናቸው ምርቱን ይዘው መጥተው እዚያው ቆመው የሚሸጡ ስለሆነ መሐል ላይ ያለውን ደላላ ለማስቀረትም ተችሏል። መሐል ላይ ያለው የገበያ ሸግግር ቀንሷል። ይህንና መሰል ነገሮች ደግሞ ዋጋውን እንዲቀንስ እድል ሰጥተውታል። ይህ ሲባል ግን ሰው ከሚገዛበት አቅም አንጻር አይደለም የሚታየው። ገበያ ላይ ካለው ዋጋ አኳያና ከሚያወጣው ወጪ አንጻር እንጂ። ስለዚህም የሰንበት ገበያ ለነዋሪዎቹ ዋጋን ከማረጋጋት አንጻር መልካም አጋጣሚን ፈጥሮ የቆየ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ይህ አልቆመም፤ ይቀጥላል።

አሁን ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ጾም ላይ ነው። ስለሆነም በዚህ ሰሞን የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ጨመር ያለበት ሁኔታ አለ። በእስልምናውም የረመዳን ጾም በቅርቡ ይጀምራል። ኢድ አልፈጥር በዓል እና የትንሳኤ በዓልም በተከታታይ እንደሚመጡ ይታወቃል። በመሆኑም ከበዓላቱ ጋር ተያይዞ ሊፈጠሩ የሚችሉ የዋጋ ንረቶችን ለመከላከል እየተሠራ ነው።

ይህንን ችግር ለመፍታት የት አካባቢ ላይ ነው ምርት ያለው? ብለን ምርቱ ካለበት አካባቢ ጋር ትስስር ለመፍጠር እየሠራን ነው። ከዚያ ውጪ እነዚህ አምራቾች በቀጥታ ወደ ገበያው ይዘው እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራ እንሠራለን። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ አንጻራዊ የሆነ ቅናሽ ይኖራቸዋል። ምርቱን በሚፈልገው አካባቢ ማግኘት ለኅብረተሰቡ ይጠቅማል የሚል እሳቤ አለን ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሚዲያውም የራሱን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከሕገወጦቹ ጋር በተያያዘ ምን መነሻ ተደርጎ ነው እየተሠራ ያለው? መንግሥት የደረሰበት ግምገማ ካለ ቢጠቀስ ?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** ግብረኃይሉ ተደራጅቶ እየሠራ ነው። በተጨባጭ ምንድነው ምክንያቱ ብለን ብናይ መጀመሪያ ሆኖ ያገኘነው ምርት ወደአዲስ አበባ እንዳይገባ የማድረግ ሁኔታዎች አሉ። ኬላዎች ይዘጋሉ፤ ምርት ይጨምራል በሚል ዝቅተኛ ዋጋ ጭምር ተወስኗል የሚል ነገር በአንዳንድ አካባቢዎች ሰማን። ችግሮች አሉ ብለንም ለንግድና ቀጣናዊ ትስስርም ጉዳዩን አቀረብን። በዚህም ኬላዎች እንዲከፈቱና መሰል ችግሮች እንዲታረሙ በሚልም አቀረብን። በዚህም ጥሩ ምላሽ ተገኝቷል።

ሌሎች ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ደግሞ በየክልሎቹ ላይ ገዝተው እዚያው በአካባቢያቸው

# ወቅታዊ

እያከማቹ ያሉ ነጋዴዎች እና ደላሎች መኖራቸውን ሰማን:: እኛ በዓይናችን ሄደን የት አካባቢ ምን ያህል ምርት፤ የትኞቹ ወፍጮ ቤቶች የሚለውን አላየንም:: ይህ ነገር እንደሚኖር ግን መገመት የሚያዳግት አይደለም:: ምክንያቱም ዋጋ ሲተመን ፤ ኬላ ሲዘጋ ምርቶችን ሰብስቦ ማከማቸቱ የሚቀር አይደለምና:: ከዚህ አንጻር ከክልሎች ጋር ተግባብተን እየሠራን ነው::

ከዚህ አለፍ ባለ መንገድ ደግሞ ፖለቲካ ችግር እንፈጥራለን የሚሉ አካላት ሊኖሩ ይችላሉ:: እነማን ናቸው የሚል ጥያቄ ቢነሳ ልንመልስ አንችልም:: ምክንያቱም መልሱ ሊመለስ የሚችለው በምርመራ ስለሆነ:: ነገር ግን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማስተካከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየሠራን ነው::

በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ምርት ተከማችቷል የሚሉ ሀሳቦች ይሰማሉ:: የት ላይ ነው ያለው የሚለውን ገና እየፈተሽን ነው:: ማነው በዚያ መንገድ እየተሳተፈ ያለው የሚሉትን እያየን ነው። አስቀድመን ግን በሕገወጥ መልኩ ምርት ለአከማቹ አካላት እጃችሁ ላይ ያከማቻችሁት ምርት ካለ ወደገበያ አውጡ ስንል ጥሪ እያስተላለፍን ነው:: የንግድ ሕጉ በሚፈቅድላችሁ ሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆናችሁ ተንቀሳቀሱ፤ ይህ አይጠቅምም:: ሁላችንም ለሕዝባችን ማሰብ ያስፈልገናል:: ልናስብ ይገባልም የሚል ነው:: «አይ ይህንን አላደርግም፣ በሕገወጥ በመደበቅ ጊዜውን አልፌው እንዲህ አደርጋለሁ» የሚል ሰው ካለ ከሕግና ከሰው እይታ ውጪ ስላልሆነ መረጃዎች መስጠት ያስፈልጋል፤ እርምጃ እንወስዳለን::

ይህ ደግሞ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ የሚወሰድ እርምጃ ነው የሚሆነው፤ያ ደግሞ አደገኛ ነው፤ አያስተምርም:: የሚያስተምረው መተሳሰብ ሲኖር ብቻ ነው:: የተወሰነ ጥቅም የሚያገኝ ሰው ለሌላው ሕዝብም ማሰብ አለበት :: የኢትዮጵያውያን ባሕላችንም ይህ ነው::

የዳቦ ገበያውንም ለማረጋጋት በየቦታው በርካታ ቁጥር ያላቸው የዳቦ ፋብሪካዎች አቋቋምን:: አሁንም እያቋቋምን ያለነው:: ለእነዚህ ስንዴ ዱቄት ያስፈልጋቸዋል:: ማኅበራት ደግሞ ይህንን እንዲያቀርቡ የሚያስችል ሥርዓት እየዘረጋን ነው :: ከክልል እንዲመጣ ኬላዎች መከፈትና ነጻ መሆን አለባቸው እያልን ነው:: ይህም ሆኖ ደግሞ አንዳንዶቹ ቀና ሆነው ለሕዝባችን መድረስ አለብን ብለው ከሚያመርቱት ምርት ደጉመው እያቀረቡ ባሉበት እኔ ብቻ ልጠቀም በሚል ይህንን አጋጣሚ ለሌላ ዓላማ መጠቀም ተገቢ አይደለም:: ወይም ለሕዝብ አመጽ ማነሳሻነት ለመጠቀም የሚያስቡ ኃይሎች ካሉ አይጠቅማቸውም:: በሕዝብ ግጭት የሚያተርፍ የለም:: ዝም ብሎ መቆጣጠር፤ እርምጃ መውሰድ፤ የት ገባህ የት ወጣህ በማለት ማሳደድ ሳይሆን መተሳሰብ ነው መቅደም ያለበት፡፡

ምርት የያዘ ሰው ወደ ገበያው ያውጣ፤ ሕዝብ መቸገር የለበትም ነው እያልን ያለነው:: ይህ እስኪሆን ድረስ እኛ አንቆምም:: በየትኛውም አካባቢ ያለው ምርት ወደ ከተማ እንዲገባ የሚያስችል እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተናል፤ ደግሞም ይሳካልናል ብለን ነው የምናስበው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግብረኃይሉ ከምን ከምን የተውጣጣ ነው?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** የግብረኃይሉ አደረጃጀት በምክትል ከንቲባ የሚመራ ሲሆን፤ የንግድ፣ የገቢዎች፣ የፖሊስ ኮሚሽን፣ ደንብ ማስከበርና ማኅበራትን ያቀፈ ነው:: ይህ አደረጃጀት ክፍለ ከተማ ላይ አለ:: ወረዳ ላይም እንዲሁ ተፈጥሯል:: ስለዚህም በየወረዳዎች ላይ ያለው ሁኔታ ሁሉ ይታወቃል ::

ከማኅበራት ጋር ተያይዞ በእቅድ መመራት እንዳለባቸው ይታወቃል:: ከዚህ አንጻር ማኅበራት መቼ ምርት ማቅረብ እንዳለባቸው፤ የት መግዛት እንዳለባቸው አቅደን አሁን ወደ ሥራ ገብተናል፤ ከሳምንት በኋላም ውጤቱን መለካት እንጀምራለን ::

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ በፊትም ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ያውቃል:: ያሳቸው ውጤታማነት ግን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: አሁን የተቋቋመው ከዚህ አኳያ ውጤታማነቱ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ጃንጥራር፡-** በነገራችን ላይ ይህ ድንገተኛ አጋጣሚ ሆነብን እንጂ ግብረ ኃይሉ በመሥራቱ ብዙ ነገሮችን ፈትቷል:: ቀደም ብዬ ገልጫለሁ:: ምርት ባለበት አካባቢ እየሄደ ምርት ያመጣል:: ማኅበራት ቅርብ ጊዜም ተነቃቅተው ምርት እንዲያስገቡ በማድረግ ሽያጭ እንዲያከናውኑ እየተደረገ ነው:: ለበዓላት የእንስሳት ውጤቶችም፤ የግብርና ምርቶችም በስፋት እንዲቀርቡ የተደረገው ክፍተት ያለበትን እየገመገምን በመሙላት

> **የ**ደላላን ጣልቃ ገብነት መበጣጠስ ይጠይቃል። ህገወጥ ኬላዎችን ማጥፋት ይጠይቃል። አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት በነጻ የሚሸጥበት እድል ሊፈጠር ይገባል። ይህንን ለማድረግ በአንድ ከተማ ብቻ የሚታጠር አይደለም። ከክልሎች ጋር መቀናጀት የግድ ነው

ነው::

አሁን ቅርብ ጊዜ የተፈጠረው ጉዳይ ግን ቅድም እንደገለጽኩት ከሕገወጥነት ጋር በተያያዘ ችግር የተከሰተ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ከተማ አስተዳደሩ እንደውም ከከተማው ውጪ አቅዶ እየሠራ ነበር:: ምርትም ለማስገባት ሞክሯል:: ሰው እየተቸገረ ምርትን ይዘን መቆየት ስለሌለብን ለመጠባበቂያ በመጋዘን ይገኙ የነበሩ ምርቶችን አውጥተን ሸጠናል::

የግብረ ኃይሉ ዋነኛ ሥራው ነገሮችን ማስተባበር ላይ እንጂ ጤፍ ኖሮት ጤፍ የሚያቀርብ ፤ ስንዴ ኖሮት ስንዴ የሚያቀርብ አይደለም:: ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ ገበያውን ለመቆጣጠር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ማሳለጥ ነው:: ለምሳሌ የእሁድ ገበያን ጸጥታ፣ የሚቀርቡ ምርቶች ችግር እንዳይገጥማቸው ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤ አርሶ አደሮች ግብይት እንዲፈጠርላቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ወደ ግብይት እንዲገባ በማድረግ፤ ክፍለ ከተማና ወረዳ ላይ ያለው ጥምረትን በሚመለከት ሲሠራ ነው የቆየው::

ግብረኃይሉ ዝም ብሎ የሚቋቋምና የሚፈርስ አይነትም አይደለም:: ይህንን እንደገና የከለስንበት ብሎም አደረጃጀቱም በአግባቡ ሲመራ ነው የቆየው። ነገር ግን ከዚህ ወጣ ባለ መንገድ ለየት ያለ ባህሪ ያለው መሆኑ ተጨማሪ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል የማጠናከር ነው። አዲስ የማፍረስ አዲስ የመገንባት አይነት አይደለም። ዋናው የግብረኃይሉ ሥራ ማመቻቸት ወይም ማደራጀት እና ቁጥጥር ሥራዎችን ማከናወን ነው። ለአቅርቦቱም እንዲሁም የግብይት ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚያስችል አደረጃጀት ነው እንደከተማ ወስነን እየገባንበት ያለው።

**አዲስ ዘመን:- ሕገወጦች ትልቅ ሚና አሳቸው ከሚባሉት ደላሎች ተጠቃሾች ናቸው። የደላላን ጣልቃ ገብነት ከማስቆም አንጻር የተሠራው ሠራ ምንድን ነው ?**

**አቶ ጃንጥራር:-** ደላላ ይኖራል። አይኖርም ማለት አይደለም። ለአብነት በመንግሥት በኩል በዓላት ሲቃረቡ የማዋከብና በገበያ ቦታዎች ላይ ችግሮችን የመፍጠር ሁኔታዎች እንደነበሩ ይታወሳል። ይህ እንዳይኖር የሚያስችል እንቅስቃሴ ባለፉት በዓላት አድርገናል። ለገና በዓልም ለዘመን መለወጫም ለአረፋ በዓልም ወዘተ በሁሉም በዓላት ላይ ማለት ይቻላል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ደላላውና ነጋዴው የመቀላቀል ሁኔታዎች ያጋጥማሉ። ነጋዴ በተፈቀደለት የንግድ ፍቃድ መሠረት ምርት ወይም አገልግሎትን ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ነው። ስለዚህ ምርትና አገልግሎትን ገዝቶ ወደ ውጭ ይልካል፤ ወይም ደግሞ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል::

በአንጻሩ ደላላው ወይም ሕገወጡ አካል ደግሞ በተጠቃሚውና በአቅራቢው መካከል ያለውን የፍላጎትና የአቅርቦት መጣጣምን ሚዛን በማሳጣት በዚህ መካከል የሚገኘውን ትርፍ በራሱ ያደርጋል:: በዚህም የከፋ ጉዳት ያደርሳል:: ይህ አካሄድ በሕዝብ ላይ ጫና ከመፍጠር በቀር ሌላ የሚያስገኘው ጥቅም የለም ። ስለሆነም ሕገወጦች ከዚህ ተግባራቸው ሊታቀቡ ይገባል::

ሸንኩርትን ከሸዋ ሮቢት ጭነን ካመጣን እና ሸዋ ሮቢት ያለው አርሶ አደር በቀጥታ አዲስ አበባ አምጥቶ የሚሸጥበትን እድል እስከፈጠርን ድረስ ሸዋ ሮቢት ያለው አርሶ አደር ተጠቃሚ ይሆናል:: አዲስ አበባ ያለው ሕዝብም እንዲሁ ተጠቃሚ ይሆናል::

ነገር ግን ሸዋ ሮቢት ያለው አርሶ አደር የደብረ ሲና ደላላ ከተቀበለው ፤ የደብረሲናውን ደግሞ የደብረ ብርሃን ደላላ ከተቀበለው በዚህ ላይ የሚኖረው የምርት ዋጋ ጭማሪ እዚህ ላይ ባለው የኅብረተሰብ ክፍል ትከሻ ላይ ይወድቃል::

ይህንን ሰንሰለት ለማሳጠር አምራቹን በቀጥታ ለተጠቃሚው የሚደርስበት ሥርዓት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል አምራቹ ለማኅበራቱ በቀጥታ አምጥቶ የሚሸጥበትን እድል ለመፍጠር የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ::

ከዚህ በተጨማሪ ለአንዳንዶቹ ደግሞ በተደራጀ መልኩ የሚያመጡትን ምርት በቀጥታ የሚያከማቹበት እድል ተፈጥሯል ፤ የገበያ ማዕከላት በማስፋፋት በርካታ ሥራዎችን ሥንሰራ ቆይተናል:: በዚህ በኩል ባለፉት ጊዜያት ብዙ ነገሮችን አሳክተናል።

አሁን የተፈጠረው ጉድለት ግን አስቀድሜ በጠቀስኩት ምክንያት በመሆኑ የደላላን ጣልቃ ገብነት መበጣጠስ ይጠይቃል። ህገወጥ ኬላዎችን ማጥፋት ይጠይቃል። አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት በነጻ የሚሸጥበት እድል ሊፈጠር ይገባል። ይህንን ለማድረግ በአንድ ከተማ ብቻ የሚታጠር አይደለም። ከክልሎች ጋር መቀናጀት የግድ ነው።

በከተማችንም ያሉትን ማኅበራት በማጠናከር በገንዘብ አቅም ውስንነት ምክንያት ምርት ለመግዛት ችግር እንዳይገጥማቸው አድርገናል። ነገር ግን ያላቸው የገንዘብ አቅም ብቻ መፍትሔ ሊሆን አልቻለም። በተለያዩ አካባቢዎች የገበያ ልውውጡን የሚያውኩ ነገሮች አሉ:: አምራቹ ወደገበያ እንዳይመጣ ያደርጋሉ:: ይህ ደግሞ ዩንየኖችን በነጻነት ተንቀሳቅሰው መግዛት እንዳይችሉ እክል ይፈጥርባቸዋል::

እንደዚህ አይነት ተግባር ላይ በስፋት የሚገኙት ደግሞ ደላላዎች እና በመንግሥት አሻጥር የሚሠሩ የራሳቸው ተልዕኮ ያላቸው ኃይሎች ናቸው:: ስለዚህ ገንዘብ መኖሩ ብቻ በቂ ስላልሆነ በሀገሪቱ የሚካሄዱ ግብይቶችን ለማሳለጥ በየአካባቢው ግብይት ላይ እክል ሚፈጥሩ አካላትን ሕዝብ እና መንግሥት ተባብረው ማረም ይኖርባቸዋል::

ገበያውን እየዘወረው ያለው ደላላው ነው የሚለው የአዲስ አበባን ብቻ ነጥሎ አይሠራም። እንደዚህ አይነት ድምዳሜ ላይ አልደረስንም። እኔ እስከማውቀው ድረስ አዲስ አበባ ላይ ደላላ አለ። በዚህ ውስጥ ብዙ ነገሮችን እንደሚያበላሽ ይታወቃል። በሁሉም መስኮች ላይ የደላላ ጣልቃ ገብነት አለ። ግልጽ ነው። ከግብርና ምርት ጋር ተያይዞ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ለአብነት ማኅበራት ደላላ ጣልቃ አይገባባቸውም። ክልል ማኅበራት ላይ ምርት ማምጣት አለባቸው። የክልል ማኅበራት ግን በቂ ምርት አልያዙም። ምርቱንም ይዘው ለመሸጥ እና እኛ ጋር ትስስር ለመፍጠር ባለፉት ጊዜያት የተወሰኑ እንቅፋቶች ገጥመው ነበር። አሁን ያ ችግር እንዲፈታ ነው እየተነጋገርን ያለነው። ይሄን ደላላው ፈጥሮታል ማለት አይቻልም።

ማኅበራት የሚያመጡትን ምርት ሲያከፋፍሉ ወይም ሲሸጡ ደላላው ሊገባበት አይችልም። በንግዱ ውስጥ ግን ደላላው አይኖርም ማለት አይደለም። በከፍተኛ ሁኔታ አለ። ይሄ ችግር በአዲስ አበባ ብቻ የሚታጠር አይደለም። በክልሎችም ምርት እያከማቹ ለረጅም ጊዜ ምርት የሚይዙበት እንቅስቃሴዎች የደላላው እጅ የለበትም እያልኩ አይደለም። የደላላው እጅ እንዳለበት አሻሚ አይደለም። በአጠቃላይ ግን በአዲስ አበባ ላይ ያለው እንቅስቃሴ ደላላው በበላይነት እየዘወረው ነው፤ አሁን ላይ ቁጥጥር እያደረግን ስለሆነ የምንደርስበት ይሆናል። ምን ያህል ነው ስፋቱ የሚለውን እናውቃለን ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን:- በተለያዩ ጊዜ የቤት ኪራይን በተመለከተ በአስተዳደሩ መመሪያዎች ይወርዳሉ። በትክክል ወደ ኅብረተሰቡ ከማድረስ አኳያ ምን ሥራዎች ተከናውነዋል? ተመን አበጅቶ ወይም በሌላ መንገድ ከመቆጣጠር አንጻር ምንድን ነው በተጨባጭ እየተሠራ ያለው?**

**አቶ ጃንጥራር:-** በመሠረታዊነት የቤት ኪራይ በዚህ አከራይ ተብሎ ተመን መተመን ተገቢ ነው ብለን አናስብም:: ነጻ ገበያን የምታራምድ ሀገር ላይ በሁሉም ነገር ላይ መንግሥት ዋጋ እየተመነ መቀጠል አይችልም::

ነገር ግን አንድ ሰው ቤት ሲከራይ ከአከራዩ ጋር የኮንትራት ውል ሲዋዋል አከራዩ በፈለገው ጊዜ ሁኔታዎችን እየጠበቀ የቤት ኪራይ ሊጨምር አይገባም ወይም ኅብረተሰቡ ያለበትን የኑሮ ጫና ግምት ውስጥ በማስገባት መጀመሪያ ተከራይ ቤቱን ሲከራይ ከተጠየቀው ገንዘብ በላይ እንዳይጨመር ነው የእኛ አቋም:: ባለፈው ዓመት ከተማ አስተዳደሩ አንድ ደንብ አውጥቷል:: ያ ደንብ በየስድስት ወሩ እየቀጠለ ነው ያለው:: አሁንም የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በቤት ኪራይ ላይ ዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር ወስኗል::

መንግሥት ይህን የመሰለ ውሳኔ ወስኖ እያለ አከራይ ቢጨምር ተከራይ ለምን ብሎ መጠየቅ አለበት:: መክፈልም የለበትም:: ነገር ግን መንግሥትን ተወው አንተና እኔ እንስማማ የሚል ተከራይ ካለ ችግሩ የተከራዩ ነው::

ግልጽ መሆን ያለበት ነገር ቢኖር ከቤት ኪራይ ተመን ጋር ተያይዞ መንግስት በካሬ ሜትር ለክቶ የቤት ኪራይን ዋጋ አልወሰነም ::

በከተማ አስተዳደሩ የቤት ኪራይን ዋጋ መናርን ለመቀነስ አከራዮች ባከራዩበት ዋጋ እንዲጸኑ ማድረጉ ችግሩን በዘላቂነት አይፈታውም:: ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት መንግሥት በግላቸው ለሚሠሩ ሰዎች በግላቸው እንዲገነቡ መፍቀድ ፤ መንግስትም ያለውን አቅም ተጠቅሞ ተጨማሪ ቤቶችን መገንባት ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን ፡- የኑሮ ውድነቱን ከማረጋጋት አንጻር ሕዝብ ምን ይጠብቅ?**

**አቶ ጃንጥራር ፡-** በነገራችን ላይ መንግሥት ቁጥር አንድ አጀንዳ አድርጎ በትኩረት እየሠራ ያለው የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ነው:: እንደአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ይህንን ችግር እንዴት እንፍታ ብለን ቀዳሚ አጀንዳ አድርገን እየሰራን ነው ያለነው::

እንደ አዲስ አበባ ከተማ ገበያውን ምቹ ማድረግ አንዱ ሥራችን ነው:: አቅርቦት እንዲኖር መሥራት ሁለተኛው ሥራችን ነው:: ሕገወጥነትን መቆጣጠር ሌላቸው ተግባራችን ነው:: የግብይት ሥርዓቱ እንዲፋጠን የሰንበት ገበያ ብቻ አይደለም ፤ተጨማሪ የገበያ ማዕከሎችን እየገነባን ነው:: ከዚህ አንጻር በመንቀሳቀስ ከተማ አስተዳደሩ የተሻለ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር እየሠራ ነው ::

**አዲስ ዘመን:- ለኑሮ ውድነቱ መባባስ በተለያዩ አካባቢዎች ኬላዎች መጣላቸው ፣ ሕገወጦች መበራከታቸውን መሆኑን ነግረውናል:: ከዚህ አንጻር የከተማ አስተዳደሩ ብሎም መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማስተካከል በእርግጥስ ኃላፊነቱን ተወጥቷል ማለት ያስችላል?**

**አቶ ጃንጥራር ፡-** እኔ የማወራው ስለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው:: ችግሩን ከመፍታት አይን ካየነው ችግሩ ብዙ ስለሆነ ችግሩን አልፈታነውም:: መንግሥት ግን እንደ መንግሥት ከመንግሥት የሚጠበቅበትን ሥራ ለመሥራት ችግር የለበትም ::

**አዲስ ዘመን ፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ ጃንጥራር ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

## ጎሜ

# የሕገወጥነት ወሰን ዲካ የት ድረስ ነው?

ገርማ መንግሥቱ

ዛሬ የሕገወጥነትን ትርጉም ለመናገር መሞከር ከቂልነት ባለፈ መሳቂያ መሆን ነው። ምናልባት ለፍትህ ሂደት ሲባል በፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ይብራራ ይሆን እንደሆን እንጂ፤ በሌሎች ቦታዎች ላይ ሕገወጥነትን ለመበየን መነሳት ኋላ ቀርነት ነው የሚሆነው። “ለምን?” ከተባለ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ገብቶ እያተራመሰን ያለን ጉዳይ የመዝገበ ቃላት ብያኔን ለመስጠት መሞከር የአይኑን በጆሮ ስለሚሆን ብቻ ነው። ቀጥለን በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ እንመለከተዋለን።

ድሮ ድሮ ሕገወጥነት (Illegal ወይም Unlawful) የሚታሰብ ተግባር አልነበረም ነው የሚባለው። “እንዴት?” ቢሉ የመጀመሪያው የፈሪሀ እግዚአብሔር መኖር ሲሆን፤ ቀጣዩ ይሉኝታ (በተራዛሚው ባህል) ነው አሉ ምክንያቱ። በቃ፣ እነዚህ ሁለቱን ጥሶ መሄድ የሚታሰብ አይሆንም። የሚያስብ እንኳን ቢኖር ሕገወጥነቱን ይዞ አገር ጥሎ መሄድ ነው መፃኢ ዕድሉ። ከእነ አገላለፁ “የእገሌ ልጅ . . .” ከመባል ሰውረኝ ነበር የሚባለው። ዛሬ ዛሬ ነገሩ ሁሉ ‹‹በኮታ ገብቶ›› “ኧረ በሕግ” ሲባል፣ “ስትፈልጉ ወይዘሮ በሉኝ” እንዳለው ጥቅመኛ ነውና ምን ማድረግ እንደሚቻል ለጊዜው ግልፅ አይደለም።

ባለፈው አመት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥን ጠቅሶ ለንባብ የበቃ ዜና “በሕገወጥ የውጭ አገራት ገንዘብ ምንዛሬ ላይ የተሰማሩ አካላትን ለጠቆመ እስከ 25 ሺህ ብር ወረታ እከፍላለሁ” (ባንኩ “391 ሕገወጥ ገንዘብ አዘዋዋሪዎች በሕግ ጥላ ስር ናቸው” ያለውንም ከዚሁ ጋር አዳምሮ ማየት ይቻላል) በማለት ያስነበበንም የሚያመለክተው ይህንኑ በሕገወጥነት የመዝረፍ ተግባርን ነውና ሕገወጥነት በየዘርፉ ሥራ ላይ ሲውል ይታያል። ወደ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቢኬድም ሕገወጥነትን በሕጋዊነት የመከላከሉ ተግባር ፋታ ሲያሳጣ ነው የሚገኘው። ይህንን ስንል ስለእውነት በእውነት እየተሠራ ነው በሚል ከብረት የጠነከረ እምነት ነው።

በዚሁ አመት፣ “ከ33 ሺሕ በላይ ሕገወጥ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ ተወሰደ” የሚል አስደንጋጭና አስደማሚ ዜናምን እኮ ሰምተናል። የሚገርመው ይህንን ያህል ቁጥር ያለው ወንበዴ፣ የጅቡቲን ሕዝብ ለማከል ጥቂት ፈሪ የሆነ ዘራፊ ባለበት አገር እንዴት ሆኖ ነው ሸማች ሥርዓት ያለው ገበያ ተጠቃሚ የሚሆነው።

በተመሳሳይ አመት (ጥር 19፣ 2014 (ኤፍቢሲ)) “በደቡብ ክልል ሕገወጥ ተግባር ፈጽመዋል የተባሉ ከ29ሺህ በላይ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ መውሰዱን የክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ አስታወቀ” የሚል ዜና መስማታችንም የሚዘነጋ አይደለም። “በጎንደር ከተማ 14 ሕገወጥ ነጋዴዎች እስከ 11 ዓመት በሚደርስ እስራት ተቀጡ” (ሐምሌ 27/2011 አ.ም)። “በቀን የገቢ ግመታ ሥራው የተለዩ ከ43ሺህ በላይ ሕገወጥ ነጋዴዎችን ወደ ሕጋዊ ግብር አከፋፈል ሥርዓት ማስገባቱን የኦሮሚያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አስታወቀ።” (ጁላይ 14, 2017) ወዘተርፈ . . .። እነዚህ ሁሉ ባሉበት ነገሮች በኑሮ መወደድ ብቻ መመለሳቸው የሚገርም ሲሆን፤ ወደ ሌላና የራሳቸውን መንግሥት እስከ ማቋቋም አለመሄዳቸው ሊያስመሰግናቸው ይገባል። ጎበዝ፣ በሕገመንግሥቱ መሰረት እንሂድ ካሉ እኮ እነዚህ የሕገወጡ ቡድን አባላት ተሰባስበው ክልል መሆን እንፈልጋለን (የሕገወጥ ነጋዴዎች ክልል፤ የሕገወጥ ገንዘብ አዘዋዋሪዎች ክልል፤ የሕገወጥ ደላላዎች ክልል . . .፤ ኧረ እንዳይሰሙን፣ ደሞ እውነት መስሏቸው . . .)፣ ይፈቀድልን የማለት መብት የላቸውም ማለት እንደማይቻል ስንቶቻችን፣ በሕገወጥ ንግድ የቆሰልንና የቆሳሰልን እናውቅ ይሆን?።

ሕገወጥነት በጨለማም ይታጀባልና “ሕገወጥ ነጋዴዎች የራሳቸውን ሀብት ያለአግባብ ለማካበት ጨለማን ተገን አድርገው መንቀሳቀስን መርጠዋል” የሚለውን ስናስታውስ “ሆሆ...” ማለታችን የግድ ይሆናልና ሕገወጥነት ሰዓትና ሁኔታ የማይገድበው የ24 ሰዓት ሥራ ነው ማለት ይሆናል። እነዚህን ሕገወጦች ከሌሎቹ ለየት የሚያደርጋቸው ጭለማን (“ሌቦች” ማለት ይቻላል) ተገን ማድረጋቸው ነውና በጭለማም መጠንቀቅ እንዳለብን ሁላችንም ለሁላችንም ማሰብና ማሳሰብ ይገባናል ማለት ነውና እነሆ ማሳሰቢያው።

“የከተማችን ነዋሪዎች ይህን ማስጠንቀቂያ ተላልፎ የሚገኙ ሕገወጥ ነጋዴዎች በአካባቢው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም በቢሮው ነፃ ስልክ ቁጥር .... ደውላችሁ አሳውቁኝ”፤ “ወቅቱ ከትርፋችን በላይ አገራችንና ሕዝባችን ስለማትረፍ የምናስብበት መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም” ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ለንግዱ ማህበረሰብ (ነጋዴው) ማሳሰቢያ መስጠቱ የሚታወስ ሲሆን፤ ቢሮው “አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ወቅታዊ አገራዊ ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ በአቋራጭ ለመክበር እና ሆን ብሎ ሕገወጥ የዋጋ ጭምሪ እና ኢኮኖሚያዊ አሻጥር ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ላይ መሆናቸውን” (ነሐሴ 19 ቀን 2013 አ.ም) ከሚለው ውስጥ “ወቅታዊ አገራዊ ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ . . .” የሚለውን ነቅሎ በማውጣት ግርግር ምን ያህል ለሌባ መልካም አጋጣሚ ስለመሆኑ መረጃም፣ ማስረጃም ነው።

መቼም ሕገወጥ ንግድንና ሕገወጥ ነጋዴን ለማጥፋት ያልተደረገ ጥረት የለም፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቃላትና ሐረጋት አለመኖራቸው፣ ያልተሰደሩ ሥርዓተ ነጥቦች ያልነበሩ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ከላይ የጠቀስናቸውና ቀጥለን የምናያቸው ለዚህ፣ እየተነጋገርንበት ስላለው ጉዳይ ተገቢና ተጨባጭ ማሳያዎች ናቸው። እንቀጥል፡-

በየመንደሩ በመዞር ሚዛን ይዘው ግዢ የሚፈጽሙት ሁሉ ሕገወጥ ነጋዴዎች ከሕገወጥ ነጋዴዎቹ ተርታ እንደሚሰለፉ እናውቅ ይሆን? አናውቅም። ምክንያት ብናውቅ ኖሮ እንደ ሕጋዊ ተግባር ቆጥረን አናስተናግዳቸውም ነበራ። ለነገሩ ፖሊስ እያየ ዝምታን ያጎናፀፋቸውን እኛ ምን ብለን ነው “ኧረ በሕግ!!!” የምንለው? ብንልስ ሕገወጦቹ መልሰው “የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ” አይሉንም ማለት ይቻላል? ይላሉ። እነሱ ምን የማያፍሩትና የሚፈሩት አካል አለ።

መንገድ መዝጋት ሲባል ምን ማለት ይሆን? ይህንን በተመለከተ እስካሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰጠ ብያኔ የለም፤ በጦርነት ወቅት ካልሆነ በስተቀር። በመሆኑም ይመስላል፣ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ፣ ለሌቦች፣ ዘራፊዎችና ዘጊዎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረው። የሚገርመው የእነሱ ምቹ ሁኔታን መጠቀም አይደለም። የሚገርመው እነሱን ሃይ ባይ መጥፋቱ እንጂ።

መረጃና ማስረጃችንን እያጣቀስን እንቀጥል።

ሰሞኑን በዚሁ ጋዜጣ (መጋቢት 3 ቀን 2015 አ.ም) ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ “ምርትን በመያዝ ለሌላ የፖለቲካ ቀውስ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚደረጉ ሙከራዎች ላይ መንግሥት ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚያደርግ፤ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱንና የጤፍ ዋጋ ከተጋነነው ጭማሪ ዝቅ እንዲል እንደሚሠራ” መግለፃቸውን ይዘን፤ “ከአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር በሕገወጥ መንገድ ዋጋን በማናር ሕዝብን ለማነሳሳት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም”፤ “በመንገድ ንግድ ላይ ያሉና ድለላ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት እየገዙ የማከማቸትና [ምርት] ወደ ግብይት እንዳይገባ የማድረግ ሁኔታዎች አጋጥመዋል”፤ “በወፍጮ ቤቶች ብዙ ምርቶችን በመያዝና ወደ ግብይት የሚገባውን ውስን በማድረግ ዋጋ ሲወደድ ለመሸጥ የሚደረጉ ፍላጎቶችና ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች” አሉ፤ “ኬላዎችን በመዝጋት ምርት በነፃ እንዳይንቀሳቀስ እና ግብይቱ እንዳይሳለጥ በማድረግ፤ በዚህም በመዲናዋ የምርት እጥረት እንዲኖር” የሚካሄደውን ከንቱ ድካም አይተን ታዝበናል። “ችግሩን ለመፍታት ከፌዴራል መንግሥትና ከክልሎች ጋር በመነጋገር በሕገወጥ መንገድ የተዘጉ ኬላዎች እየተከፈቱና ምርት የሚገባበት ሁኔታ እየተፈጠረ” ይገኛል ማለታቸውን የሰማና ፖለቲካም ለሕገወጥነት ተግባር ሲያገለግል የተመለከተ “ጎበዝ፣ ምንድን ነው መላው??” ቢል ምን ይገርማል?

> **ጉዳያችን ሕገወጥነትን እያገላበጡ ማሳየት ሆነና ነው እንጂ ምድራችን ሕጋዊያንን አላፈራችም ማለት አይደለም። ከሚገባው በላይ አፍርታለች። በማፍራቷም ነው አገራችን እዚህ የደረሰችው፤ የእነሱ ቁጥር በመብዛቱም ነው ወደ ፊትም የምትቀጥለው**

“ባለፈው ረቡዕ ምሽት ሀዋሳ ላይ ፖሊሶችና የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ሲታኮሱ አደሩ፡፡” (ማርች 17፣ 2012 (www.worancha.com)) የሚል ዜና ሰምተን “እንዴ ይሄ ነገር ወዴት እያመራ ነው? ሕገወጡ ቡድን ጭራሽ መሣሪያም ታጥቋል?” እንዳላልን ሁሉ፤ ዛሬ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ጤፍ እንዳይገባ እየተደረገ መሆኑን ስንሰማ የሕገወጦች እድገት አዝጋሚ አለመሆኑን ከመረዳት ውጪ ሌላ ምንም ማለት አይቻልም፤ ለጊዜውም ቢሆን። ግን ግን፣ “የሕግ የበላይነት ይከበር!!!” ብሎ መፈክር ማሰማት ይቻላል። ሕገወጡን በሕግ ዱላ ማለት ግን ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አይደደለም። ኧረ ለመሆኑ ሕገወጡ ሁሉ እየተነሳ በሕግ አምላክ እንዳይለን።

የገቢዎች ሚኒስቴር በይፋዊ ድረገፁ (http://www.mor.gov.et) ላይ 42 አንቱ የተባሉ ድርጅቶችን ስም ዝርዝር በሰንጠረዥ በመግለፅ “ሀሰተኛ ደረሰኝ በማሰራጨት አገራቸውን ሲሰርቁ የነበሩ ድርጅቶች ተለዩ” በሚል ርእስ አስፍሮት እንደተነበበው ከሆነ ሕገወጥነት በእድገቱም ሆነ ተግባራቱ በከፍተኛ ደረጃ እየተሻሻለ መሄዱንና፤ ከግለሰብ(ቦች)ም አልፎ ወደ ድርጅት(ቶች) ደረጃ እንዳደገ፤ በተግባሩም ከሀብትና ንብረት መዝረፍ ደረጃ አልፎ አገር ወደ መስረቅ ደረጃ እንደተሸጋገረ ለማየት ይቻላል። ምናባቱ፣ ከሆነ አይቀር እንዲህ ነው።

“በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በትናንትናው ዕለት ይፋ የተደረገው ጥናት “መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፣ በተለይም በወጣቶችና ሴቶች ላይ እያስከተሉት ያለው አሉታዊ ተጽእኖ” በሚል ርዕስ የተካሄደ ሲሆን ከ3ሺህ 600 በላይ ሕገወጥ የወሲብ ድርጊት የሚፈፀምባቸው ቤቶች እንዳሉ” (ዛሬ ስንት ደርሰው ይሆን?) ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ለማወቅ የተቻለውም “አዲስ አበባ በሕገወጥ ልማዶችና የወሲብ ድርጊቶች እየተናጠች ነው” በሚል ርእስ ለንባብ በበቃው ዜና (እሁድ፣ ጃንዋሪ 13፣ 2013) አማካኝነት ነው። “ወይ አዲስ አበባ . . .” እንዳትሉ፤ ገና ነው።

ይህ ብቻም አይደለም፣ “በከተማዋ የቀንና የሌሊት ጭፈራ ቤቶች፣ የራቁት ዳንስ ቤቶች፣ የሺሻና የጫት ቤቶች፣ የቁማር ቤትና ሕገወጥ የቪዲዮ ቤቶች ቁጥር በከፍተኛ መጠን” እያደገ ይገኛል። ጥናቱ እንደደረሰበት ከሆነ “አሥሩም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ የፖሊስ መምሪያዎች የተሰበሰበ መረጃ እንዳመለከተው፣ 3ሺህ 691 ቤቶች ለእነዚሁ ተግባራት ተከፍተው በከተማዋ ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ቤቶች መበራከትና በስፋት መሰራጨት ሳቢያም በርካታ ወጣቶች ለወንጀል ተግባራት፣ ለአደገኛ እፆች ሱሰኝነት፣ ለዝርፊያ፣ ለስደት፣ ለጐዳና ተዳዳሪነት፣ ለኤችአይቪና ተያያዥ በሽታዎች፤ እንዲሁም፣ ላልተፈለገ እርግዝና ተዳርገዋል፡፡” (ሌሎቹን፣ ጥናቱ የደረሰባቸውን ገመናችንን እዚህ የመዘርዘር ድፍረቱ ስላልተገኘ አንባቢ በራሱ ሊደርስበት መብት አለው) ጎበዝ፣ መላው ምንድን ነው ታዲያ?

ኢትዮጵያ ውስጥ የሕገወጥነት ችግር የለም። ከጥፍራችን እስከ ፀጉራችን ድረስ ተዘፍቀንበታል። ይህ ደግሞ እስከ “የመንግሥት ሌቦች” ድረስ የዘለቀ ስለመሆኑ ያልሰማን ካለን ጥቂቶች መሆን አለብንና ለእኛ ሕገወጥነት ‹‹ብርቅ›› አይደለም። ችግሩ ብርቅ ባለመሆኑ ጭራሹኑ ጠራርጎን ወደ መውሰዱ መቃረቡ ነው።

እንደ በኢትዮጵያ የዓለምአቀፉ የፍልሰት ድርጅት (አይኦኤም) አቤቱታ (ኢዜአ፤ ታኅሣሥ 8/2012) “ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችና ደላሎች ሕገወጥ ስደትን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል”።

እንደው ለነገሩ ምን ምንድን ናቸው ሕገወጦቹ? ሕገወጥ የሆኑትን ከመፈለግ ያልሆኑትን መዘርዘር ቢቀልም፣ የሕገወጥነት ወሰን ዲካው የት ድረስ እንደሆነ ለማሳየት የሚከተሉትን መጠቃቀስ ይቻላል።

ሕገወጥ የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ሕገወጥ መድኃኒቶች፣ ሕገወጥ ቤቶች፣ ሕገወጥ የትምህርት ማስረጃዎች፣ ሕገወጥ የውጭ አገር የሥራ ስምሪት፣ “ሕገወጥ የእንቁላል ዝውውር” (አሜሪካ “ሕገወጥ የእንቁላል ዝውውር” አሳስቦኛል አለች። ጃን. 24, 2023)፣ ሕገወጥ ሰፋሪ፣ ሕገወጥ የጦር መሳሪያ (ሕገወጥ ቱርክ ሰራሽ ሽጉጦችን ጨምሮ)፣ ሕገወጥ የገንዘብ መላኪያ፣ ሕገወጥ ስደት፣ ሕገወጥ አደን፣ ሕገወጥ እርምጃ፣ ሕገወጥ የመሬት ወረራ (“ወረራ” ብሎ ሕገወጥ ባይሆን ነው የሚገርመው)፣ ሕገወጥ ግብይት፣ ሕገወጥ እቃዎች (“የሕገ-ወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝና የወሮታ አከፋፈል”ን ያነቧል)፣

እርግጥ ነው፣ ጉዳያችን ሕገወጥነትን እያገላበጡ ማሳየት ሆነና ነው እንጂ ምድራችን ሕጋዊያንን አላፈራችም ማለት አይደለም። ከሚገባው በላይ አፍርታለች። በማፍራቷም ነው አገራችን እዚህ የደረሰችው፤ የእነሱ ቁጥር በመብዛቱም ነው ወደ ፊትም የምትቀጥለው።

በየዘርፉ፣ በየአካባቢው፣ በየክፍለ ዓለማቱ ሕጋዊያን ሞልተዋል። በየሄድንበት፣ በየተሰማራንበት፣ በምንሸምትበት ወዘተርፈ ሁሉ ኢሕጋዊነትን አምርረው የሚጠየፉ ሕጋዊያን አሉ። እንደውም አንድ አባባል አለ። ይህች ዓለም እስካሁን ያለችው በገጠሩ ሕዝብ ቅንነትና ሕጋዊነት ነው የሚል። እውነት ነው። ቅንነትና ሕጋዊነትን ጨምሮ፣ ግልፅነት፣ የዋህነት፣ ጀግንነት . . . እዛ አሉ። “አብሮ እሚበላ፣ አብሮ እሚጠጣ . . .” የሚለው ሁሉ እንደ ወረደ የሚገኘው እዛ እንጂ እዚህ ኢሕጋዊያን ጫካ ውስጥ አይደለም። አስተዋይነትን፣ ሰብአዊነትን፣ ታታሪነትን፣ ጥብቅ አማኝነትን፣ ባለማተብነትን፣ በሕግ የበላይነት ማመንን፣ ሩህሩህነትን፣ እንግዳ ተቀባይነትን፣ ከእግዚአብሔር ሰላምታ ጀምሮ ሰው አክባሪነትን፣ አድማጭነትን፣ አስታራቂነትን . . . ወዘተርፈ ሁሉ እዛ ይገኛሉ።

በመሆኑም፣ ኢሕጋዊያንን ወደ ሕጋዊነት ለማምጣት አንዱና ዋናው መሳሪያ (እሴት) ይሄው የገጠሩ ቱባ ማንነት ነው ስንል፣ በእነዚህና ሌሎችም በቂ ምክንያቶች መሆኑን ስንገልፅ “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!” (ይህንን አባባል ለመጀመሪያ ጊዜ መደበኛ በሆነ መልኩ ተጠቅመው ያገኘሁት ጀኔራል ዐቢይ አበበን ሲሆን፣ እሱም በ“አውቀን እንታረም” ድንቅ መጽሐፋቸው ውስጥ ነው) በማለት ነው። በ“ታሪክን የኋሊት” እንደግመዋለን፣ “ኢሕጋዊነት ይውደም!!!” “ፀረ-ኢሕጋዊነት ትግል ይፋፋም!!!”፤ “ሕጋዊነት ይለምልም!!!” “ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!”

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## «ዩቲዩብ» ለፊልም ኢንዱስትሪው ስጋት ወይስ ተስፋ?

ቦጋስ አበበ




በኢትዮጵያ ፊልም መሠራት ከጀመረ ረጅም ዓመታት ቢያስቆጥርም በፖሊሲና በተቋም የተደገፈ ባለመሆኑ ራሱን ችሎ የሚቆም ዘርፍ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። በተለምዶ ግን የኢትዮጵያ ፊልም ኢንዱስትሪ ተብሎ ይጠራል።

በ1990ዎቹ ማንሰራራት የጀመረው የኢትዮጵያ ሲኒማ ዛሬም ዳዴ እያለ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ። ለዚህ አንድ ማሳያ ተደርጎ የሚቀርበው ደግሞ የኢትዮጵያ ፊልም በወጣቶች ተደራጅቶ፤ ለወጣቶች የእንጀራ ገመድ ከመሆን በዘለለ በኢንዱስትሪው ላይ የሚፈሰው መዋዕለ ንዋይ እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ ነው።

እስከ ቅርብ ጊዜ ለዕይታ የበቁ ፊልሞች በአማካይ አንድ ፊልም ተሠርቶ ለእይታ እስኪበቃ ድረስ ስድስት መቶ ሺህ ብር ገደማ እንደሚፈጅ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በእርግጥ አልፎ አልፎ እስከ 4 ሚሊዮን ብር የወጣባቸው ፊልሞችም አይታጡም። ነገር ግን ከአማካይ ወጪው አልፎ መበጀት የቻለ ፕሮዲውሰር፣ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ፊልሞችንም የጻፈ ደራሲ፤ ገና የፊልም ኢንዱስትሪው ማፍራት አልቻለም። ያም ሆኖ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወዲህ ኢንዱስትሪው ከመቀዛቀዙ አስቀድሞ በዓመት በትንሹ ሰማንያ በትልቁ ደግሞ መቶ ፊልሞች ተሠርተው ለእይታ እንደሚበቁ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከወረርሽኙ መከሰት በኋላ እየተቀዛቀዘ የመጣው የፊልም ኢንዱስትሪ ለማንሰራራት ሲጣጣር ቢታይም በበርካታ ምክንያቶች ብዙ መራመድ አልቻለም። ለዚህ አንዱ ምክንያት ደግሞ ከጥራትና ከይዘት ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ሚዛን ይደፋሉ።

የኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ ራሳቸውን በሙያው ብቁ ለማድረግ በሚጥሩ ወጣት ባለሙያዎች እየተገነባ መምጣቱ አንድ ጠንካራ ጎን መሆኑን አንዳንድ ባለሙያዎች አስተያየት ሲሰጡ ይሰማል። ይህም ከጥራት ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ችግሮች አንድ መፍትሄ ሊፈጥር እንደሚችል ተስፋ ተደርጎበታል። ያም ሆኖ ይህን ተስፋ የሚያደበዝዙ ስጋቶችም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢንዱስትሪው እንቅፋቶች ሆነው መታየት ጀምረዋል።

የፊልም ኢንዱስትሪው ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ከወረርሽኙ በኋላ የፊልም ዘርፉ የሥራ ውጤቶቹን ለማቅረብ ከሲኒማ ወደ ዩቲዩብ እና የኢንተርኔት አማራጭ መንገዶች ፊቱን አዙሯል። ይህም ለኢንዱስትሪው የራሱ የሆነ በጎ ነገር ቢኖረውም አሉታዊ ተፅእኖው የጎላ እየሆነ ይገኛል።

ባለፉት ሦስት አስርት አመታት ኢንዱስትሪው ባደረገው ጉዞ በ1990ዎቹ ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ዓይነተኛ መነቃቃትአሳይቶ እንደነበር ባለሙያዎቹ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

የኢትዮጵያ ሲኒማ ለዓለም አቀፍ እይታና ተደራሽነት ለመብቃት ረዥም መንገድ እንደሚቀረው ብዙዎች ቢስማሙበትም ከቅርብ አመታት ወዲህ ያለው ጉዞ ግን የኮቪድ ወረርሽኝና ሌሎች ገፊ ምክንያቶች አንፃር በቁልቁለት ጎዳና ላይ እንደሚገኝ ለማንም ግልፅ ነው።

በፊልም ኢንዱስትሪው የተሰማሩ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት፣ ከወረርሽኙ በኋላ የፊልም ዘርፉ የሥራ ውጤቶቹን ለማቅረብ ከሲኒማ ወደ ዩቲዩብ እና የኢንተርኔት አማራጮችን መንገዶች በስፋት እየመረጡ ነው። ይህም የዲጂታል ሚድያው አትራፊና ገንዘብ ማጋበስ የሚቻልበት መንገድ በመሆኑ በፊልም ሠሪዎች ተመራጭ መሆኑ ነው። እነዚህ አዲስ ለውጦች የፊልም ኢንዱስትሪው ለረዥም ጊዜ ሲጠቀምባቸው የነበሩትን የሲኒማ እንዲሁም የሲዲና ዲቪዲ መንገዶችን ከጨዋታ ውጪ እያደረገ ነው።

የፊልም ኢንዱስትሪው ወደ ቴሌቪዥንና በተለይ ደግሞ ዩቲዩብ ፊቱን ማዞሩ በዘርፉ የሚመረቱት የፊልም ሥራዎች ጥራት ላይ አደጋ እየሆነና ሙያዊ ብቃትም ኪሳራ ውስጥ እንዲገባ ትልቅ ምክንያት መሆኑ በግልፅ እየታየ ይገኛል።

ከወረርሽኙ በፊት አንድ በፊልም ኢንዱስትሪው የተሰማራ የፊልም ባለሙያ ፊልም ሠርቶ ጨርሶ ወደተለያዩ ሲኒማ ቤቶች ከማሰራጨቱ በፊት በአንድ ሲኒማ ቤት በማስመረቅ ለእይታ ያበቃል። ከዚያም በኋላ ወደተለያዩ ሲኒማ ቤቶች አሰራጭቶ ገቢም ያገኝበታል፤ በፊልሙ ድርሻ ያላቸው ሰዎችም የሚገባቸውን ክፍያ ያገኛሉ። ከዚያም የፊልሙ ባለቤት በተለያዩ ሲኒማ ቤቶች ፊልሙን ለእይታ ካበቃ በኋላ ከፈለገ በራሱ ዩቲዩብ ላይ ይጭነዋል፣ ካልሆነም ለቻናል ባለቤቶች (ዩቲዩበሮች) ይሸጥላቸዋል። ይህንን በማድረግ በፊልሙ ለተሳተፉ አካላት የሚገባቸውን ክፍያ እንዲከፍል ከማስቻል ባሻገር አነሰም በዛም ለሙያው የሚመጥንና ጥራት ያለው ሥራ እንዲሠራ አድርጎት ቆይቷል።

ሆኖም ከኮቪድ በኋላ ሲኒማ ቤቶች መዘጋታቸውን ተከትሎ የፊልም ሥራው ልምድ ለዩቲዩብ የሚሆኑ ፊልሞችን ወደ ማምረት አዘንብሏል።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት፣ በተለያዩ በዩቲዩብ ቻናሎች የሚጫኑ ፊልሞች በአነስተኛና ወጪ ቆጣቢ ፕሮዳክሽን እስከ በሁለት እና ሦስት ቀናት ብቻ ባለ ጊዜ የሚሠሩበት አጋጣሚ እየሰፋ ሄዶ የጥራት ጉዳይ ውሃ እየበላው ይገኛል።

በዩቲዩብ ቻናሎቻቸው ላይ ፊልሞችን ለመጫን የሚገዙት የቻናል ባለቤቶች ለፊልሞች የሚያቀርቡት ክፍያ በፍጹም ፊልሞችንም ሆነ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎቹን የሚመጥን እንዳልሆነ ባለሙያዎቹ ያስረዳሉ።

ከዚህ ባሻገር ፊልሞች የወረደ የጥበብ ይዘት ያላቸውና ቶሎ እይታ እንዲኖራቸው ብቻ እየተሠሩ፣ እንዲሁም ሰዎች በቀላሉ እንዲቀበሏቸው ብዙ ቁምነገር ሳያዝሉ እንዲመረቱ በር ከፍቷል። ይህም የሙያው እውቀትና ችሎታ የሌላቸው በርካቶች በድፍረት እንዲሳተፉበት እያደረገ ይገኛል።

የዩቲዩብ ፊልም ፊልሞችን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ሂደቶችን ስለማይከተሉ፣ በቅናሽ ብር ስለሚገዙ፣ በቸልተኝነትና በለብ ለብ እንዲሁም ለትርፍ ብቻ ታስበው ስለሚሠሩ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሚገባቸውን ክፍያ እንዳያገኙ ከማድረጉ በተጨማሪ የፊልም ኢንዱስትሪው እንዲያሽቆለቁል በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ባለሙያዎች ይናገራሉ።

አሁን አሁን የሚሠሩ ፊልሞች በጥራታቸውም ሆነ በይዘታቸው በጣም የወረዱ እና ለፊልም ኢንዱስትሪው የማይመጥኑ ሥራዎች በብዛት እየተስተዋሉ የሚገኙትም በዚሁ ምክንያት ነው።

በተለይ ከኮቪድ ወረርሽኝ መከሰት በኋላ በዩቲዩብ የሚለቀቁ ፊልሞች የድምጽና የምስል ጥራት የሌላቸው፣ የማጀቢያ ሙዚቃዎቻቸው ብዙም የማይጥም፣ ወጥ የሆነ ቃለ ተውኔት እንኳን የማይታይባቸውና ክህሎት የሌላቸው ባለሙያዎች የሚሳተፉበት የፊልም አሠራርን የተከተሉ ሆነዋል።

በተለያዩ የዩቲዩብ ቻናሎች የሚጫኑ ፊልሞች ብዙ እይታ እንደሚያገኙ ብዙዎች ይስማሙበታል። ሆኖም በእነዚህ ዩቲዩብ ቻናሎች የሚጫኑ ፊልሞች ጥራት ከሌላቸው እንዴት እይታ እንደሚያገኙ አስገራሚ ነው። አንድ ፊልም በዩቲዩብ ብዙ እይታ አገኘ ማለት ጥራት አለው ማለት ግን አይደለም።

በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሙያውን ሥነ ምግባር ተከትለው ኢንዱስትሪው እንዲያድግ እና በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ተግተው የመሥራት ኃላፊነት እንዳለባቸው እሙን ነው። ሆኖም በፊልም ሥራ ላይ ልምድ ያካበቱ ባለሙያዎች በተለይ የዩቲዩብ ፊልሞች ከመጡ በኋላ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሥነ ምግባር ክፍተት እንደሚታይባቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ።

በሌላው አገር ላይ ፊልም ሲባል፣ ሕዝብና ባለሙያው አይደለም መንግሥት ራሱ ስለዘርፉ በደንብ አድርጎ ይገነዘባል። የፊልም ዘርፍ ትልቅ ገበያ መሆኑን የተረዱ ብዙ አገራትም ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተው ትምህርት ቤቶችን፣ ስቱዲዮ እንዲሁም ዕቃዎችን ያሟላሉ። እኛ ጋር ግን የተገላቢጦሽ ነው። ዘርፉን መቶ በመቶ ተሸክመው የሚጓዙት በራሳቸው የሚጥሩ ባለሙያዎች ናቸው። በዚህ መንገድ የተሠራ ፊልም ደግሞ ውጤቱ ውስንና ደካማ እንደሚሆን ግልፅ ነው።

የአገራችን ፊልም ዘርፍ ገብተው ከሚሠሩ ተዋናዮች ብዙዎች የሚሞገሱና የሚወደዱ ባለሙያዎች አይጠፉም። እሱ ወይም እሷ ያለችበት ፊልም ከሆነ ያምራል የሚባልላቸው ተዋናዮች ስለመኖራቸው መካድ አይቻልም። በአንጻሩ ደግሞ በቀላሉ ዕድሉን ስላገኙ ብቻ ወደ ፊልም ሥራው ዘው ብለው የሚገቡ ቁጥራቸው ቀላል እንዳልሆነ የታወቀ ነው። እንደሌሎች አገሮች እጅግ ትልቅ በሆነ የፊልም ትምህርት ቤት ተምሮና በተደራጀ ሥርዓት ውስጥ ገብቶ የሚሠራ ባለሙያ አለ ብሎ ለመናገር ከባድ ነው። ይህም ተዋናዮች ወደ ዘርፉ የሚመጡበት መንገድ ደካማ እና የፊልም ሳይንሱ በሚጠይቀው መንገድ ከመሄድ ይልቅ በባህላዊ መንገድ መሆኑን ያሳያል። እዚህ ችግር ላይ አሁን ስጋት እየሆነ የመጣው የዩቲዩብ ጉዳይ ሲጨመር ወትሮም ህፀፅ የማያጣው የፊልም ኢንዱስትሪ ከድጡ ወደ ማጡ እንዲያመራ ይበልጥ ሁኔታዎች ምቹ እየሆኑ እንዲሄዱ ማድረጉ አይቀርም።

ትክክለኛ ፊልም ለመሥራት ቢያንስ ዘጠኝ ወር እንደሚፈጅ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሦስት ወር ለቅድመ ዝግጅት፣ ሦስት ወር ለቀረጻና ሦስት ወር ለአርትኦት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ይህ ተግባራዊ ሲሆን አይታይም። እንዲያውም አሁን አሁን አንድ ፊልም ካፌ ውስጥ ወይም ኮንዶሚንየም ውስጥ ታስቦ ያልቃል ተብሎ ይታማል። በዚህ ላይ አንድ ተዋናይ በሆነ ምክንያት ቢያቋርጥ አንዱ ብድግ ብሎ የሚቀጥልበት ሁኔታም ከፊልሞች ባሻገር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ጭምር እንዲስተዋል አድርጓል።

ኢንዱስትሪው ወትሮም በሃይማኖት፣ በታሪክ፣ በባህል፣ በአመጋገብና በአለባበስ ውስጥ ያለውን አገራዊ የኪነጥበብ ሀብት ወደ ፊልም በመቀየር ረገድ ያለበትም ክፍተት ሙያው እያደገ ሲመጣ ይቀረፋል የሚል ተስፋ ቢኖረውም በተቃራኒው ሌላ እንቅፋት ከፊቱ ገጥሞታል።

ይህን ችግር ለመቅረፍ መንግሥትና ባለሙያዎች በአንድ መስመር አብረው መሮጥ ከቻሉ ዘርፉን መታደግ የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ነው። በዚህም የአገርን ገጽታ ለመገንባት፣ የቱሪዝም ገበያውን ለማስተዋወቅ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ይቻላል።

ባለሙያዎች እንደሚሉትም፣ የአገርን ገጽታ ከፍ አድርገው የሚያሳዩና በዓለም አቀፍ የፊልም መድረኮች ላይ ተገኝተው ለዓለም መታየት የሚችሉ የፊልም ጽሑፎች ይመጣሉ። ነገር ግን፣ በተለይ ጽሑፉን ወደ ፊልም ለመቀየር አስቸጋሪ በሆነው የአገራችን ቢሮክራሲና በወጪው ምክንያት የሚሠራው የታሰበው ሳይሆን የተቻለው ብቻ ነው።

ብዙ ባለሙያዎችም እስኪሰለቻቸው ድረስ ዘርፉ ባለቤት እንዲኖረውና በተቋም እንዲመራ መንግሥትን ሲወተውቱ እንደቆዩ ይናገራሉ። መንግሥት የፊልም ኮሚሽን አቋቁሞ አገሪቱን የሚያስተዋውቁ ሥራዎችን ማበረታታትና የፊልም ወርክሾፖችንና ትምህርት ቤቶችን መደገፍ እንዳለበት አስፈላጊ መሆኑንም ይጠቅሳሉ።

መንግሥት ይህንን ዘርፍ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የአገሪቱን ባህል ለሌሎች ለማስተዋወቅ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ሊጠቀምበት ይችላል። ለዚህ ደግሞ የደቡብ አፍሪካንና የናይጄሪያን ልምድ ማየት በቂ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የፊልም ቁሳቁስ ላይ የሚጣሉ ቀረጦች ላይ ማስተካከያ ቢደረግ የአገር ውስጥ ፊልም ሠሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የውጭ ባለሙያዎችም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሠሩ በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ሊገኝ ይችላል።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የነፍሰ ጡሯ ሊስትሮ የሕይወት ውጣ ውረድ


ሰላማዊት ውቤ

መቅደስ ደስታ ትባላለች፡፡ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የመጣችው የዛሬ ስድስት ዓመት ነው፡፡ ለአዲስ አበባ እንግዳ ብትሆንም ሕይወቷን ለመግፋት የሰው እጅ መመልከትን አማራጭ አላደረገችም፡፡ ከአንድ ሁለት ይሻላል በሚልም የሚመስላትን አግብታ ከአዲስ አበባን ኑሮ ጋር መጋፈጥ ከጀመረች ሰነባብታለች፡፡

የተገኘውን ሥራ ከመሥራት አንስቶ ከኑሮ ውድነቱ ጫና ራሷን ለማዳን መሸሸጊያ ያደረገችው ጥንድ ሆኖ ጎጆ የሚሞቅበትን ትዳር ነው፡፡ 20 ዓመቷን የያዘችው ገና በዚህ ወር ቢሆንም 16ኛ ዓመቷን እንደያዘች የወለደቻት አንዲት የአራት ዓመት ሴት ልጅ አለቻት፡፡ አሁን ላይ ደግሞ ሁለተኛ ልጇን ለመውለድ የተቃረበች የሰባት ወር ነፍሰ ጡር ናት፡፡ መቅደስን ያገኘናት አራት ኪሎ አካባቢ ጫማ ስትጠርግ ነው፡፡ የወንድ ተብሎ በሚፈረጀው የጫማ መጥረግ ሥራ(ሊስትሮ) መሰማራትና በተለይም ነፍሰ ጡር ሆኖ ጫማ መጥረግ ጎንበስ ቀና ማለት የሚጠይቅ አስቸጋሪ በመሆኑ ብዙዎች አድናቆታቸውን ሲቸሯት ተመልክተናል፡፡

ወደ ጫማ መጥረግ ሥራ የገባችውም በድንገት እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ‹‹ጫማ ይጠርግ የነበረው ባለቤቴ አባቱ ሞተውበት ውርስ ለመካፈል ወላይታ ዞን ወደ አለችው በዴሳ ወረዳ ያሉት ቤተሰቦቹ ጋር ሲሄድ እኔ የእሱን ቦታ ተክቼ መሥራት ጀመርኩ፤ከዛ ጊዜ ጀምሮም ሙያውን ወደድኩት›› ትላለች ፡፡ በርግጥ ከማርገዟ በፊት ቱሪስት ፊት ለፊት ያለው ፓርኪንግ ነበር የምትሠራው፡፡ ሥራውን ከወላይታ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣች አንዲት አዲስ አበባ ከተማ የምትኖር ዘመዷ ነበረች ያስገባቻት፡፡ ታዲያ ባለቤቷ ሊስትሮ እሷ ደግሞ ፓርኪንግ እየሠሩ በ1ሺህ 200 ብር ፈረንሳይ አካባቢ ቤት ተከራይተው በጋራ ይኖሩ እንደነበር መቅደስ ትናገራለች፡፡

‹‹ባለቤቴን ያገኘሁት አዲስ አበባ በመጣሁ በ15ኛው ቀኔ ነው፡፡ በተዋወቅን በሦስት ወርም አገባሁት››የምትለው መቅደስ ማግባቷ በጋራ በመኖር ኑሮ ውድነቱን በመተጋገዝ እንድታቀለው ያስቻላት መሆኑን ታወሳለች፡፡ ሆኖም ገና 16ኛ ዓመቷን በያዘችበትና በዛው በተጋቡበት ወር የመጀመሪያ ልጇን አረገዘች፡፡ እንደነገረችን ታድያ እዚህ አዲስ አበባ መውለድም ሆነ ልጅ ማሳደግ ከባድ በመሆኑ ባለቤቷ ቤተሰቦች ጋር እዛው እሷ ትውልድ አካባቢ ወላይታ ሄዳ ተገላገላለች፡፡ የባለቤቷ ቤተሰቦች እርሻ ያላቸውና የተሻለ ኑሮ የሚኖሩ በመሆናቸው ልጇን እዛው እነሱ ጋር ትታ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰች፡፡



አሁን ደግሞ ሁለተኛ ልጇን አርግዛለች፡፡ ካረገዘች ሰባተኛ ወሯን ይዛለች፡፡ በቀጣይም ሥራን ሳታማርጥ የተገኘውን ሁሉ በመሥራት ልጆቿን የማሳደግ ዓላማ እንዳላት አጫውታናለች፡፡ ምክንያቱም አዲስ አበባ ከተማ ላይ ከየትኛውም በአገሪቱ ያለ ሥፍራ በላይ ኑሮ ውድ ነው፡፡ በየወሩ የሚከፈል የቤት ኪራይ ወጪ እንዲሁም በየቀኑ የቀለብ፤የትራንስፖርት ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል የገንዘብ ገቢ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ሁሉ ለማሟላት ደግሞ ሥራን ሳይንቁ መሥራት ግድ ይላል፡፡

መቅደስ ልጇን ለመውለድና ለማሳደግ እሷ እንደ ቀድሞው ባለቤቷ ቤተሰቦች ጋር መሄድ አትፈልግም፡፡ ስለዚህ አሁን ያረገዘችውን ልጇን ለመውለድና ለማሳደግ ያሰበችው እዚሁ አዲስ አበባ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ አማራጭ የያዘችውን የሊስትሮ ሥራ አጠናክሮ መሥራት ነው፡፡ በተሻለ መልኩ ለመሥራትም የሊስትሮ ሳጥን ገዝታለች፤ የጫማ ቀለሞችንም እያሟላች ነው፡፡

መቅደስ እንደምትናገረው ሴት ልጅ ስትሠራ ደስ የሚላቸው የሚያበረታቷት ብዙ ሰዎችን መመልከቷን ትናገራለች፡፡ ከወዲሁ ቋሚ ደንበኛ የሆኗት በርካታ ሰዎች እንዳሉም ትገልጻለች፡፡ ከ25 እስከ 50 ብር ድረስ ጉርሻ የሚሰጧት ደንበኞችም እንዳሉ አጫውታናለች፡፡

መቅደስ ከልጅነቷ ጀምሮ መከራ ቢፈራረቅባትም እጅ እንዳልሰጠች ትናገራለች፡፡ እናቷ የስድስት ወር ልጅ ሳለች ከአባቷ ጋር በመጋጨታቸው ጥላት እንደሄደች አባቷ ነግረዋታል፡፡ በእንጀራ እናት ያደገችው መቅደስ በእንጀራ እናቷ ብዙ በደሎች ደርሰውብኛል ትላለች፡፡ ‹‹ገና ሕፃን ሳለች ጀምሮ ነበር ከባድ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ታሠራኝ ነበር፡፡ በጨቅላ ዕድሜዬ የአዋቂ ልብሶችን ታሳጥበኛለች፡፡ ደግሞ ልብስ ማጥበው ወንዝ ወርጄ በመሆኑ ለኔ ከባድ ነበር፡፡ ልብሶቹን ተሸክሞ ወደ ወንዝ መሄዱ በራሱ በጣም ያደክማል፡፡ የቤት ውስጥ ሥራዎችንም የምሠራው እኔ ነኝ፡፡ ቤት ማጽዳቱ፤ከብት መጠበቁ፤ምግብ ማዘጋጀቱ የእኔ ዕዳዎች ነበሩ፡፡ ያለ አቅሜ የበቆሎ ገንፎ ታሠራኝና ሲጓጉልብኝ ትገርፈኝ የነበረውን መቼም አልረሳውም›› ትላለች መቅደስ የልጅነት ሐይወቷን ስታስታውስ፡፡

መቅደስ እንደምትናገረው ከፍ እያለች ስትመጣ የእንጀራ እናቷ የምታሠራት ሥራም ጫናው እየጨመረ መጣ፡፡ እንዲህም ሆኖ አባቷ ‹‹እሷ ትምህርት ቤት ከገባች የቤቱን ሥራ ማን ሊሠራ ነው››ስትል ትምህርት ቤት መግባቷን ተቃውማ ለነበረችው ባለቤቱ ጆሮ ሳይሰጥ በአካባቢው የሚገኝ ፋና የተሰኘ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት አስገብቷት ነበርና ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታለች፡፡ እውነት ለመናገር በፈጣሪ ኃይል ከክፍል ክፍል ትዛወር እንጂ ስምንተኛ ክፍል እስከትደርስ ድረስ ለደረሰችበት ደረጃ የሚመጥን ዕውቀት እንዳልቀሰመች ትናገራለች፡፡

እንጀራ እናቷ በተደጋጋሚ የሰጠሁሽን ሥራ ሳትጨርሽ ትምህርት ቤት እትሄጂም ስለምትላት ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት ትቀር ነበር፡፡ አብዛኛውን ጊዜም ታረፍዳለች፡፡ ትምህርት ያመልጣታል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት በቅጡ ለማንበብና ለመፃፍ እንኳን ይቸግራት እንደነበርም ትናገራለች፡፡ ትምህርቷን እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ ነው የተከታተለችው፡፡ የስምንተኛ ክፍል ትምህርቷንም ቢሆን ከእንጀራ እናቷ ጋር የመረረ ፀብ ውስጥ በመግባቷ ምክንያት ከቤት በመውጣቷ ምክንያት ከሦስት ወር በላይ የመከታተል ዕድል አላገኘችም፡፡

ሆኖም ያቀረጠችው ትምህርት ያንገበግባታል፡፡ ተምራም ሰው ለመሆን ዕቅድ አላት፡፡ በሚቀጥለውም ዓመት በማታው ክፍለ ጊዜ ተመዝግባ ትምህርቷን ለመቀጠል ከወዲሁ አስባለች፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ተስፋ ያየችበትንና በርካታ ደንበኞች ያፈራችበትን የሊስትሮ ሙያ በማጠናከር ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና በማለት ላይ እንደምትገኝ እኛም ከእርሷ ጋር በነበረን ጥቂት ቆይታዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በኡጋንዳ ትምህርት ቤት ጥሶ የገባው ተሽከርካሪ ተማሪዎችን ገደለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በኡጋንዳ ዋና ከተማ አቅራቢያ ወዳለ አንድ ትምህርት ቤት ክፍል ጥሶ የገባ ከባድ ተሽከርካሪ ሦስት ተማሪዎችን ገደለ።

ከባድ የጭነት ተሽከርካሪው ከዋና ከተማዋ ካምፓላ 130 ኪሎ ሜትሮች ርቃ በምትገኘው ጎምቤ በተባለችው አካባቢ አደጋውን መድረሱን ቢቢሲ ዘግቧል።

በአደጋው ከሞቱት ሦስት ተማሪዎች በተጨማሪ በክፍሉ ውስጥ የነበሩ ቢያንስ 18 ተማሪዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል።

አደጋውን ተከትሎ የኡጋንዳ ፖሊስ እንዳለው የጭነት ተሽከርካሪው ከአሽከርካሪው ቁጥጥር ውጪ ከሆነ በኋላ የትምህርት ቤቱን አጥር ጥሶ ገብቷል።

በትምህርት ቤቱ ውስጥም በርካታ ተማሪዎች የነበሩበትን የኮምፒውተር ቤተ ሙከራን ግማሽ ጎን አፍርሶ በመግባት በሕይወት እና በአካል ላይ ጉዳት አድርሷል።

የከባድ መኪናው ግማሽ አካል ተማሪዎች የነበሩበትን ክፍል ጥሶ በመግባት የክፍሉን ጣራም ገነጣጥሎታል። አደጋ ያደረሰውን የጭነት መኪናን ሲያሽከረክር የነበረው የ26 ዓመት ሾፌር በቁጥጥር ስር ውሎ በፖሊስ ምርመራ እየተደረገበት ነው።

አደጋውን ተከትሎ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማደስተማር ሂደት እንዲቋረጥ ተደርጎ ተማሪዎች ለአንድ ሳምንት በቤታቸው እንዲቆዩ ታዘዋል።

በአደጋው ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች ስላሉ የሟቾች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል የኡጋንዳ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። አደጋውን ያደረሰው ሲኖትራክ በመባል የሚታወቀው ከባድ የጭነት መኪና መሆኑን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ተናግረዋል።

ከተማሪዎች በተጨማሪ በኮምፒውተር ቤተ ሙከራው ውስጥ የነበሩ አንዲት መምህርም የእጅና የእግር ስብራት አደጋ ደርሶባቸዋል።

## አሜሪካ ድሮኗ በጥቁር ባሕር ላይ መውደቁን አስታወቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ ሰው አልባ በራሪ አውሮፕላን /ድሮኗ/ በጥቁር ባሕር ላይ መውደቁን አስታወቀች።



ከአሜሪካ የቅኝት ሰው አልባ በራሪ አውሮፕላኗ ከሩሲያ የጦር ጀት ጋር ተጋጭቶ ጥቁር ባሕር ላይ መውደቁን ገልጿ፣ ድርጊቱንም ኃላፊት የጎደለው ነው ማለቷን ቢቢሲ ዘግቧል።

አሜሪካ ድሮኑ በዓለም አቀፍ የአየር ክልል ውስጥ በመደበኛ የቅኝት በረራ ላይ እንዳለ ሁለት የሩሲያ ተዋጊ ጀቶች ሊጠልፉት እንደሞከሩ ገልጻለች።

ክስተቱ በዩክሬኑ ጦርነት ምክንያት ሩሲያ እና አሜሪካ ቀጥተኛ ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ የተፈጠረውን ስጋት አጉልቶታል።

ሆኖም ሩሲያ ተዋጊ ጀቶቹ ከድሮኗ ጋር ምንም አይነት ግኑኝነት አልነበራቸውም ብላለች። የሩሲያ የመከላከያ ሚኒስቴር ድሮኑ በራሱ ምክንያት መውደቁን ጠቁሟል።

ኤምኪው 9 የተባሉት የጦር አውሮፕላኖችን በዓለም አቀፍ የአየር ክልል ውስጥ እየተንቀሳቀሰ በነበረበት ጊዜ በሩሲያ የጦር አውሮፕላን ተጠልፎ ተመቷል። በውጤቱም ድሮኑ ተከስክሶ ወድሟል ሲል የአሜሪካ መንግሥት ባወጣው መግለጫ ገልጿል።

ድርጊቱን በመቃወም አሜሪካ በዋሽንግተን የሚገኙትን የሩሲያ አምባሳደር አናቶሊ አንቶኖቭን ለማብራሪያ ጠርታለች።

ንግግሩንም ተከትሎ የሩሲያ መንግሥት መገናኛ ብዙኃን አምባሳደር አንቶኖቭን ጠቅሰው እንደዘገቡት፣ ሩሲያ የድሮኑን ክስተት እንደ ትንኮሳ እንደምትቆጥረውና የአሜሪካ ጦር ከድንበራችን አቅራቢያ ስጋት ሊጭር የሚችል ድርጊት መፍጠሩ ተቀባይነት የለውም ብለዋል።

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2014 ሩሲያ ክሪሚያን ከጠቀለለች በኋላ በጥቁር ባሕር አቅራቢያ ውጥረት ነግሷል።

እንደ አሜሪካ ገልጻ ከሆነ ሩሲያ በቀጠናው ከሚገኙ የአሜሪካ አጋር አገራት አውሮፕላኖች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ተደጋጋሚ እና አደገኛ እንቅስቃሴዎችን ስታደርግ ቆይታለች።

ስለዚህ የአሜሪካ ድሮን ላይ የተፈጸመው ተግባር በዚህ ሂደት ውስጥ በስህተት የተፈጸመ ሊሆን ይችላል።

ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ ይህ ድርጊት በሩሲያ ሆን ተብሎ የተፈጸመ ከሆነ ከፍተኛ ውጥረት ሊያስከትል የሚችል ነው። ይህም ማለት የሩሲያ መንግሥት የአሜሪካንን ምላሽ ለመፈተሽ የፈጸመው ድርጊት ሊሆን ይችላል ተብሏል።

የአሜሪካ የጦር አዛዦች ድርጊቱ አደገኛ ነው ያሉ ሲሆን ይህም ወደተሳሳተ ስሌት እና ባልታሰበ ሁኔታ ሊባባስ ይችላል ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የትራንስፖርቱን ዘርፍ በታዳሽ የኃይል ምንጭ

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ ከመኪና ጋር የተዋወቀችው ከ115 ዓመታት በፊት፣ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው።በ1900 ዓ.ም የተጀመረው የኢትዮጵያና የመኪና ትውውቅ፣ብዙ ደረጃዎችን አልፎ ዛሬ ካለበት ደረጃ ደርሷል።መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ተሽከርካሪዎች ይገኛሉ።ይሁን እንጂ ከእነዚህ ተሽከርካሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እድሜያቸው የገፋ (አሮጌዎች) እና ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ያላቸው ናቸው።

በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ እየጨመረ ነው።ከዚህ በተጨማሪም በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚወጣውና ለአየር ብክለት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ጭስ የአካባቢ ሥነ ምሕዳር ትልቅ አደጋ ሆኖ ቀጥሏል።የነዳጅ ዋጋ መጨመር ያደጉም ሆኑ ታዳጊ ሀገራት አማራጭ የትራንስፖርት ዘርፎችን እንዲያማትሩ እያስገደዳቸው ነው። ከእነዚህ አማራጮች መካከል አንዱ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ነው። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በየጊዜው በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተሻሻሉና ተጠቃሚያቸውም እየጨመረ ይገኛል። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱት ተሽከርካሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ የራሳቸው የሆኑ ጥቅሞች አሏቸው።ለአብነት ያህል ከወጪ አንፃር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹን ባትሪያቸውን ሙሉ (Full) ለማድረግ የሚፈጀው ወጪ የነዳጅ ተሽከርካሪዎች ከሚፈልጉት ወጪ በ24 በመቶ ይቀንሳል። ተሽከርካሪዎቹ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀሙት በሀገር ውስጥ የተመረተ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው።የሀገር ውስጥ ኤሌክትሪክ የሚገኘው ደግሞ ከታዳሽ የኃይል ምንጮች ስለሆነ ይህ ዓይነቱ የኃይል አጠቃቀም እንደሀገር ጭምር ለነዳጅ የሚጣውን ወጪ ለመቀነስ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ምንም ዓይነት ጭስ ወደ ከባቢ አየር የማይለቁ በመሆናቸው የአየር ብክለትን በማስወገድ የአካባቢ ጥበቃን አስተማማኝ ለማድረግ ያስችላሉ።

ኢትዮጵያም በየዓመቱ ለነዳጅ ግዢ ከፍተኛ ገንዘብ ታወጣለች፤ይህም በውጭ ምንዛሪ ክምችቷ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። በሀገሪቱ የሚገኙት አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ያላቸው በመሆናቸው ከተሽከርካሪዎቹ የሚወጣው ጭስ ለአየር ብክለት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረገ ነው። እነዚህን ፈተናዎች ለመቀየር ከተጀመሩት ሥራዎች መካከል አንዱ የማበረታቻ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥትም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ ያላቸውን አንፃራዊ ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችንና አስመጪዎችን የሚያበረታታ እንዲሁም ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የታክስ ማሻሻያ ተግባራዊ ማድረጉን የገንዘብ ሚኒስቴር ማስታወቁ ይታወሳል። የታክስ ማሻሻያው ዓላማ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የተሽከርካሪዎች ቁጥር በፖሊሲ ማዕቀፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የሚስማማ ለማድረግ፣ በኅብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል፣ በአየር ንብረትና በብዝኃ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የማያሳርፍ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በአግባቡ የሚጠቀም የመጓጓዣ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ እንዲቀርቡ ለማስቻል እንደሆነም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

በዚህ የታክስ ማሻሻያ ከውጭ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኤሌክትሪክ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የቤት አውቶሞቢሎች



የባትሪ መሙያ መሠረተ ልማቶቹ የሚገነቡት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ነው

እና የእቃ መጫኛ ተሽከርካሪዎች ላይ ዝቅተኛ የጉምሩክ ታሪፍ የሚጣልባቸው ሲሆን ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ከኤክሳይዝ ታክስና ከሱር ታክስ ነፃ ይደረጋሉ። በታክስ ማሻሻያው መሠረት የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎችን በተመለከተም ሙሉ በሙሉ ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎች ከጉምሩክ ቀረጥ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተደርጓል። በከፊል ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎች አምስት በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተደርጓል።ሙሉ ለሙሉ ተገጣጥመው ያለቀላቸው የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎች ወደ ሀገር ሲገቡ ደግሞ 15 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡

የታክስ ማሻሻያው ከተደረገ በኋላም ከሰባት ሺ በላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታውቋል። ከዚህ በተጨማሪም በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አንድ ሺ 300 የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አውቶብሶችን ከውጭ አቅራቢዎች በዱቤ ለመግዛት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር መግባባት ላይ መደረሱንም ሚኒስቴሩ መግለፁ ይታወሳል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በርሆ ሁሴን እንደሚሉት፣ በትራንስፖርት ዘርፉ ምክንያት ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን በካይ ጋዝ መጠን በመቀነስ ለተፈጥሮ/አካባቢ ተስማሚ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የካርቦን ነዳጅ አጠቃቀምን መቀነስና ለአካባቢ ምቹ የሆኑ የትራንስፖርት አማራጮችን መጠቀም ይገባል።የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የበካይ ጋዝ ልቀትን በመቀነስ ለአካባቢ ምቹ የሆኑ የትራንስፖርት አማራጭን ለማቅረብ የሚያስችሉ ግብዓቶች ናቸው።

‹‹ለአካባቢ ብክለት አስተዋፅዖ ያለው ነዳጅ ዋጋው መጨመሩ፣ የኃይል አማራጭ በማፈላለግ ላይ ለሚገኘው የትራንስፖርት ዘርፍ ተጨማሪ ችግር ነው። አስፈላጊ እርምጃዎች ካልተወሰዱ እ.አ.አ እስከ 2050 ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ የሙቀት መጠን ከአንድ ነጥብ ስምንት እስከ ሁለት ነጥብ አንድ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደሚያድግ ጥናቶች ያመለክታሉ።በዓለም አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎችን የመጠቀም ልምድ እየተስፋፋ መጥቷል።የትራንስፖርት ፖሊሲ ያችን ታዳሽ፣ ተደራሽ፣ የተቀናጀ፣ የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ፣ ለአካባቢ ተስማሚና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የትራንስፖርት ሥርዓት ተዘርግቶ የማየት ራዕይን ይዞ የተቀረፀ ነው።ዘላቂና ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ የትራንስፖርት ሥርዓት መዘርጋት በብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲያችን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው›› ይላሉ።

በ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት ዘርፍ መገንባት ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን ጠቁመው፣ በእቅዱም 4800 አውቶብሶችን እና 148ሺ የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎችን ጥቅም ላይ ለማዋል መታቀዱንም አቶ በርሆ ይናገራሉ።የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የሰርቪስና የጥገና ወጪን የሚቀንሱ፣ ከድምፅ ብክለት የፀዱ፣ በየጊዜው እየተሻሻለ የመጣ የባትሪ ቴክኖሎጂና ረጅም የአገልግሎት ጊዜ ያላቸው እንዲሁም አካባቢን የማይበክሉ በመሆናቸው በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የተሻለ ተመራጭ በመሆናቸው የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝም ይገልፃሉ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢንጂነር ሱልጣን ወሊ በበኩላቸው፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ኢትዮጵያ ለነዳጅ ግዢ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ የምታደርገውን ጥረት ለማሳካት የሚያግዝ አማራጭ የመፍትሔአቅጣጫእንደሆነይናገራሉ። እንደርሳቸው ገለፃ፣ ኢትዮጵያ ከወጪ ንግድ ከምታገኘው ገቢ አብዛኛውን ለነዳጅ ግዢ ስለምታውለው በውጭ ምንዛሪ ክምችቷ ላይ ጫና እያሳረፈባት ነው። የነዳጅ ዋጋ እየጨመረ በመሄዱ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብትና በነዳጅ አቅርቦት ደህንነት ላይ መዛባት እየፈጠረ ነው። ስለሆነም ችግሩን በአጭርና በረጅም ጊዜ የመፍትሔ አማራጮች መፍታት ያስፈልጋል። በቅርቡ በሥራ ላይ የሚውለው የኢነርጂ ፖሊሲ የኤሌክትሪክ መጓጓዣዎችን ለማስፋፋት መደላድል የሚፈጥር፣ ታዳሽ ኃይል የሚጠቀም የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እንዲኖር የሚያስችል እና ኢትዮጵያ ከነዳጅ ጥገኝነት ለመላቀቅ የምታደርገውን ጥረት ለማሳካት የሚያግዝ ይሆናል። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አገልግሎት ላይ የማዋል አማራጭ ታዳሽ ኃይልን ለመጠቀም ያስችላል። ታዳሽ ኃይል ደግሞ ሀገሪቱ ለምትከተለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ትልቅ ሚና ይጫወታል፤ለካርበን ልቀት መቀነስም አስተዋፅዖ ያደርጋል። የኃይል መሙያ ማዕከላትን በግል ባለሀብቶችም ሆነ በመንግሥት መገንባት ተጨማሪ ገቢ ከማስገኘቱ ባሻገር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ተጨማሪ የሥራ እድል እድሎችን እንደሚፈጥር የሚናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሚኒስቴሩ በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች አቅርቦትና በኃይል መሙያ ጣቢያዎች ግንባታ ለሚሰማሩ ባለሀብቶችና ተቋማት ድጋፍ እንደሚያደርግም ተናግረዋል።


በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ከውጭ በማስመጣት ለገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶች አሉ። ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል አንዱ የሆነው ‹‹ግሪንቴክ ኢትዮጵያ›› ከ500 በላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችንወደሀገርውስጥአስገብቶአገልግሎቱን ለሚሰጡ ድርጅቶችና ለግለሰቦች አቅርቧል። የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ፍጹም ዴሬሳ እንደሚናገሩት፣ ‹‹ግሪንቴክ ኢትዮጵያ›› የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ከውጭ አስመጥቶ ለገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ በቀጣይ ሦስት ወራት ተሽከርካሪዎቹን በሀገር ውስጥ ገጣጥሞ ለገበያ ለማቅረብ አቅዶ እየሠራ ይገኛል። ይህን እቅዱን ለማሳካትም ሰንዳፋ ላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ፋብሪካ እየገነባ ነው።ድርጅቱ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መገጣጠም በሚጀምርበት የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት 300 መኪኖችን የመገጣጠም እቅድ ያለው ሲሆን፣ በቀጣይ ጊዜያት ሥራውን ይበልጥ በማስፋት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ አምርቶ የመሸጥ እቅድም አለው፡፡

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለው የሚናገሩት ዋና ሥራ አስኪያጁ፣ ከዋጋ አዋጭነት፣ ከውጭ ምንዛሪ ቁጠባ እና ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ተመራጭ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ‹‹መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ የወሰዳቸው እርምጃው የሚደነቁ ናቸው›› የሚሉት ኢንጂነር ፍፁም፣ የታክስ ማሻሻያው ለዘርፉ እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለውና በዘርፉ የተሠማሩ አካላት ተሽከርካሪዎችን ከማስመጣት ባሻገር ገጣጥመው እንዲሸጡና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ እንደሚያበረታታ ያስረዳሉ።

‹‹ግሪንቴክ ኢትዮጵያ›› የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መገጣጠሚያ ፋብሪካውን ከመገንባት ጎን ለጎን የጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በጀመረው ሥራ ለ25 ወጣቶች የአራት ወር ሙሉ ስልጠና ሰጥቷል፤ቀጣይ ዙር ሰልጣኞችንም እያስተማረ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም ተሽከርካሪዎቹ አስተማማኝ የኃይል ምንጭ እንዲያገኙ የሚያስችሉ 45 የባትሪ መሙያዎችንም (Charging Stations) አዘጋጅቷል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አገልግሎት ላይ የማዋሉ ተግባር ስኬታማ እንዲሆን ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች መካከል አንዱ ለተሽከርካሪዎቹ ኃይል የሚያቀርቡ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችን መገንባት ነው።‹‹ካርዲናል ኢንዱስትሪ›› የተባለው ኩባንያ ይህን ተግባር ለማከናወን በ25 ሚሊዮን ዶላር የመነሻ በጀት ሥራ ጀምሯል።የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሊሊያ ኃይሉ እንደሚሉት፣ ኩባንያው በመጀመሪያው ዓመት 500 የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችን ለመትከል አቅዷል። የጣቢያዎቹ ቁጥር በየዓመቱ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን፤ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችን የመትከል ሥራውን በቅድሚያ በአዲስ አበባ ከተማ በመጀመር፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን የመጠቀም ልምድ እየዳበረ ሲሄድ ወደ ሌሎች ከተሞች ለማስፋፋት ጥረት እንደሚደረግም ተናግረዋል።‹‹ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ መገንዘብ እንደሚቻለው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን የመጠቀም ልምድ እንዲጨምር አስተዋፅዖ ከሚያደርጉት ነገሮች ዋነኞቹ የኃይል አቅርቦት እና የባትሪ መሙያ መሠረተ ልማት አቅርቦት ናቸው። የጣቢያዎቹ ቁጥር ሲጨምር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን የመጠቀም ልምድም እየዳበረ ይሄዳል ተብሎ ይጠበቃል›› ይላሉ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በበኩሉ ለሥራው ስኬት ኃይል እና መሠረተ ልማት ያቀርባል።የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን እንደሚናገሩት፣ መሠረተ ልማቶቹ የሚገነቡት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ነው።ይህም ሰፊ የተደራሽነት እድልን ይፈጥራል።ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ኃይል የሚያቀርብ ራሱን የቻለ የኃይል መስመር በማዘጋጀትና ተጨማሪ ኃይል ለማምረት የሚያስችል አቅም በመጠቀም ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የሚቀርበው ኃይል አሁን ባለው የኃይል አቅርቦት ላይ ተፅዕኖ ማሳረፍ እንዳይችል ዝግጅት ተደርጓል።አሁን ባለው ኃይል የማመንጨት አቅም በዓመት እስከ አንድ ሺ ጊጋ ዋት ሰዓት ኃይል ማቅረብ የሚቻልበት አቅም አለ። በመጀመሪያው ዓመት ሊተከሉ ከታቀዱ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችም በዓመት እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዷል፡፡



# ስፖርት



## ዋሊያዎቹ በአቋም መለኪያ ጨዋታ ሩዋንዳን ይገጥማሉ

ብርሃን ፈይሳ

በአፍሪካ ትልቁ የእግር ኳስ መድረክ የሆነውና ተወዳጁ የአፍሪካ ዋንጫ ለ34ኛ ጊዜ በተያዘው ዓመት መጨረሻ በምዕራብ አፍሪካዊቷ ሃገር ኮትዲቯር አዘጋጅነት ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ተካፋይ ከሚሆኑት 24 ሃገራት መካከል ለመካተትም 44 ብሔራዊ ቡድኖች በ12 ምድቦች ተደልድለው ካለፈው ዓመት ጀምሮ የማጣሪያ ፍልሚያቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በማጣሪያ ውድድሩ ላይ እየተካፈሉ ከሚገኙት ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም በምድብ አራት ከግብጽ፣ ማላዊ እና ጊኒ ጋር ተደልድላ በመወዳደር ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋሊያዎቹ) የምድቡን ወሳኝ ሦስተኛ እና አራተኛ ጨዋታዎችም ከቀናት በኋላ የምታደርግ ይሆናል። መጋቢት 15 እና 18/2015 ዓም ከጊኒ ብሔራዊ ቡድን ጋር ለሚካሄደው ጨዋታም የዋሊያዎቹ ዋና አሰልጣኝ ውበቱ አባተ ከቀናት በፊት የቡድናቸውን 23 ተሰላፊዎች ማሳወቃቸው የሚታወስ ነው። ጥሪ የተደረገላው የቡድኑ አባላትም ከትናንት አንስቶ ወደ ዝግጅት መግባታቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስታውቋል።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) የስታዲየሞች ዝቅተኛ መስፈርትን ባለማሟላቷ የትኛውንም አህጉር እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሃገሯ እንዳታስተናግድ የታገደችው ኢትዮጵያ ይህንንም ጨዋታ በሰው ሃገር በውሰት ሜዳ ላይ ታከናውናለች። ከደጋፊውና ከሜዳው ከሦስት ዓመታት በላይ ርቆ ለመጫወት የተገደደውና «ስደተኛው» የሚል ቅጽል የተሰጠው ብሔራዊ ቡድኑ (ዋሊያዎቹ) ከጊኒ አቻው ጋር ያለበትን ጨዋታ በሞሮኮ ካዛብላንካ የሚያደርግ ይሆናል። ከሦስት ቀናት በኋላ ደግሞ ሁለቱ ሃገራት ራባት ላይ የመልስ ጨዋታቸውን በልዑል ሞላይ አብዱላህ ስታዲየም ያከናውናሉ።



ዋልያዎቹ ከነገ በስቲያ በአቋም መለኪያ ጨዋታ ሩዋንዳን ይገጥማሉ፣

ዋሊያዎቹ ላለባቸው ግጥሚያ የሚሆናቸውን የዝግጅት ጨዋታም ከሩዋንዳ ብሔራዊ ቡድን ጋር እንደሚያደርጉ ታውቋል። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በያዘው መርሐ ግብር መሠረትም የአቋም መለኪያ ጨዋታው በመጪው እሁድ መጋቢት 10/2015 ዓም በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስታዲየም የሚከናወን ይሆናል። በማጣሪያ ውድድሩ ላይ ሩዋንዳ በምድብ 12 ከሴኔጋል፣ ሞዛምቢክ እና ቤኒን ጋር የተደለደለች ሲሆን፤ ከሞዛምቢክ ጋር አቻ በመውጣት እንዲሁም በሴኔጋል ሽንፈትን አስተናግዳ በአንድ ነጥብ ከምድቡ ሦስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች።

በዚህ የማጣሪያ ውድድር ኢትዮጵያ ከማላዊ ጋር በነበራት የመጀመሪያ የማጣሪያ ጨዋታ 68ኛው ደቂቃ ላይ ያገኘውን ቅጣት ምት በመጠቀም የመጀመሪያዋን ግብ ለሃገሩ ያስቆጠረው ወጣቱ አጥቂ አቡበከር ናስር በቅዳሜው የወዳጅነት ጨዋታ ላይ እንደማይሰለፍ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል። ለደቡብ አፍሪካው ታላቅ ቡድን ማሜሎዲ ሰንዳውስ በመጫወት ላይ የሚገኘው የ23 ዓመቱ አቡበከር በዚህ ጨዋታ ላይ የማይሰለፈው በገጠመው ጉዳት ምክንያት ነው። ተጫዋቹ ከጉዳቱ ሙሉ ለሙሉ አገግሞ ከቀናት በኋላ በሞሮኮ ከጊኒ ጋር ለሚካሄደው ግጥሚያ እንደማይደርስም ተረጋግጧል። በመሆኑም በተጫዋቹ ምትክ በፕሪሚየር ሊጉን ጥሩ ተፎካካሪ ሆኖ የሚገኘው ኢትዮጵያ መድን አጥቂ የሆነውና በቻን ውድድር ላይ የብሄራዊ ቡድን አባል የነበረው ኪቲካ ጀማ ዋሊያዎቹን በመቀላቀል በሞሮኮ የሚካሄዱት ቀጣይ ጨዋታዎች ላይ የሚካፈል ይሆናል።

ዋሊያዎቹ የማጣሪያ ጨዋታቸውን በማላዊ የ2ለ1 ሽንፈት የጀመሩ ቢሆንም፤ ከቀናት በኋላ እዚያው ማላዊ ላይ ግብጽን በማስተናገድ የ2 ለምንም ጣፋጭ ድል ማስመዝገባቸው የሚታወስ ነው። በዚህም ኢትዮጵያ ከሁለት ጨዋታ 3 ነጥብ እና 1 የግብ ልዩነት በመያዝ ምድቡን በመምራት ላይ ትገኛለች።

## ኦሮሚያ ክልል

በይግባኝ ባዮች እነ አለማየሁ ነገሌ እና ሦስት ሰዎች እና በመልስ ሰጪ ውል ሰጪዎች እነ ሁሩሜ ነገሌ እና 7 ሰዎች መካከል ያለውን የውርስ ንብረት ክፍፍል ክርክር አስመልክቶ አቶ ነገሰ ነገሌ መከሰሳቸውን አውቀው በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ ለቀጠሮው ቀን ለ11/7/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡20 እንድታቀርቡ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## ሲዳማ ክልል

የንብረት ባለቤት ስም በላቸው ለማ የሻንሲ ቁጥር JTFW5726100007030 የሞተር ቁጥር 2KD-0990636 የተሽከርካሪ ሞዴል KDN170L የሠሌዳ ቁጥር 2 ሲዲ-00324 የተሽከርካሪው ዓይነት የጭነት የሊብሬ ቁጥር 010289 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ የኋላ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ24/5/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ የመኪናውን ሠሌዳ ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሾች 1ኛ አቶ ቻላቸው በዛብህ ወርቅነህ 2ኛ ወ/ሮ መልካም ቢያድግ ካሣ እና በተከሳሾች 1ኛ አቶ አንዱአምላክ ዮሐንስ ወዳጆ እና ወይም አቶ አንዱአምላክ አለሸኝ ወዳጆ 2ኛ. አቶ ተሾመ ሁሪሳ 3ኛ. ወ/ሮ በቀለች ድንቁ ወይም ወ/ሮ በቀሉ ድንቁ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች ለ11/7/2015 ዓ.ም በ8፡40 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ እንዲያውቁ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ማርታ አበራ ተገኝ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B10026 የተሽከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KSP90-5170379 ሞዴል DBA-KSP90-AHXNK የሞተር ቁጥር 1KR0992709 የሊብሬ ቁጥር 235529 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ6/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገኛ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች አሰፋ አብርሃም ገብረመስቀል እና ተጠሪ አመለወርቅ ታምራት ተጠሪ ከየካቲት 8 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለመሆኑ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም አመለወርቅ ታምራት ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ26/7/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎት**


## Changing Tender Opening date

As we known our organization people in need has inviting the potential suppliers who offers diffirent sewing machine & leather goods on the date 14/03/23. How ever we would like our potential bidders that the opining time of this tender mentioned 11:50 Am (morning 5:30 local time) be changed to 11:30 Am (Morning 5:30).

**International non profit non government organization**


ሕብረት ባንክ Hibret Bank

**ለአቶ ሲራክ አስረስ መልካ**
**በአዋጅ ቁጥር 97/90**
**መሠረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ፣**

እርስዎ አቶ ሲራክ አስረስ መልካ ከሕብረት ባንክ አ.ማ ኮተቤ መሳለሚያ ቅርንጫፍ የተበደሩትን ብድር ወቅቱን ጠብቀው ባለመክፈልዎ ምክንያት ያዘጋጀነውን ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በአድራሻዎ ለማድረስ ጥረት ያደረግን ቢሆንም ልናገኝዎ አልቻልንም፡፡ ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቀሪውን ዕዳ በጠቅላላው እንዲከፍሉ እያስጠነቀቅን ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለብድሩ በዋስትና ያስያዙትን ንብረት በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድደሩ መክፈያነት ለማዋል የምንገደድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ሕብረት ባንክ አ.ማ.**

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

**ለአቶ ይልማ ተክልዬ ወ/ሰንበት እና ለአቶ ዜና ተድላ**
**በአዋጅ ቁጥር 97/90**
**መሠረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ፣**

እርስዎ አቶ ይልማ ተክልዬ ከሕብረት ባንክ አ.ማ አረርቲ ቅርንጫፍ የተበደሩትን ብድር ወቅቱን ጠብቀው ባለመክፈልዎ ምክንያት እንዲሁም አቶ ዜና ተድላ ለብድሩ መልሶ መክፈል ዋስትና ንብረቶችን በመያዣ ያስያዙ በመሆኑ ያዘጋጀነውን ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በአድራሻችሁ ለማድረስ ጥረት ያደረግን ቢሆንም ልናገኛችሁ አልቻልንም፡፡ ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቀሪውን ዕዳ በጠቅላላው እንዲከፍሉ እያስጠነቀቅን ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለብድሩ በዋስትና ያስያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድሩ መክፈያነት ለማዋል የምንገደድ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**ሕብረት ባንክ አ.ማ.**